ማውጫ

ርእስ ገጽ

የተርጓሚው ማስታወሻ 4
መግቢያ 5
ቁርአንና ሱንና ለጊዜ የሰጡት ትኩረት 7
የእስልምና አምልኮና ስርዓት የጊዜን ዋጋ ያጸናሉ 10
የጊዜ ልዩ ባህሪያት 13
1 በፍጥነት መጓዙ 13
2 ያለፈው አይመለስም፣ አይተካም 14
3 ከየትኛውም ንብረት ይበልጥ ውድ ነው 14
ሙስሊም ከጊዜ ጋር በተያያዘ ያለበት ሐላፊነት 17
ጊዜን በአግባቡ ለመጠቀም መንገዶች 17
ጊዜን ገዳዮች 18
ትርፍ ጊዜን መጠቀም 19
ለበጎ ነገር መትጋት 20
ከቀናት ውደት ትምህርት መቅሰም 23
ጊዜን ማደራጀት 24
ሁሉም ጊዜያት የየራሳቸው ስራ አላቸው 27
በላጭ ወቅቶችን ማደን 30
የሙስሊም የየእለት ፕሮግራም 34
ትላንት፣ ዛሬና ነገ 44
ትላንትን የሙጥኝ ያሉ 44
መጭውን ዘመን አምላኪዎች 49
መጭውን ዘመን በጥቁር መነጽር መመልከት 49
ሕልምና ምኞት 54
ዛሬን አፍቃሪዎች 57
ለጊዜ ትክክለኛው እይታ 58
ትላንትን ከስሌት ውስጥ ማስገባት 58
ነገን አሻግሮ ማየት 62
ለዛሬ ተገቢውን ትኩረት መስጠት 64
እድሜ እንዴት ይረዝማል? 67
ዳግም መኖር 74
ጊዜን የሚገድሉ በሽታዎችን መጠንቀቅ 77
ዝ ጉነት 77

በይደር ማቆየት 78
በይደር ማቆየት የሚያስከትለው ጥፋት 79
ጊዜን መስደብ 82

@iqraabookspdf

Scanned by CamScanner

የተርጓሚው ማስታወሻ

በተለምዶ *ጊዜ ወርቅ ነው* ሲባል እንሰማለን። አባባሉ የጊዜን ዋጋ ለማክበድ የተነገረ ቢሆንም አይመጥነውም። ጊዜ ከወርቅ ይበልጣል። ከአልማዝም ከእንቁም ይበልጣል። *ግብዳዊው አሊምና የዳእዎ መሐንዲስ ሊማም ሐሰን አልበንና* እንዳሉት ጊዜ ሕይወት ነው። ሕይወታችን የቀናት ድምር፣ የሰአታት ከምር አይደለምን? መሽቶ በነጋ ቁጥር ሕይወታችን እየተሸረሸረች በመጨረሻ ታልቃለች። ሻማ ቀልጦ ሲያልቅ ብርሃኑ እንደሚጠፋውም የርሷም ብርሃን ይጠፋል። ጊዜን ሊተካ የሚችል ምንም ነገር የለም። ከአድሜያችን አንድ ተጨማሪ ቀን ሊገዛልን የሚችል ምንም ሐብት የለም።

ይህ መጽሐፍ ስለጊዜ ያለንን የተሰመደ አይታ ይቀይራል። ክብደቱን አጽንኦት ሰጥቶ ይተነትናል። የጊዜን ልዩ ባህሪያት ይዘረዝራል። አጠቃቀሙን ያመላክታል። በጊዜ አጠቃቀምና ምልከታ ረገድ በስፋት የሚታዩ ግድፈቶችን ያርማል። የጊዜን ውድነት ተረድተን፣ ከዚህ አኳያ ሕይወታችንን አደራጅተን ለዚህችም ሆነ ለመጭው አለም ስኬት እንድንበቃ ጉልህ አቅጣጫ ያሳየናል።

ደራሲው ይህን ሁሉ ሲያደርጉ ቁርአንንና ሐዲስን መሠረት አድርገው ነው። የሸሪዓ ሊቃውንትን ምክር እና ምግባር ተንተርሰው ነው። ኢስላም ለሁሉም ነገር ማብራሪያ ይሰጣል። ስለ ጊዜ የያዘው መመሪያና ምልከታው ደግሞ በግርምት ያስደምማል።

የመጽሐፉን ደራሲ ማስተዋወቅ አያስፈልገንም። በሸሪዓው የእውቀት መስክ ለግማሽ ምእተ አመታት ያለ ተቀናቃኝ የነገሱ፣ ለአለማችን ባበረከቷቸው ከ160 በላይ ድንቅ የምርምር ስራዎች አንቱ የተሰኙና ብቃታቸውን ያስመሰከሩ የሸሪዓ ሊቃውንት ፈርጥ መሆናቸውን ሁሉም ያውቃልና። በሥራቸው ተጠቃሚዎች ያደርገን ዘንድ አላህን እንለምናለን።

ሐሰን ታጁ
ጥቅምት 2002

መግቢያ

በጎ ስራዎችን በጸጋው ለሚሞላው አምላክ ምስጋና ይድረሰው። የዓለማት እዝነት ተደርገው በተላኩት በመልእክተኛው፣ እንደዚሁም በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ ፈለጋቸውን በተከተሉ ሁሉ ላይ የአላህ እዝነትና ሰላም ይስፈን።

ቀጣዮቹ ገጾች የጊዜን ጸጋ፣ በሙስሊሞች ሕይወት ውስጥ ያለውን ከፍተኛ ዋጋና ከዚህ ጸጋ ጋር በተያያዘ ሙስሊም ያለበትን ሐላፊነት ለማስገንዘብ የጻፍኳትን ማስታወሻ አካተዋል።

ይህችን ማስታወሻ ለመጻፍ ያነሳሳኝ እስልምና በቁርአንና በሱንና ለጊዜ የሰጠውን ከፍተኛ ትኩረት መረዳቴ፣ የመጀመሪያዎቹ ሙስሊሞች ለጊዜ የነበራቸው ይህ ወሰንህ የማይባል ጉጉትና ስስት፣ የኋለኞች ትውልዶች ለገንዘብ ከሚሰጡት የላቀ ዋጋ፣ ውጤቱ እጅግ ጠቃሚ እውቀት፣ የተትረፈረፈ በጎ ስራ፣ የተባረከ ትግል፣ ታላቅ ድል እና ስሩ የጠለቀ፣ ላዩ የዘለቀ ግዙፍ ስልጣኔ ማነጻቸው መሆኑን በጥልቀት በመገንዘቤ፣ በአንጻሩ በአሁኑ ሰአት ሙስሊሞች ጊዜን ያለ አግባብ የሚያባክኑበትንና የሚገድሉበትን ከቂልነትም ያለፈ አሳዛኝ ተግባር እና በዚህ ተግባራቸውም ምክንያት የዓለም መሪነታቸውን ተነጥቀው የዓለም ጅራቶች መሆናቸውን በማስተዋሌ ነው። የአሁኑ ትውልድ አባላት· ለዓለማዊ ሕይወታቸው በመስራት ህይወታቸውን አላሳኩም። ወይም ደግሞ ለመጭው ዓለም በመትጋት መጭውን ሕይወታቸውን አላሳመሩም። በዋል ፈሰስ ሁለቱንም ዓለማት አበላሹ። ሐይማኖታቸውን በትክክል ቢረዱ ኖሮ ለዚህች ዓለም ሁሌም እንደሚኖሩ አድርገው በሰሩ ነበር። ለመጭው ዓለም ነገ እንደሚሞቱ እየተሰማቸው በተጉ ነበር። ተከታዩን የቁርአን ዱዓ መፈክራቸው ባደረጉ ነበር፡-

﴿ رَبَّنَآ ءَاتِنَا فِي ٱلدُّنْيَا حَسَنَةً وَفِي ٱلْآخِرَةِ حَسَنَةً وَقِنَا عَذَابَ ٱلنَّارِ ﴿٢٠١﴾ ﴾

البقرة ٢٠١

"ጌታችን ሆይ! በቅርቢቱ ዓለም መልካም ነገርን በመጪዪቱም ዓለም መልካም ነገርን ለግሠን። ከእሳት ቅጣትም ጠብቀን።" (አል በቀራህ 201)

Scanned by CamScanner

የአስተውሎት ባለቤቶች ከሆኑ ምን አልባትም የጊዜ ሂደት፣ የሌሊትና የቀን መፈራረቅ ያስተምራቸው ይሆናል፡-

﴿ إِنَّ فِي خَلْقِ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ وَٱخْتِلَٰفِ ٱلَّيْلِ وَٱلنَّهَارِ لَءَايَٰتٍ لِّأُو۟لِى ٱلْأَلْبَٰبِ ﴿١٩٠﴾
ٱلَّذِينَ يَذْكُرُونَ ٱللَّهَ قِيَٰمًا وَقُعُودًا وَعَلَىٰ جُنُوبِهِمْ وَيَتَفَكَّرُونَ فِى خَلْقِ ٱلسَّمَٰوَٰتِ
وَٱلْأَرْضِ رَبَّنَا مَا خَلَقْتَ هَٰذَا بَٰطِلًا سُبْحَٰنَكَ فَقِنَا عَذَابَ ٱلنَّارِ ﴿١٩١﴾ رَبَّنَآ إِنَّكَ مَن تُدْخِلِ
ٱلنَّارَ فَقَدْ أَخْزَيْتَهُۥ ۖ وَمَا لِلظَّٰلِمِينَ مِنْ أَنصَارٍ ﴿١٩٢﴾ رَّبَّنَآ إِنَّنَا سَمِعْنَا مُنَادِيًا يُنَادِى
لِلْإِيمَٰنِ أَنْ ءَامِنُوا۟ بِرَبِّكُمْ فَـَٔامَنَّا ۚ رَبَّنَا فَٱغْفِرْ لَنَا ذُنُوبَنَا وَكَفِّرْ عَنَّا سَيِّـَٔاتِنَا وَتَوَفَّنَا مَعَ
ٱلْأَبْرَارِ ﴿١٩٣﴾ رَبَّنَا وَءَاتِنَا مَا وَعَدتَّنَا عَلَىٰ رُسُلِكَ وَلَا تُخْزِنَا يَوْمَ ٱلْقِيَٰمَةِ ۗ إِنَّكَ لَا تُخْلِفُ ٱلْمِيعَادَ
﴿١٩٤﴾ ال عمران: ١٩٠ - ١٩٤

«የሰማያትና የምድር መፈጠር፥ የቀንና የሌሊት መፈራረቅ ለአስተዋዮች ታላላቅ ተአምራት ናቸው - እነርሱ አላህን ቁመውም ተቀምጠውም፥ በጉኖቻቸው ተጋድመውም የሚያወሱት፥ የሰማያትንና የምድርን (ድንቅ) አፈጣጠር የሚያስተነትኑት፥ "ጌታችን ሆይ! ይህን (ድንቅ ዓለም) እንዲሁ (ያለ ዓላማ) አልፈጠርከውም፣ ክብር ላንተ ይሁን። ከእሳት ቅጣት ጠብቀን።" (የሚሉት ናቸው)። "ጌታችን ሆይ! እሳት ያስገባህው በእርግጥም ለውርደት ዳርገህዋል። በደለኞች ረዳቶች የሏቸውም።" "ጌታችን ሆይ! በጌታችሁ እመኑ፥ በማለት ወደ እምነት የሚጠራን ተጣሪ ሰማን። አመንበትም። ጌታችን ሆይ! ኃጢአቶቻችንን ማርልን። ከፋ. ሥራዎቻችንንም አብስልን። ከመል ካም ሰዎች ጋርም ግደለን።" "ጌታችን ሆይ! በመልዕክተኛው አማካይነት የሰጠህውን የተስፋ ቃል ሙላልን። በዕለተ ትንሳኤም አታዋርደን። አንተ ቃልኪዳንን አፍራሽ አይደለህምና።"(አሊ ዒምራን 190-194)

♣ ♣ ♣

ቁርአንና ሱንና ለጊዜ የሰጡት ትኩረት

ቁርአንና ሱንና ለጊዜ በብዙ አቅጣጫዎችና ገጽታዎች ትኩረት ሰጥተውታል። ከነዚህም ውስጥ የመጀመሪያው የጊዜን ዋጋ፣ በርሱ ውስጥ የተካተተውን የአላህ ጸጋ ማብራራታቸው ነው። አላህ ለሰው ልጆች የገለጸውን ጸጋ፣ የዋለውን ውለታ ሲያብራራ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَسَخَّرَ لَكُمُ ٱلشَّمْسَ وَٱلْقَمَرَ دَآئِبَيْنِ ۖ وَسَخَّرَ لَكُمُ ٱلَّيْلَ وَٱلنَّهَارَ ﴿٣٣﴾ وَءَاتَىٰكُم مِّن
كُلِّ مَا سَأَلْتُمُوهُ ۚ وَإِن تَعُدُّوا۟ نِعْمَتَ ٱللَّهِ لَا تُحْصُوهَآ ۗ ﴾ ابراهيم: ٣٣ - ٣٤

«ወሐይንና ጨረቃንም፥ ዘወትር ተጓገቦች አደርጉ፥ ገራላችሁ። ሌትንና ቀንንም ገራላችሁ። (ለሕይወት) የሚያስፈልጋችሁንም ነገሮች ሁሉ ሰጥታችኋል። የአላህን ዐጋዎች ቆጥራችሁ አትዘልቋቸውም።» (ኢብራሂም 33-34)

﴿ وَهُوَ ٱلَّذِى جَعَلَ ٱلَّيْلَ وَٱلنَّهَارَ خِلْفَةً لِّمَنْ أَرَادَ أَن يَذَّكَّرَ أَوْ أَرَادَ شُكُورًا ﴿٦٢﴾ ﴾
الفرقان: ٦٢

«እርሱ ያ፥ (ዐጋውን) ማስታወስ ወይም (እርሱን) ማመስገን ለሚሹ ሁሉ፥ ሌሊትንና ቀንን ተፈራራቂ ያደረገ አምላክ ነው።» (አል ፉርቃን 62)

ማለትም ቀኑ ሌሊቱን፣ ሌሊቱም ቀኑን እንዲተካው አድርጓል። እናም አንዳች ስራ በቀን ያለፈው በሌሊት ያካክሰው፣ በሌሊት ያለፈውም በቀን ያካክሰው።

አላህ የጊዜን የላቀ ዋጋ ለመግለጽ በበርካታ የቁርአን ምእራፎች መግቢያዎች ላይ በርሱ ሲምል እናስተውላለን። ለምሳሌ በቀን፣ በሌሊት፣ በንጋት፣ በረፋድ፣ እና በራሱ በጊዜ ምሏል። የሚከተሉትን የቁርአን አናቅጽ እናስተውል፡-

﴿ وَٱلَّيْلِ إِذَا يَغْشَىٰ ﴿١﴾ وَٱلنَّهَارِ إِذَا تَجَلَّىٰ ﴿٢﴾ ﴾ الليل: ١ - ٢

«በሌሊት እምላለሁ፣ (በዕልመቱ ፍጡራንን) በሸፈነ ጊዜ። በቀንም እምላለሁ፣ በተገለፀ ጊዜ።» (አልለይል 1-2)

Scanned by CamScanner

﴿ وَٱلْفَجْرِ ۝١ وَلَيَالٍ عَشْرٍ ۝٢ ﴾ الفجر: ١ - ٢

«በጉሀ እምላለሁ። በአሥሩ ሌሊቶችም።» (አል ፈጅር 1-2)

﴿ وَٱلضُّحَىٰ ۝١ وَٱلَّيْلِ إِذَا سَجَىٰ ۝٢ ﴾ الضحى: ١ - ٢

«በረፋድ እምላለሁ! በሌሊትም እምላለሁ፣ ጸልመቱ በበረታ ጊዜ።» (አል ዱሐ 1-2)

﴿ وَٱلْعَصْرِ ۝١ إِنَّ ٱلْإِنسَٰنَ لَفِى خُسْرٍ ۝٢ ﴾ العصر: ١ - ٢

«በ"አል-ዐስር" እምላለሁ። የሰው ልጅ ኪሣራ ውስጥ ነው።» (አል ዓስር 1-2)

የቁርአን ተንታኝ ምሁራን እንደሚሉት፣ ሙስሊሞችም እንደሚገነዘቡት አላህ ከፍጡራኑ ባንዱ የሚምለው የሰው ልጆች ለዚያ ነገር ትኩረት እንዲቸሩት ለማስታወስና የላቀ ዋጋውንና ጠቀሜታውን ለማስገንዘብ ነው።

በነቢዩ ሐዲሶችም እንደዚሁ የጊዜን ሩይዳ የሚያብራራ፣ የሰው ልጅ በጊዜ አጠቃቀም ጉዳይ በመጭው ዓለም ከአላህ ዘንድ ቀርቦ እንደሚጠየቅ የሚገልጹ መልእክቶችን እናገኛለን። እያንዳንዱ ሰው በትንሳኤ ቀን ከሚቀርቡለት አራት መሠረታዊ ጥያቄዎች መካከል ሁለቱ ከጊዜ አጠቃቀም ጋር የተያያዙ ናቸው። ሙዓዝ ቢን ጀበል እንዳስተላለፉት ነቢዩ (ሰዐወ) እንዲህ ብለዋል፡

«በእለተ ቂያማ አንድ ሰው አራት ነገሮችን ሳይጠየቅ እግሩ አትንቀሳቀስም። እነርሱም እድሜውን በምን ሁኔታ እንዳሳለፈው፣ ወጣትነቱን በምን እንዳባከነው፣ ገንዘቡን ከየት እንዳገኘውና ለምን እንዳዋለው፣ በእውቀቱ ምን እንደሰራበት ይጠየቃል።» (በዛርና ጠበራኒ)

በዚህ አኳኋን ሰውየው ስለ እድሜው ይጠየቃል። ስለወጣትነቱም እንደገና ይጠየቃል። ወጣትነት የእድሜው አካል ቢሆንም ሐይልና ወኔ የሞላበት፣ በሁለት የደካማነት ጊዜዎች፣ ማለትም በልጅነትና በእርጅና መካከል ያለ ልዩ የሕይወት እርከን በመሆኑ የተለየ ትኩረት ተችሮታል። አላህ እንዲህ ብሏል፡

﴿ ٱللَّهُ ٱلَّذِى خَلَقَكُم مِّن ضَعْفٍ ثُمَّ جَعَلَ مِنۢ بَعْدِ ضَعْفٍ قُوَّةً ثُمَّ جَعَلَ مِنۢ بَعْدِ قُوَّةٍ ضَعْفًا وَشَيْبَةً ۚ يَخْلُقُ مَا يَشَآءُ ۖ وَهُوَ ٱلْعَلِيمُ ٱلْقَدِيرُ ۝٥٤ ﴾ الروم: ٥٤

«አላህ ያ ደካማ አድርጉ የፈጠራችሁ፣ ከደካማነት በኋላም ብርታትን የለገሳችሁ፣ ብርቱ ከሆናችሁ በኋላም ደካሞች ያደረጋችሁና ሽበትን የሰጣችሁ (አምላክ) ነው። የሚሻውን ይፈጥራል። እርሱ (ሁሉን) ዐዋቂ፣ (ሁሉን) ቻይ (አምላክ) ነው።» (አል ሩም 54)

♣ ♣ ♣

Scanned by CamScanner

የእስልምና አምልኮና ስርዓት የጊዜን ዋጋ ያጸናሉ

ኢስላማዊ የአምልኮ (ኢባዳ) ግዴታዎችና ስርዓቶች ይህን ትልቅ ፋይዳ ያጸናሉ። የጊዜን ጥቅም፣ በእያንዳንዱ ቅጽበት መጠቀምን ያስተምራሉ። በሰው ልጅ ሕሊና ውስጥ ለጊዜ ዋጋ የመስጠትን ስሜት ያነቃቃሉ። ከፍጥረተ ዓለሙ እንቅስቃሴ፣ ከኘላኔቶች ዑደት፣ ከጸሐይና ከዋክብት ቅዝፈት፣ ከሌሊትና ከቀን መፈራረቅ ጋር ሁሌም ለጊዜ ዋጋ በመስጠት የማሳሰቢያ ደወል ይደውላሉ።

ሌለቱ ተገባዶ ስፍራውን ለንጋት ሲለቅ አዛን አድራጊው «ሐያ አለሶላህ» (ወደ ሶላት ኑ)፣ «ሐያ አለል ፈላህ» (ወደ ድነት ኑ)፣ «አሶላቱ ኸይሩን ሚነነውም» (ሶላት ከእንቅልፍ ይበልጣል) በሚል ጥሪ አድማሱን በመሙላት አዲሱን ንዑህ ቀን ከአላህ ይቀበሉ ዘንድ የተጙትን ያነቃል። እናም አላህን የሚያስታውሱ አንደበቶች ለጥሪው በጎ ምላሽ ይሰጣሉ። የሰይጣን ቋጠሮዎች ይፈታሉ።[1] አማኞች ፈጥነው ወደ ሶላት ይሄዳሉ።

እኩለ ቀን ላይ፣ ሰዎች በዓለማዊ ጉዳዮች፣ በየእለት ትካሮች ውስጥ በሰጠሙበት ወቅት አዛን አድራጊው ለሁለተኛ ጊዜ ድምጹን ያሰማል። «አላሁ አክበር» (አላህ ከሁሉም የላቀ ነው) «ላኢላሐ ኢለላህ» (ከአላህ ሌላ አምላክ የለም) ሲል የአላህን አንድነት ያውጃል። የነቢዩን መልእክተኛነትም ይመሰክራል። ወደ ስግደትና ድነት ይጠራል። በዚህ ጊዜ ሰዎች ከተለመደ ስራቸውና ሕይወታቸው ወጥተው ከፈጣሪያቸው፣ ከሲሳይ ለጋሻቸው፣ ከጉዳያቸው ባለቤት ፊት ለተወሰኑ ደቂቃዎች በመቆም የዓለማዊ ሕይወት ግብግብና የዱንያ ፍለጋ ድካማቸውን ያቃልላሉ። ይህ የሚሆነው በእኩለ ቀን ማለትም በዙሀር ሶላት ወቅት ነው።

መሸትሸት ሲል፣ ጸሐይ መጥለቀያዋ ሲቃረብ አዛን አድራጊው ለአስር ሶላት ሦስተኛ ጥሪ ያሰማል። ጸሐይ ከአድማሱ ስትሰወር፣

[1] ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- «ከናንተ አንዳችሁ በሚተኛ ጊዜ ሰይጣን ከራሱ ላይ ሦስት ቋጠሮዎችን ይቋጥራል...።» የሐዲሱን ሙሉ መልእክት ስለ ሙስሊም የቀን ውሎ ስናወሳ እንዘከረዋለን።

በቀኑ ማጠናቀቂያና በሌሊቱ መጀመሪያ ሰአት አዛን አድራጊው ለመግሪብ አራተኛ ጥሪ ያሰማል።

ምሽት ላይ የሙስሊም የቀን ውሎው መጠናቀቂያ ለሆነው የኢሻእ ሶላት የአዛን ጥሪ ይደመጣል። ሙስሊም በዚህ አኳኋን ቀኑን በሶላት ይጀምራል። በሶላትም ያጠናቅቃል። በሁለቱ ሶላቶች በፈጅርና በኢሻእ መካከል ከአላህ ጋር ያለው ግንኙነት ለአፍታም አይቋረጥም።

በየሳምንቱ የጁሙዓ ቀን የተለየ ባህሪ ላለው ሳምንታዊ ሶላት አዛን አድራጊው ጥሪ ያሰማል። ከነዚህ የግዴታ ሶላቶች በተጨማሪ የሌሊት ሶላት ይገኛል። ለአላህ ሲሰግዱ የሚያድሩት ባሮቹ ነቅተው ያከናውኑታል። የዱሐና ሌሎች ሱንና ሶላቶችም ይገኛሉ።

የየወራቱ ጨረቃ ሲወጣ ሙስሊም አላህን በማስታወስ ወሩን ይቀበላል። እንዲህ ሲልም ያወድሰዋል፡-

«አላህ ከሁሉም የላቀ ነው። አላህ ከሁሉም የላቀ ነው። አላህ ከሁሉም የላቀ ነው። ለፊጠረህ፣ መኖሪያህን ለመጠነልህ፣ ለዓለማት ምልኩት ላደረገህ አላህ ምስጋና ይድረሰው። አላህ ሆይ፣ የሰላም፣ የጤንነትና የየጽናት ወር አድርግልን። አንተ የምትወደውን ለመስራትም ግጠመን። አንች ጨረቃ ሆይ፣ የኔም ያንችም አምላክ አላህ ነው።»

በየዓመቱ በረመዳን ወር የጀነት በሮች ሲከፈቱና የጀሃነም በሮች ሲዘጉ፣ ሰይጣናት ሲታሰሩ፣ ከምድር ላይሆን ከሰማይ አንድ ተጣሪ እንዲህ ሲል ይጣራል፡-

«በጎ ነገር ፈላጊው ሆይ፣ ና። ክፉ ነገር ከጃይ ሆይ፣ ተቆጠብ።»

በዚህ ጊዜ ወንጀለኛው ይቶብታል። የዘነጋው ይነቃል። የሸሸ ወደ አላህ መስክ ይመለሳል። ውዴታውን ሽተው ምህረቱን ከጅለው ይጸማሉ። ይሰግዳሉ። የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ሲሉ ቃል ገብተዋል፡-

«ረመዳንን በጽኑ እምነትና ከአላህ ምንዳ በመሻት የጸመ ያለፈ ወንጀሉ ይማርለታል። ረመዳንን በጽኑ እምነትና ከአላህ ምንዳ ከጅሎ የቆመ (የሰገደ) ያለፈ ወንጀሉ ይማርለታል።»

Scanned by CamScanner

በረመዳን ከሚደረገው ከዚህ መንፈሳዊ ሕይወት በተጨማሪ የመንፈስም የአካልም ቅኝት የሚያደርግበት ሌላ ወር ይመጣል። እርሱም የሐጅ ወር ነው። የሐጅ ወራት የረመዳን ወር እንደተጠናቀቀ ይጀምራሉ።

﴿ ٱلْحَجُّ أَشْهُرٌ مَّعْلُومَٰتٌ ۚ فَمَن فَرَضَ فِيهِنَّ ٱلْحَجَّ فَلَا رَفَثَ وَلَا فُسُوقَ وَلَا جِدَالَ فِى ٱلْحَجِّ ۗ وَمَا تَفْعَلُوا۟ مِنْ خَيْرٍ يَعْلَمْهُ ٱللَّهُ ۗ وَتَزَوَّدُوا۟ فَإِنَّ خَيْرَ ٱلزَّادِ ٱلتَّقْوَىٰ ۚ وَٱتَّقُونِ يَٰٓأُو۟لِى ٱلْأَلْبَٰبِ ﴿١٩٧﴾ ﴾ البقرة: ١٩٧

«የሐጅ (ጊዜ) የታወቁ ወራት ናቸው። በነኝህ (ወራት) ውስጥ ሐጅን በራሱ ላይ ግዳጅ ያደረገ ሐጅ ውስጥ ከሴት ጋር መገናኘት፣ (በአላህ ላይ) ማመጽም፣ (ከባልደረቦቹ) ጋር መከራከርም የለበትም። ከበጉ ምግባር የምትፈጽሙትን አላህ ያውቃል። ተሰነቁ። ከሰንቅ ሁሉ በላጩ አላህን መፍራት ነው። እናንተ አስተዋዮች ሆይ! ፍሩኝ።» (አል በቀራህ 197)

አንድ ቀደምት ሙስሊም(ሰለፍ) የየእለት ሶላታችንን «የቀን ሚዛን»፣ የጁሙዓን ሶላት «ሳምንታዊ ሚዛን»፣ ረመዳንን «ዓመታዊ ሚዛን»፣ ሐጅን ደግሞ «የእድሜ ሚዛን» በማለት ጠርተውታል። ይህውም አንድ ሙስሊም ቀኑን ስኬታማ ለማድረግ እንዲጥር፣ ከዚያም ሳምንቱን ለማሳመር እንዲተጋ፣ ቀጥሎም ዓመቱን ብሎም እድሜውን ሙሉ ጥሩ ለማድረግ እንዲሰራ ለማስታወስ ነው። ጥሩ ፍጻሜ ይህ ነው።
ከዚህ በተጓዳኝ የዘካ ግዴታ ይኸል። በየዓመቱና በየመሀር ወቅቱ ግዴታ ይሆናል፡

﴿ وَءَاتُوا۟ حَقَّهُۥ يَوْمَ حَصَادِهِۦ ۖ ﴾ الأنعام: ١٤١

«የታጨዱ ዕለትም (ለድሆች) ድርሻቸውን ስጡ።» (አል አንዓም 141)
በዚህ መልኩ ሙስሊም ዘካን በወቅቱ ጊዜውን ሳያሳልፍ ለመክፈል፣ ኢባዳውን በሰአቱ ለማከናወን ሲል ሰጊዜ ዑደትና እንቅስቃሴ ምንጊዜም ትኩረት ሰጥቶ ይኖራል።

♦ ♦ ♦

የጊዜ ልዩ ባህሪያት

ጊዜ ልዩ ባህሪያት አሉት። እነዚህን ባህሪያት በግወት ከባህራው አኳያ መጠቀም ተገቢ ይሆናል።

1 በፍጥነት መጓዙ

ጊዜ በፍጥነት ያልፋል። በትጽበት ይሸልካል። የደስታም ሆነ የሐዘን ጊዜ ቶሎ አላፊ ነው። በእርግጥ በሰዎች ስሜት ውስጥ ደስታ ፈጥኖ የሚያልፍ፣ ሐዘንና መከራ ደግሞ የሚዘገይ ቢመስልም።

የሰው ልጅ የዚህች አለም እድሜ ያሻውን ያህል ቢረዝምም አጭር ነው። ምክንያቱም ፍጻሜው ምንጊዜም ሞት ነውና። በሞት ጊዜ ሰውየው በመጫወት ያሳለፋቸው አመታት ተጠቅልለው፣ ዘመናቱ አጥረው እና ሚሽው ትጽበት ይመስላሉ።

ከነብያት አባት ከኑህ ጋር በተያያዘ የሚወጋ ታሪክ አለ። 1000 ዓመታት በሕይወት ከቆዩ በኋላ የሞት መላእክ በመጣባቸው ጊዜ፣ «ከሁሉም ነብያት የረዘመ እድሜ ተሰጥቶሐል። ይህችን ዓለም እንዴት አገኘሃት?» በማለት ጠየቃቸው። «ሁለት በሮች እንዳሉት ቤት ሆና አገኘኋት። በአንዱ ገብቼ በሌላኛው እንደወጣሁ ነው የተሰማኝ» አሉ።

ይህ ታሪክ እውነትም ይሁን አይሁን አንድን የማያከራክር እውነት ያጸድቃል። ይህውም በሞት ጊዜ እድሜ እንደሚጫሽ። በቂያማ ቀንም እንደዚሁ ነው። የሰው ልጅ ዓለማዊ ሕይወቱን አጭርና ቅጽበታዊ አድርጎ ይመለከታል። አላህ እንዲህ ብሏል፡

﴿ كَأَنَّهُمْ يَوْمَ يَرَوْنَهَا لَمْ يَلْبَثُوٓا۟ إِلَّا عَشِيَّةً أَوْ ضُحَىٰهَا ﴿٤٦﴾ ﴾ النازعات: ٤٦

«እነርሱ (ኪሳዲያን) (ትንሣኤን) በሚመለከቷት ቀን (ከዚህች ዓለም ውስጥ) አንድ ምሽት ወይም አንድ ረፋድ ብቻ የቆዩ ያህል ይሰማቸዋል።» (አል ናዚለት 46)

﴿ وَيَوْمَ يَحْشُرُهُمْ كَأَن لَّمْ يَلْبَثُوٓا۟ إِلَّا سَاعَةً مِّنَ ٱلنَّهَارِ يَتَعَارَفُونَ بَيْنَهُمْ ﴾ يونس: ٤٥

Scanned by CamScanner

«በሚያሰባስባቸው ቀን፡ (በዚህች ዓለም) ከቀን ውስጥ የተወሰነ ሰዓት ብቻ የኖሩ ያህል ይሰማቸዋል። እርስ በርስ ይተዋወቃሉም።» (ዩኑስ 45)

2 ያለፈው አይመለስም፣ አይተካም

ይህ ሌላው የጊዜ ባህሪ ነው። እያንዳንዱ የሚያልፍ ቀን፣ እያንዳንዷ የምታልፍ ሰአት እና ቅጽበት ልትመለስ አትችልም። ስለሆነም ማካካሻ ምትክ የላትም። ይህም በመሆኑ ሐሰን አል በስሪ እንዲህ ብለዋል፡-

እያንዳንዱ ቀን፡- «የአደም ልጅ ሆይ፣ እኔ አዲስ ፍጡር፣ ለስራህም መስካሪ ነኝ። ከኔ ተሰነቅ። ካለፍኩ እስከ እለተ ቂያማ አልመለስም፣ ይላል።»

አንዳንድ ሰዎች ይህችን ንግግር የነቢዩ ቃል አድርገው መውሰዳቸው ስህተት ነው። በእርግጥ የሐሰነል በስሪ ንግግር ነው። ዘይኑል ዓቢዲን ስለርሳቸው ሲናገሩ፡- «ይህ ሰው ንግግሩ የነብያትን ንግግር ይመስላል።» ብለዋል።

ጊዜ ካመለጠ አይያዝም። ሰዎች ከእርጅና በኋላ ወጣትነትን ይመኛሉ። ግና ምኞት ብቻ ይሆናል። የሚፈይደው ነገር የለም።

3 ከየትኛውም ንብረት ይበልጥ ውድ ነው

ጊዜ በፍጥነት የሚያልፍ፣ ካመለጠ የማይያዝ እና የማይተካ ከመሆኑ አንጻር የሰው ልጅ ከሚኖሩት ሐብቶች ሁሉ ውድ ዋጋ ያለው እርሱ ነው። ጊዜን ይበልጥ ውድ የሚያደርገው የየትኛውም ተግባርና ምርት መሠረት በመሆኑ ነው። የግለሰብም ሆነ የማሕበረሰብ እውነተኛ ጥሪት እርሱ ነው።

ጊዜ በተለምዶ እንደሚነገረው ወርቅ ብቻ አይደለም። ከወርቅም፣ ከአልማዝም፣ ከየትኛውም የከበረ ድንጋይ በላይ ነው። ሸሂድ ኢማም ሐሰን አልበንና እንዳሉት «ጊዜ ሕይወት ነው።» የሰው ልጅ ሕይወት ከተወለደ አንስቶ እስኪሞት ድረስ የሚተነፍሳት እስትንፋሱ እንጅ ሌላ አይደለችምና።

ኢማም ሐሰን አልበስሪ ይህን አስመልክተው ሲናገሩ፡-

«የሰው ልጅ ሆይ፣ አንተ የቀናት ጥርቅም ነህ። እያንዳንዱ ቀን በሄደ ቁጥር ከፊል ማንነትህ አብሮ ይሄዳል።»

የጊዜን ዋጋ አሁን ያላወቀ ይህን የሚያውቅበት ጊዜ ወደፊት ይመጣል። ግና ያኔ ካመለጠ በኋላ ይሆንና ፋይዳ አይኖረውም። የሰው ልጅ ባሳለፈው ጊዜ የሚቆጭባቸው ሁለት አጋጣሚዎች በቁርአን ተወስተዋል፡-

አንደኛ፡ ጣእረ ሞት ላይ፣ ይህችን ዓለም ሊሰናበትና መጭውን ዓለም ሊቀበል ጥቂት ጊዜያት ብቻ ሲቀሩት ያበላሸውን ያስተካክል፣ ያሳለፈውን ይይዝ ዘንድ ጥቂት ጊዜ እንኳ ቢሰጠው ይመኛል። ቁርአን ይህን በማስመልከት ሲናገር፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ لَا تُلْهِكُمْ أَمْوَٰلُكُمْ وَلَآ أَوْلَٰدُكُمْ عَن ذِكْرِ ٱللَّهِ ۚ وَمَن يَفْعَلْ ذَٰلِكَ فَأُو۟لَٰٓئِكَ هُمُ ٱلْخَٰسِرُونَ ﴿٩﴾ وَأَنفِقُوا۟ مِن مَّا رَزَقْنَٰكُم مِّن قَبْلِ أَن يَأْتِىَ أَحَدَكُمُ ٱلْمَوْتُ فَيَقُولَ رَبِّ لَوْلَآ أَخَّرْتَنِىٓ إِلَىٰٓ أَجَلٍ قَرِيبٍ فَأَصَّدَّقَ وَأَكُن مِّنَ ٱلصَّٰلِحِينَ ﴿١٠﴾ ﴾

المنافقون: ٩ - ١٠

«እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ገንዘቦቻችሁም ልጆቻችሁም አላህን ከማስታወስ አያዘናጓችሁ። ይህንን የሚፈጽሙ (በገንዘቦቻቸውና በልጆቻቸው ሳቢያ አላህን ከማስታወስ የሚዘናጉ ሰዎች) እነዚያ እነርሱ ከሚሪዎች ናቸው። ከናንተ አንዳችሁ ሞት መጥቶበት፡- ጌታዬ ሆይ! እመዐውት ዘንድ፡ ከደጋጉች ሰዎች እሆንም ዘንድ ለጥቂት ጊዜ ብታቆየኝ እመኛለሁ፡ ከማለቱ በፊት ከሰጠናችሁ ሲሳይ ለግሱ።» (አል ሙናፊቁን 9-10)

ለዚህ ባዶ ምኞት የሚሰጠው ምላሽ ቁርጥ ያለ ነው፡-

﴿ وَلَن يُؤَخِّرَ ٱللَّهُ نَفْسًا إِذَا جَآءَ أَجَلُهَا ۚ وَٱللَّهُ خَبِيرٌۢ بِمَا تَعْمَلُونَ ﴿١١﴾ ﴾ المنافقون: ١١

«አላህ አንዲትን ነፍስ (የሞት) ቀጠሮዋ በደረሰ ጊዜ (ለቅጽበት ያህል እንኳ) ፈፅሞ አያቆያትም። አላህ የምትሠሩትን ሁሉ ወዋቂ ነው።» (አል መናፊቁን 11)

ሁለተኛ፡ በመጭው ዓለምም ይቆጫል። ነፍስ ሁሉ የስራዋን ስታጣኝ፣ የጀነት ሰዎች ወደ ጀነት የእሳት ሰዎች ወደ እሳት ሲገቡ።

Scanned by CamScanner

በዚህ ቅጽበት የእሳት ሰዎች ወደ ዱንያ ሕይወት በመላክ፣ ዳግም እድል ቢሰጣቸው እንደ አዲስ ለመጀመር፣ በጎም ለመስራት ይመኛሉ። ግና ያሰቡት አይሳካም። የተመኙት አይሆንም። ምክንያቱም የስራ ጊዜ አክትሞ፣ የውጤት መቀበያ ጊዜ መጥቷል። በወቀሳ አዘል ምላሽ ምኞታቸው ከንቱ መሆኑ ይገለጽላቸዋል። መልስ አይኖራቸውም። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ وَٱلَّذِينَ كَفَرُواْ لَهُمْ نَارُ جَهَنَّمَ لَا يُقْضَىٰ عَلَيْهِمْ فَيَمُوتُواْ وَلَا يُخَفَّفُ عَنْهُم مِّنْ عَذَابِهَا كَذَٰلِكَ نَجْزِي كُلَّ كَفُورٍ ﴿٣٦﴾ وَهُمْ يَصْطَرِخُونَ فِيهَا رَبَّنَآ أَخْرِجْنَا نَعْمَلْ صَٰلِحًا غَيْرَ ٱلَّذِي كُنَّا نَعْمَلُ ۚ أَوَلَمْ نُعَمِّرْكُم مَّا يَتَذَكَّرُ فِيهِ مَن تَذَكَّرَ وَجَآءَكُمُ ٱلنَّذِيرُ ۖ فَذُوقُواْ فَمَا لِلظَّٰلِمِينَ مِن نَّصِيرٍ ﴿٣٧﴾ ﴾ فاطر: ٣٦ - ٣٧

«እነዚያ የካዱትንም የገሃነም እሳት ይጠብቃቸዋል። ይሞቱ ዘንድ (ሞት) አይፈረድባቸውም። ቅጣቱም አይቃለልላቸውም። ከሓዲያንን ሁሉ በዚህ አኳኋን እንቀጣለን። "ጌታችን ሆይ! (ከእሳት) አውጣን። (ከአሁን በፊት) እንሠራው ከነበረው (እኩይ ምግባር) የተለየ መልካም ሥራ እንሠራለን።" በማለት (የእርዳታ) ጩኸት ያሰማሉ። (የሚሰጣቸው ምላሽ) "መገሰጥ የሚሻ ሁሉ ሊገሰጥ የሚችልበትን ያህል ዕድሜ አልሰጠናችሁምን? (በተጨማሪም) የሚያስጠነቅቁ (መልዕክተኞች) መጡላችሁ። (ይህ ሁሉ ሆኖ ግን አላመናችሁም)። ስለዚህም (ቅጣቴን) ቅመሱ። በዳዮች ረዳት የላቸውም።" (የሚል ይሆናል)።»(ፋጢር 36-37)

አላህ ለእያንዳንዱ ሰው ሐላፊነቱን በአግባቡ መወጣት፣ ሲዘነጋ ማስታወስ የሚያስችለው እድሜ በመስጠት ምክንያት አልባ አድርጎታል። በተለይም 60 ዓመታት እስኪሞላው ድረስ የቆየ ሰው ምክንያት የለውም። የዘነጋ እንዲያስታውስ፣ ያመጸ እንዲመለስ፣ ወንጀለኛ እንዲቆጠብ ይህ የእድሜ ደረጃ በቂ አስታዋሽ ነው። በሶሂህ የሐዲስ ዘገባ የሚከተለው ተወስቷል፡-

«አላህ የሰውን ልጅ 60 ዓመታት በመስጠት ምክንያት አልባ አድርጎታል።» (ቡኻሪ)

♣ ♣ ♣

ሙስሊም ከጊዜ ጋር በተያያዘ ያለበት ሐላፊነት

ጊዜ ይህን ያህል ትኩረት የሚቸረው፣ ዋጋውም ሕይወትን የሚመጥን ከሆነ ሙስሊም ግለሰብ ጊዜውን በተመለከተ በርካታ ግዴታዎች ይኖሩበታል። እነዚህን ግዴታዎች መጀመሪያ ግወቅ፣ በነርሱ በጥልቅ ግመንና ወደ ተግባር መለወጥ ይጠበቅበታል። እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፡-

ጊዜን በአግባቡ ለመጠቀም መጓጓት

የመጀመሪያው ግዴታው ለጊዜው ልከ እንደጎንዘቡ ወይም ከዚያ በላይ መሳሳትና ጊዜውን ሙሉ በሙሉ ለዚህች ወይም ለመጭው ዓለም ሕይወቱ እንደዚሁም ለማሕበረሰቡ ደስታና ብልጽግና ሊያስገኝ በሚችል ተግባር ላይ መትጋት ነው። ቀደምት ሙስሊሞች (ሰለፍ) ለጊዜ ከፍተኛ ዋጋ ይሰጣሉ። ይሳሱለታልም። ምክንያቱም ከምንም በላይ የላቀ ዋጋ እንዳለው ይገነዘቡ ነበርና። ሐሰን አል በስሪ እንዲህ ብለዋል፡-

«እናንተ ለገንዘባችሁ ከምትሳሱት የበለጠ ለጊዜ የሚሳሱ ሰዎችን አግኝቻለሁ።»

እናም ጊዜያቸውን በጠቃሚ ስራ ላይ ለማዋል፣ ከርሱ ትንሣት ታክል እንኳ እንዳይባክን ለማድረግ ተግተው ይሰሩ ነበር። ዑመር ቢን አብድል አዚዝ እንዲህ ብለዋል፡-

«ሌሊትና ቀን ባንተ ላይ ይሰራሉ። አንተም በነርሰ ላይ ስራባቸው።»

ሰለፎች እንዲህም ይሉ ነበር፡-

«ጊዜን ማባከን የመረገም ምልክት ነው።»

«ጊዜ ሰይፍ ነው። ካልቆረጥከው ይቆርጥሐል።»

ሁሌም ወደተሻለ ደረጃ ለማደግ ይጥሩ ነበር። ከትላንት ዛሬ፣ ከዛሬነገ የተሻለ ይሆን ዘንድ ይሰሩ ነበር። አንድ ሰለፍ እንዲህ ብለዋል፡-

«ዛሬው እንደ ትላንቱ የሆነ ከሳሪ ነው። ከትላንቱ የዛሬው የከፋ ደግሞ የተረገመ ነው።»

Scanned by CamScanner

ጠቃሚ እውቀት ሳይሸምቱባት፣ በጎ ስራ ሳይሰሩባት፣ ወገንን ሳይጠቅሙባት አንዲት ቅጽበት እንኳ እንድታልጥና እድሚያቸው ሳያውቁት እንዲባክን አይፈልጉም ነበር።

አንድ ሰው በቀን ውስጥ ለራሱ ወይም በዙሪያው ላሉ ሕያውያን የእውቀት፣ የእምነት ወይም የበጎ ስራ ምርት ሳይጨምር እንዲሁ ማሳለፉን በአላህ ጸጋ ከመካድ (ከኩፍሩ ኒዕማ) ይቆጥሩት ነበር።

ኢብን መስዑድ እንዲህ ብለዋል፦

«ሕድሜዬ አንሶ በጎ ስራዬ ሳይጨምር ጸሐይ ከምትጠልቅበት ቀን የበለጠ የሚያስቆጨኝ ምንም ነገር የለም።»

ሌላኛው ሰለፍ እንዲህ ብለዋል፦

«ወደ አላህ የሚያቀርበኝ እውቀት ሳልጨምርበት የሚያመልጠኝ ቀን ሁሉ የዚያን ቀን ጸሐይ መውጣቷ ለኔ በረከታማ አይደለም።»

አንዳንድ ሰዎች ይህ የነቢዩ ንግግር ነው ያሉ ሲሆን ኢማም ቢን አልቀይም «ሚፍታሁ ሰአዳህ) በተሰኘ መጽሐፋቸው ትክክል እንዳልሆነ ገልጸው ከሶሐባ ወይም ከታቢኢ መገኘቱ በቂው ነው ብለዋል።

ሐኪም እንዲህ ብልዋል፦

«ከእድሜው አንድ ቀን እንኳ ግዴታውን ሳይወጣበት፣ መብት ሳያደርስበት፣ ክብር ሳያገኝበት፣ በጎ ሳይጨመርበት ወይም እውቀት ሳይቀስምበት ያሳለፈ ራሱን በድሏል።»

ጊዜን ገዳዮች

ሰለፎቻችን ለጊዜ የነበራቸው ጉጉትና የሚሰጡት ዋጋ ይህ ሆኖ ሳለ በአሁኑ ሰአት በሙስሊሞች ዘንድ የምናየው ጊዜን የማባከንና የመግደል ድርጊት እጅግ ያሳዝናል።

ጊዜን ማባከን ገንዘብን ከማባከን የበለጠ ቂልነት ነው። አባካኝ ጊዜ ካመለጠ ግን ዳግም አይገኝም።

«ጊዜን መግደል» የሚሉት ብሂል በማሕበረሰቡ ውስጥ ተስፋፍቷል። ጊዜ አባካኞች ካርታ፣ ዳማ ወይም ሌላ ሐላል ወይም ሐራም ነገር እየተጫወቱ ረዥም ሰአት ያሳልፋሉ። ይውላሉ። ያመሻሉ። በዚህ ጊዜ ውስጥ አላህን አያስታውሱም። ስለሶላት ደንታ የላቸውም። ዲናዊና ዱንያዊ ግዴታቸውንም አይወጡም። ለምን ይህን እንደሚያደርጉ ስትጠይቃቸው «ጊዜን መግደል ስለፈለግን ነው» በማለት ያለ ሐፍረት ይነግሩሐል። ጊዜውን የገደለ ራሱን እንደገደለ መሆኑን እነዚህ ሚስኪኖች አላወቁም። ሰዎች እያዩና እየሰሙ ባደባባይ የሚፈጸም ሂደታዊ ራስን የማጥፋት ድርጊት ነው። ግና ባለቤቱ በወንጀል አይጠየቅም። ለራሱም እንኳ ባልታወቀው ጥፋት እንዴት ይጠየቃል?

ትርፍ ጊዜን መጠቀም

ሰዎች የማያውቁትና እንዲሁ እንደ ቀላል የሚያዩት ትርፍ ጊዜን የመጠቀም ነገር ነው። ቡኻሪ ኢብን አባስን በመጥቀስ እንደዘገቡት ነቢዩ (ሰዐወ) እንዲህ ብለዋል፦

«በሁለት የአላህ ጸጋዎች ሰዎች ሁሉ ይከስራሉ። (በእግባቡ አይጠቀሙባቸውም)። እነርሱም ጤንነትና ትርፍ ጊዜ ናቸው።»

ትርፍ ጊዜ የሚባሉት ለመጭው ዓለም ለመስራት እንቅፋት ከሚሆኑ ዓለማዊ ስራዎች ነጻ መሆን ነው። የመጭውን ዓለም ስራ በማያዘናጋ መልኩ ለዚህች ዓለም መስራት ከእስልምና አስተምህሮት ጋር አይጋጭም።

«መክሰር» የሚለው ቃል በመሠረቱ ከንግድ ጋር የተያያዘ ነው። ሐዲሱ ግለሰብን በነጋዴ፣ መስሎታል። ጤንነትንና ትርፍ ጊዜን ደግሞ በራስ ማል መስሏቸዋል። ምክንያቱም የትርፍ ሰበቦች ናቸውና። ከአላህ ጋር ትእዛዙን በመፈጸም የተገበያየ አተረፈ። ከሰይጣን ጋር እርሱን በመከተል የተገበያየ ከሰረ።»

በሌላ ሐዲስ «ከአምስት ነገሮች በፊት አምስት ነገሮችን ተጠቀም» በማለት ተዘርዝረዋል። ከነርሱ መካከል እንዱ፦ «ትርፍ ጊዜህን በስራ ከመጠመድህ በፊት ተጠቀምበት» የሚል ይገኛል።

Scanned by CamScanner

ትርፍ ጊዜ ሁሌም እንዲሁ አይቀርም። በበጎ ወይም በክፉ ነገር መሞላቱ አይቀሬ ነው። ራሱን በሐቅ ያልጠመደ፣ ነፍሱ በከንቱ ነገር ትጠምደዋለች። እናም ትርፍ ጊዜውን በበጎ ነገር የሞላው ሰው ምንኛ አማረለት። በክፉ ነገር የሞላው ደግሞ ምንኛ ከሰረ።

አንድ በጎ ሰው እንዲህ ብለዋል፦

«ትርፍ ጊዜ ትልቅ ጸጋ ነው። ይህን ጸጋ ያባከነ በራሱ ላይ የከንቱ ስሜት በር ከፍቷል። ስጋዊ ፍላጎቱን ተከትሏል። አላህ የቀልቡን ጸጋ ነፍጎታል። እድሉን አደፍርሶበታል።»

አንድ ሌላ ሰው እንዲህ ብለዋል፦

«ነጻ ጊዜ አግኝተህና እንቅፋቶች ሁሉ ተነስተውልህ ወደ አላህ አለመጓዝህ ትልቅ ውርደትና ኪሣራ ነው።»

አንድ ሰው ያለ ስራ እንዲሁ መቀመጡን ሰለፎች አጥብቀው ይጠሉ ነበር። ዱንያዊ ወይም ዲናዊ ስራ ሳይኖር እንዲሁ መቀመጥ ይወገዛል። ነጻ ጊዜ በአግባቡ ካልተጠቀሙበት ይጎዳል። ይህም በመሆኑ፦ «ትርፍ ጊዜ ወንዶችን ያደንዛል። የሴቶችን እንስታዊ ስሜት ይቀሰቅሳል።» ተብሏል።

የዩሱፍ አሳዳሪ የነበረችው እንስት በርሱ ፍላጎት እንድትጠመድ ያደረጋት ነጻ ጊዜ ማግኘቷ አይደለምን? በተለይም የገንዘብ አቅም ያለው ወጣት፣ ካለው ሙቀት፣ ጉልበትና ስሜት ጋር ነጻ ጊዜ ሲያገኝ አደገኛ ይሆናል።

ለበጎ ነገር መትጋት

የጊዜን ዋጋ የተገነዘበ ሙእሚን በበጎ ስራ ሊያደምቀው ተገቢ ይሆናል። እየተሰላቹና እየታከቱ ወደ በጎ ስራ መሄድ ወይም ከፊሉን ሰርቶ ከፊሉን በይደር ማስተላለፍ ወይም በስንፍና ምክንያት ሌላ ጊዜ እሰራዋለሁ እያሉ መቅጠር ፍጹም መኖር የሌለበት ባህሪ ነው።

የአላህ መልእክተኛ ለተከታዮቻቸው ካስተማሯቸው ዱዓዎች መካከል የሚከተለው ይገኝበታል፦

«አላህ ሆይ፣ ከሐሳብእና ከሐዘን፣ ከስንፍናና ከመታከት ባንተ እጠበቃለሁ።»

ይህም በመሆኑ ቁርአን ለበጎ ነገር መሽቀዳደምን አጥብቆ ያዛል። እንቅፋት ሳይመጣ፣ አቋራጭ ሳይከሰት፣ በሌላ ነገር ሳትጠመዱ በፊት በጎ ነገር ስሩ ይላል፦

﴿ وَلِكُلٍّ وِجْهَةٌ هُوَ مُوَلِّيهَا ۖ فَاسْتَبِقُوا الْخَيْرَاتِ ۚ أَيْنَ مَا تَكُونُوا يَأْتِ بِكُمُ اللَّهُ جَمِيعًا ۚ إِنَّ اللَّهَ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ ﴿١٤٨﴾ ﴾ البقرة: ١٤٨

«የትኛውም (ሕዝብ) የስግደት አቅጣጫ አለው -(ቂብላህ)፣ ወደ መልካም ሥራዎች ተሽቀዳደሙ። የትም ብትሆኑ አላህ ይሰበስባችኋል። አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነውና።» (አል በቀራህ 148)

﴿ وَلَوْ شَاءَ اللَّهُ لَجَعَلَكُمْ أُمَّةً وَاحِدَةً وَلَٰكِن لِّيَبْلُوَكُمْ فِي مَا آتَاكُمْ ۖ فَاسْتَبِقُوا الْخَيْرَاتِ ۚ إِلَى اللَّهِ مَرْجِعُكُمْ جَمِيعًا فَيُنَبِّئُكُم بِمَا كُنتُمْ فِيهِ تَخْتَلِفُونَ ﴿٤٨﴾ ﴾ المائدة: ٤٨

«አላህ ቢሻ ኖሮ (ተመሳሳይ ፍኖት የሚከተል) አንድ ሕዝብ ባደረጋችሁ ነበር። ግና በሰጣችሁ ነገር ሊፈትናችሁ (የተለያዩ መንገዶችን አደረገ)። ለመልካም ሥራም ተሽቀዳዳሙ። ሁላችሁም መመለሻችሁ ወደ አላህ ነው። ከዚያም ትወዛ ገቡበት የነበረውን ነገር ይነግራችኋል።» (አል ማኢዳህ 48)

﴿ وَسَارِعُوا إِلَىٰ مَغْفِرَةٍ مِّن رَّبِّكُمْ وَجَنَّةٍ عَرْضُهَا السَّمَاوَاتُ وَالْأَرْضُ أُعِدَّتْ لِلْمُتَّقِينَ ﴿١٣٣﴾ ﴾ آل عمران: ١٣٣

«የጌታችሁን ምሕረት ለመጉናዐፍና ስፋቷ የሰማያትንና የምድርን ስፋት የሚመጥነውን ገነት ለመውረስ ተቻኮሉ። አላህን ለሚፈሩ ሰዎች ተዘጋጅታለች።» (አሊ ዒምራን 133)

﴿ سَابِقُوا إِلَىٰ مَغْفِرَةٍ مِّن رَّبِّكُمْ وَجَنَّةٍ عَرْضُهَا كَعَرْضِ السَّمَاءِ وَالْأَرْضِ أُعِدَّتْ لِلَّذِينَ آمَنُوا بِاللَّهِ وَرُسُلِهِ ۚ ذَٰلِكَ فَضْلُ اللَّهِ يُؤْتِيهِ مَن يَشَاءُ ۚ وَاللَّهُ ذُو الْفَضْلِ الْعَظِيمِ ﴿٢١﴾ ﴾ الحديد: ٢١

«የጌታችሁን ምሕረትና ስፋቷ እንደ ሰማይና ምድር ስፋት የሆነውን ገነት ለመጉናዐፍ ተሽቀዳደሙ። ለነዚያ በአላህና በመልዕክተኛው ላመኑት ተዘጋጅታለች። ይህ የአላህ ችሮታ ነው። ለፈለገው ይቸረዋል። አላህ የታላቅ ችሮታ ባለቤት ነውና።» (አል ሐዲድ 21)

የአላህን ምህረትና ጀነትን ለማግኘት በሚረዱ ነገሮች እንድንሽቀዳደም ያዛል። ማለትም ለተቅዋ፣ ለኢማን፣ ለበጎ ስራ

Scanned by CamScanner

መሽቀዳደምን ያነሳሳል። ለደግ ነገር መሽቀዳደም ተፈላጊ እና የሚበረታታ ነው።

﴿ وَفِي ذَٰلِكَ فَلْيَتَنَافَسِ ٱلْمُتَنَٰفِسُونَ ﴿٢٦﴾ ﴾ المطففين: ٢٦

«ማሸጊያው ሚስክ ነው። የሚሽቀዳደሙ ሰዎች ለዚህ (ይህን ዐጋ ለመጉናዐፍ) ይሽቀዳደሙ።» (አል ሙጠፈፊን 26)

አላህ የቅርብ ባለሚሎቹ የሆኑ ነብያትን እንዲህ ሲል አሞግሷል፡-

﴿ إِنَّهُمْ كَانُوا۟ يُسَٰرِعُونَ فِى ٱلْخَيْرَٰتِ وَيَدْعُونَنَا رَغَبًا وَرَهَبًا ۖ وَكَانُوا۟ لَنَا خَٰشِعِينَ ﴿٩٠﴾ ﴾ الأنبياء: ٩٠

«እነርሱ (ነቢያት) ለመልካም ሥራ ይሮጡ ነበር። በጉጉትና በፍርሃትም ይጠሩን ነበር። ፍውም ታዛገሮቻችንም ነበሩ።» (አል አንቢያእ 90)

ከመጽሐፉ ሰዎች ደጎችን እንዲህ ሲል አወድሷል፡-

﴿ يُؤْمِنُونَ بِٱللَّهِ وَٱلْيَوْمِ ٱلْءَاخِرِ وَيَأْمُرُونَ بِٱلْمَعْرُوفِ وَيَنْهَوْنَ عَنِ ٱلْمُنكَرِ وَيُسَٰرِعُونَ فِى ٱلْخَيْرَٰتِ ۚ وَأُو۟لَٰٓئِكَ مِنَ ٱلصَّٰلِحِينَ ﴿١١٤﴾ ﴾ ال عمران: ١١٤

«በአላህና በመጭው ዓለም ያምናሉ። በመልካም ያዛሉ፥ ከክፉ ይከለክላሉ። ለጽድቅ ተግባራት ይሽቀዳደማሉ። እነርሱ ከደጋግ ሰዎች ናቸው።» (አሊ ዒምራን 114)

በአንጻሩ ሙናፊቆችን እንዲህ በማለት ወቅሷል፡-

﴿ وَإِذَا قَامُوٓا۟ إِلَى ٱلصَّلَوٰةِ قَامُوا۟ كُسَالَىٰ ﴾ النساء: ١٤٢

«ለሶላትም የሚቆሙት እየታከታቸውና ለመታየት ሲሉ ብቻ ነው።» (አል ኒሣእ 142)

﴿ وَلَا يَأْتُونَ ٱلصَّلَوٰةَ إِلَّا وَهُمْ كُسَالَىٰ وَلَا يُنفِقُونَ إِلَّا وَهُمْ كَٰرِهُونَ ﴿٥٤﴾ ﴾ التوبة: ٥٤

ሶላትን እየተሰላቹ እንጅ የማይሰገዱ፥ እየጠሉ እንጅ የማይለግሱ በመሆናቸው ነው።» (አል ተውባህ 54)

እንቅፋቶች ከመከሰታቸው በፊት ለበጎ ስራ መጣደፍን የአላህ መልእክተኛ አበክረው ይመክሩ ነበር። እንዲህ ብለዋል፡-

«(ለበጎ ስራ ፍጠኑ እንጅ)። ወሰን አላፊ የሚያደርግን ሐብት፣ ዝንጉ የሚያደርግን ድህነት፣ የሚያበላሽን በሽታ፣ የሚያጃጃን እርጅና፣ የሚሸኝን ሞት፣ ከፋቱ ይመጣል ተብሎ የሚጠበቀውን ደጃል ወይም መከራው የከበደና መሪር የሆነውን ትንሳኤን እንጅ ትጠባበቃላችሁን?» (ቲርሚዚ)

ከቀናት ዑደት ትምህርት መቅሰም

ሙእሚን ለቀናት ዑደት ክብደትና ግምት መስጠትና ከርሱ መማር ይጠበቅበታል። ሌትና ቀን አዲስ ነገሮችን ሁሉ ያነትባሉ። የራቀውን ሁሉ ያቀርባሉ። እድሜን ይጠቀልላሉ። ሕጻናትን ያሳረምሳሉ። ጎልማሶችን ያስረጃሉ።

የጊዜ ዑደት፣ የሌትና የቀን መፈራረቅ በሙስሊም አእምሮ ውስጥ ማስተንተንን ሳያስከትል፣ ማስተዋልና ትምህርት መቅሰም ሳይኖርበት እንዲሁ እንደዋዛ ሊያልፍ አይገባም። በእያንዳንዱ ቀን፣ በእያንዳንዱ ሰአት፣ በእያንዳንዱ ቅጽበት በዩኒቨርሱና በሕይወት ውስጥ ድንቃድንቅ ክስተቶች እውን ይሆናሉ። የሚታዩም የማይታዩም። የሚታወቁም የማይታወቁም። መረት ነፍስ ትዘራለች። ቅንጣቶች ይበቅላሉ። እጽዋት ያብባሉ። ብዙ አበቦች ያፈራሉ። ፍሪዎች ይቀጠፋሉ። ብዙ አዝመራዎች ይረግፋሉ። ሕጻናት ይወለዳሉ። ወጣቶች ይጎለምሳሉ። ጎልማሶች ያረጃሉ። አዛውንቶች ይሞታሉ። ከሰማይ ኘላኔቶች ሲዞሩ፣ ከታች ምድር ሱትሽከረከር በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ እጅግ የበዙ ነገሮች ይከሰታሉ። ደስታና መከራ፣ ሐብትና ድህነት፣ በሽታና ጤንነት፣ ሐዘንና ሐሴት፣ ችጋርና ምቾት፣ ወዘተ። ይህ ሁሉ ልብ ላለው ተአምር ነው። ሕሊና ላለው አስታዋሽ ነው። አእምሮ ላለው ትምህርት ሰጭ ነው። የባለ ልቦችን ማስተንተን፣ የባለ ሕሊናዎችን የማስታወስ ከሕሎት፣

Scanned by CamScanner

የአስተዋዮችን አስተውሎት የተነፈገውማ የቀንና የሌሊት መፈራረቅ ምንም መስሎ አይታየውም።

﴿ إِنَّ فِي خَلْقِ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ وَٱخْتِلَٰفِ ٱلَّيْلِ وَٱلنَّهَارِ لَءَايَٰتٍ لِّأُو۟لِى ٱلْأَلْبَٰبِ ﴿١٩٠﴾ ﴾ آل عمران: ١٩٠

«የሰማያትና የምድር መፈጠር፣ የቀንና የሌሊት መፈራረቅ ለአስተዋዮች ታላላቅ ተአምራት ናቸው» (አሊ ዒምራን 190)

﴿ يُقَلِّبُ ٱللَّهُ ٱلَّيْلَ وَٱلنَّهَارَ ۚ إِنَّ فِى ذَٰلِكَ لَعِبْرَةً لِّأُو۟لِى ٱلْأَبْصَٰرِ ﴿٤٤﴾ ﴾ النور: ٤٤

«አላህ ሌትንና ቀንንም ያፈራርቃል። በዚህ ውስጥ ለአስተውሎት ባለ ቤቶች ትምህርትና ተግሳጽ አለ።» (አል ኑር 44)

ጊዜን ማደራጀት

ጊዜን በአግባቡ ማደራጀት፣ በኘሮግራም ከፋፍሎ መጠቀም፣ ለእያንዳንዱ ጊዜ ተገቢውን ስራ ዱንያዊም ሆነ ዲናዊ መመደብ ተገቢ ነው። ይህ ሲሆን አንዱ ስራ የሌሎችን ጊዜ አይሻማም። ቅድሚያ የሚሰጠው ተትቶ ሌሎች አይፈጸሙም። መቅደም ያለበት አይዘገይም። መዘግየት ያለበትም አይቀድምም።

የአላህ መልእክተኛ ከኢብራሂም ድርሳን ውስጥ የሰፈረ በማለት የጠቀሱልን ቃል እንዲህ ይላል፦

«አእምሮ ያለው ሰው፣ የአእምሮ ሚዛኑ እስካልተዛባ ድረስ አራት ወቅቶች ሊኖሩት ይገባል። ይህውም አንደኛው ከአምላኩ ጋር የሚገናኝበት፣ ሁለተኛው ራሱን የሚመረምርበት፣ ሦስተኛው የአላህን ስራ የሚያስተነትንበት፣ አራተኛው ምግብ፣ መጠጥና ሌሎች አስፈልጎቶችን የሚያሟላበት ወቅት።» (ኢብን ሂባን)

ጊዜን ከፋፍሎ በኘሮግራም መጠቀም ይበልጥ የሚያስፈልግባቸው የተደራረበ ሐላፊነት ያለባቸው ሰዎች ናቸው። ምክንያቱም ሐላፊነቶች ሲደራረቡ፣ ካላቸው ጊዜ በላይ ሆነው ይሰሟቸዋል።

ከኘሮግራማችን ውስጥ የእረፍት ጊዜ መኖሩ አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም ሁሌም ቁም ነገር ላይ ብቻ መቆየት ለሰው ልጅ የሚቻል አይደለም። ቀልብ ልክ እንደ አካል ትደክማለች። ትሰለቻለች። ስለሆነም የተወሰነ መዝናኛ እና ማረፊያ ያስፈልጋታል። አሊ ቢን አቢ ጧሊብ እንዲህ ብለዋል፦

«ቀልቦችን የተወሰነ ጊዜ አዝናኑ። ምክንያቱም ከተገደዱ ይታወራሉና።»[1]

ሙስሊም አቅሙ እስኪዳከምና መቀጠል እስኪያቅተው፣ ራሱን እስኪጎዳና የቤተሰቡንም ሆነ የማሕበረሰቡን መብት እስኪያጓድል ድረስ በስራ መጠመድ የለበትም። በዓለማዊ ስራ ይቅርና በአምልኮ እንኳ ይህን ማድረግ አይደገፍም።

ይህም በመሆኑ የአላህ መልእክተኛ (ሰዐወ) ባልንጀሮቻቸውን በሌሊት ሶላት እርሳቸውን ለመከተል ባሰቡ ጊዜ እንዲህ አሏቸው፦

«ከስራ የምትችሉትን ያህል ብቻ ፈጽሙ። እናንተ ከበጎ ስራ እስካልሰለቻችሁ ድረስ አላህ ምንዳ ከመስጠት አይሰለችም። ከአላህ ዘንድ ተወዳጁ ስራ ጥቂትም ቢሆን ዘውታሪ የሆነው ነው።» (ቡኻሪና ሙስሊም)

በሌላ ሐዲስም እንዲህ ብለዋል፦

«ሐይማኖት ገር ነው። ከናንተ አንዳችሁ ሐይማኖቱን አያጠብቅም፣ ያሸነፈው ቢሆን እንጅ። ቀጥተኛ ሁኑ። ተቃረቡ። ብስራት ይድረሳችሁ።»[2] (ቡኻሪ)

የቁርአን ንባብና ጾም ከልክ በላይ ያበዛውን ሰው ሚዛናዊ እንዲሆን እንዲህ ሲሉ መክረውታል፦

«አካልህ ባንተ ላይ መብት አለው። ቤተሰቦችህ ባንተ ላይ መብት አላቸው። ባልንጀሮችህም ባንተ ላይ መብት አላቸው» (ቡኻሪ)

---

[1] ሐላልና ሐራም ከተሰኘው መጽሐፋችን ውስጥ «መዝናኛ» የሚለውን ክፍል ይመልከቱ።

[2] ቀጥተኛ ሁኑ ማለት ሚዛናዊውን የለምልኮ መንገድ ተከተሉ ማለት ነው። ተቃረቡ ማለት ምሉእ ለመሆን ቢሳናችሁ እንኳ ወደርሱ ለመቃረብ ሞክሩ ማለት ነው።

Scanned by CamScanner

በአምልኮ እና ከዓለማዊ ጉዳዮች በመራቅ ወሰን ላለፉ ወገኖች እንዲህ ብለዋቸዋል፡-

«እኔ ከናንተ ይበልጥ አላህን የምፈራ እና የምጠነቀቅ ሰው ነኝ። ግና እሰግዳለሁ እተኛለሁ። እጾማለሁ አፈጥራለሁ። ሚስትም አገባለሁ። ከኔ ፈለግ ያፈነገጠ የኔ አካል አይደለም።» (ቡኻሪ)

የነቢዩ ፈለግ ይህ ነው። ሚዛናዊ እና ልከኛ። በአካልና በመንፈስ መካከል ሚዛን ይጠብቃሉ። ለሁለቱም የሚገባቸውን ያደርሳሉ። የራስን መብትና የአላህን መብትም በሚዛናዊነት ያስተናግዳሉ።

ይህም በመሆኑ ሰውየው ራሱን በሐላል መንገድና ጫዋታዎች የሚያዝናናበት ወቅት ማበጀቱን እስልምና አይታወምም።

ሐንዞላህ የተባለው የነቢዩ ባልደረባ ከርሳቸው ጋር ሲሆንና ከቤተሰቦቹ ጋር ሲሆን የተለያየ ባህሪና ስሜት በማሳየቱ ራሱን በሙናፊቅነት በወቀሰ ጊዜ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለውታል፡-

«ከኔ ዘንድ በምትሆኑበት ሰአት የሚሰማችሁን ስሜት ጠብቃችሁ የምትቆዩ ቢሆን ኖሮ መላኢኮች በየመንገዱ እጆቻችሁን በመጨበጥ ሰላምታ ባቀረቡላችሁ ነበር። ግና ሐንዞላህ ሆይ፣ አንዴ እንዲህ አንዴ እንዲያ ማለት ተፈጥሯዊ ነው።» (ሙስሊም)

የሙስሊም ባህሪ ይህው ነው። አንዴ ለአምላኩ የተወሰነ ሰአት ይሰጣል። ሌላ ጊዜ ለራሱ ማረፊያ፣ መዝናኛ፣ መጫወቻ ጊዜ ይኖረዋል።

አስማእ የሚከተለውን አስተላልፈዋል፡-

አንዲት ሙስባሐ የያዘች እንስት ስትቆነጃጅ አየሁና፡- «እነዚህ ሁለት ነገሮች ይገናኛሉን?» ስል ጠየቅኳት። (አላህን የምታመልክና የምታስታውስ እንስት መቆነጃጀቷ ግራ ቢያጋባቸው ነው) እርሷም እንዲህ አለች፡-

«የአላህን መብት ላላጓድል እጠብቃለሁ። ግና የጨዋታ ጊዜም ያስፈልገኛል።»

ይህን ስትል የምትዋብለት ባል እንዳላት ተረዳሁ።

ሁሉም ጊዜያት የየራሳቸው ስራ አላቸው

እያንዳንዱ ወቅት በጎ ተግባራት አሉት። ሙእሚን ለየወቅቶቹ አስፈላጊ የሆኑትን በጎ ተግባራት ጠንቅቆ ማወቅ ይጠበቅበታል። ማወቅ ብቻ ሳይሆን መፈጸምም ተገቢው ነው። ይህ ሲሆን ትክክለኛ ነገሮችን በትክክለኛ ጊዜያቸው በማድረግ ከአላህ ዘንድ የበለጠ ምንዳ ይሸምታል።

አቡበክር ዑመርን በሽሊፋነት በተኳቸው ጊዜ እንዲህ አሉ፡-

«አላህ በሌሊት የማይቀበለው የቀን ተግባር አለው። በቀን የማይቀበለው የሌሊት ተግባር አለው።»

ስለዚህም ቁም ነገሩ በየትኛውም ወቅት ያገኙትን በጎ ስራ መስራት ብቻ ሳይሆን ለዚያ ወቅት የሆነውን በጎ ስራ መስራት ነው። ለዚህም ነው አላህ አምልኮዎችን በጊዜ የከፋፈላቸውና በየወቅቱ የመደባቸው። ከነዚህ ወቅቶች ዝንፍ ማለት ተቀባይነት የለውም። ይህን ያደረገው አንድ ነገር ከወቅቱ በፊትም ሆነ በኋላ ተቀባይነት እንደሌለው ሊያስተምረን ነው። አላህ ሶላትን አስመልክቶ እንዲህ ብሏል፡-

﴿إِنَّ ٱلصَّلَوٰةَ كَانَتۡ عَلَى ٱلۡمُؤۡمِنِينَ كِتَٰبٗا مَّوۡقُوتٗا ١٠٣﴾ النساء: ١٠٣

«ሶላት በአማንያን ላይ ጊዜዋ የተወሰነ ግዴታ ናትና።» (አል ኒሣእ 103)

ጾምን በተመለከተም እንዲህ ብሏል፡-

﴿فَمَن شَهِدَ مِنكُمُ ٱلشَّهۡرَ فَلۡيَصُمۡهُۖ﴾ البقرة: ١٨٥

«ከመካከላችሁ በዚህ ወር ውስጥ የተገኘ (ውሉን) በጾም ማሳለፍ አለበት።» (አል በቀራህ 185)

ስለ ሐጅም፡

﴿ٱلۡحَجُّ أَشۡهُرٞ مَّعۡلُومَٰتٞ﴾ البقرة: ١٩٧

Scanned by CamScanner

«የሐጅ (ጊዜ) የታወቁ ወራት ናቸው።» (አል በቀራህ 197)

ስለ ዘካም፡-

﴿ وَءَاتُوا۟ حَقَّهُۥ يَوْمَ حَصَادِهِۦ ﴾ الأنعام: ١٤١

«የታጨዱ ዕለትም (ለድሆች)ድርሻቸውን ስጡ።» (አል አንዓም 141)

የቀልብ ተግባር ልክ እንደ አካል ተግባራት ጊዜ ሊጠበቅላቸው ይገባል። አንድ ሊቅ እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል፡-

«የአንድ ሰው ጊዜ አራት ናቸው። አምስተኛ የላቸውም። ጸጋ፣ መከራ፣ አምልኮና ሐጢአት። በነዚህ ወቅቶች ውስጥ አላህ እንደጌትነቱ ካንተ እንደባርነትህ የሚጠብቀው መብት አለው።

ጊዜው አምልኮ የሆነለት ሰው፣ አላህ ለዚህ ስላቀናው፣ ለመልካም ተግባር ስለገጠመው ውለታውን ማስታወስ ይጠበቅበታል።

ጊዜው የአላህን ጸጋ መጠቀም የሆነለት ሰው ደግሞ ልቦናው የተደሰተች ሆና አላህን ማመስገን ተገቢው ነው።

ጊዜውን ሐጢአት በመፈጸም የተሳሳተ ተውባና ምህረት ጥየቃ ይጠበቅበታል።

መከራ በደረሰበት ጊዜም መከራውን በጸጋ መቀበልና ትእግስት ማድረግ ይጠበቅበታል። በዚህ መልክ በእያንዳንዱ የሕይወት አጋጣሚው የአላህን መብት ያደርሳል።

እኒህ ሊቅ የተናገሩት የቁርአንና የሐዲስን መልእክት ነው። ይህውም፡-

አላህ ለበጎ ያበቃው ሰው በዚህ የአላህ ችሮታ እንዲደሰት እና ውለታውን እንዲያስታውስ ቁርአን ያስተምራል፡-

﴿ قُلْ بِفَضْلِ ٱللَّهِ وَبِرَحْمَتِهِۦ فَبِذَٰلِكَ فَلْيَفْرَحُوا۟ هُوَ خَيْرٌ مِّمَّا يَجْمَعُونَ ﴿٥٨﴾ ﴾ يونس: ٥٨

"(የሰው ልጆችን) በአላህ ችሮታና እዝነት፣ በዚህ (በተሰገሳቸው ፀጋ) ይደሰቱ።" በላቸው። እርሱ ከሚሰበስቡት ሁሉ የረሐጠ ነው።" (ዩኑስ 58)

ጸጋውን ያጣኘ ሰው ደግሞ አላህን እንዲያመሰግን ቁርአን ያዛል፡-

﴿ كُلُوا۟ مِن رِّزْقِ رَبِّكُمْ وَٱشْكُرُوا۟ لَهُۥ ۚ بَلْدَةٌ طَيِّبَةٌ وَرَبٌّ غَفُورٌ ﴿١٥﴾ ﴾ سبأ: ١٥

"የጌታችሁን ሲሳይ ተመገቡ። እርሱንም አመስግኑ። ሀገራችሁ መልካም፣ ጌታችሁም መሐሪ ነው።" (ተባሉም)።" (ሰበእ 15)

ሐጢአት የፈጸመ ወደ አላህ እንዲመለስ ይመክራል፡-

﴿ قُلْ يَٰعِبَادِىَ ٱلَّذِينَ أَسْرَفُوا۟ عَلَىٰٓ أَنفُسِهِمْ لَا تَقْنَطُوا۟ مِن رَّحْمَةِ ٱللَّهِ ۚ إِنَّ ٱللَّهَ يَغْفِرُ ٱلذُّنُوبَ جَمِيعًا ۚ إِنَّهُۥ هُوَ ٱلْغَفُورُ ٱلرَّحِيمُ ﴿٥٣﴾ ﴾ الزمر: ٥٣

«በላቸው፡- "በነፍሶቻችሁ ላይ ድንበር ያለፋችሁ (ራሳችሁን የበደላችሁ) ባሮቼ ሆይ! ከአላህ እዝነት ተስፋ አትቁረጡ። አላህ በእርግጥም ኃጢአቶችን ሁሉ ይምራል። እነሆ እርሱ መሐሪው፣ አዛኙ ነውና።" (አል ዙመር 53)

መከራ የደረሰበት እንዲታገስ ያስተምራል፡-

﴿ وَلَنَبْلُوَنَّكُم بِشَىْءٍ مِّنَ ٱلْخَوْفِ وَٱلْجُوعِ وَنَقْصٍ مِّنَ ٱلْأَمْوَٰلِ وَٱلْأَنفُسِ وَٱلثَّمَرَٰتِ ۗ وَبَشِّرِ ٱلصَّٰبِرِينَ ﴿١٥٥﴾ ٱلَّذِينَ إِذَآ أَصَٰبَتْهُم مُّصِيبَةٌ قَالُوٓا۟ إِنَّا لِلَّهِ وَإِنَّآ إِلَيْهِ رَٰجِعُونَ ﴿١٥٦﴾ ﴾ البقرة: ١٥٥ - ١٥٦

«ከፍርሃትና ከረሃብ በተጨት ነገር፣ ከገንዘብና ከልጆችም፣ ከፍራፍሬዎችም በመቀነስ በእርግጥ እንሞክራችኋለን። (ሙሐመድ ሆይ!) ታጋሾችን (በጎነት) አብስር፣ እነዚያን መከራ በሚያገኛቸው፣(ችግር በሚገጥማቸው) ወቅት፡-"እኛ የአላህ ነን። መመላሻችንም ወደርሱው ነው።" የሚሉትን።" (አል በቀራህ 155-156)

ሙስሊም ባሰፈሩት ዘገባ ነቢዩ (ሰዐወ)፡- «የሙእሚን ባህሪ አስገራሚ ነው። ለርሱ ሁሉም አጋጣሚዎች በጎ ናቸው። ይህ እድል ለሙእሚን እንጅ ለሌላ ለማንም አልተሰጠም። አስደሳች ነገር ሲያገኘው አላህን ያመሰግናል። እናም በጎ ይሆንለታል። የሚያስከፋ ነገር ሲያገኘውም ይታገሳል። በጎም ይሆንለታል።» ብለዋል።

Scanned by CamScanner

በላጭ ወቅቶችን ማደን

ሙስሊም በጎ ነገርን መሽቀዳደም፣ ማለትም አላህ የተለየ ክብር የሰጣቸውን ጊዜያት እየተከታተሉና እያደነ መጠቀም ይጠበቅበታል።

የአላህ መልእክተኛ (ሰዐወ) እንዲህ ብለዋል፦

«በዓመታችሁ ውስጥ ለአምላካችሁ የተለዩ ጊዜያት አሉት። ተጠቀሙባቸው።» (ጠበራኒ)

ይህ ክብር አላህ በችሮታው ለሚሻቸው ወገኖች የሚሰጠው ነው። ሰዎችን አንዱን ከአንዱ እንዳበላለጠ ሁሉ ጊዜያትንም አበላልጧል።

﴿وَرَبُّكَ يَخْلُقُ مَا يَشَاءُ وَيَخْتَارُ مَا كَانَ لَهُمُ الْخِيَرَةُ﴾ القصص: ٦٨

«ጌታህ የሚሻውን ይፈጥራል፣ ይመርጣልም። ለነርሱ ምርጫ የላቸውም።» (አል ቀሶስ 68)

ከሌሊት «ሱህርን» ማለትም የሌሊቱን የመጨረሻ ሲሶ አብልጧል። አላህ ለባሮቹ በየሌሊቱ እየተገለጸ እንዲህ ሲል ይጣራል፦

«ምህረት የሚጠይቅና የምምረው፣ ተውባ የሚያደርግ እና የምቀበለው፣ አለን?»

እስከ ንጋት ይህንኑ ይላል። (አህመድና ሙስሊም)

ይህም በመሆኑ አላህ በጎ ሰሪ ባሮቹን እንዲህ ሲል አወደሰ፦

﴿إِنَّ الْمُتَّقِينَ فِي جَنَّاتٍ وَعُيُونٍ ﴿١٥﴾ آخِذِينَ مَا آتَاهُمْ رَبُّهُمْ ۚ إِنَّهُمْ كَانُوا قَبْلَ ذَٰلِكَ مُحْسِنِينَ ﴿١٦﴾ كَانُوا قَلِيلًا مِّنَ اللَّيْلِ مَا يَهْجَعُونَ ﴿١٧﴾ وَبِالْأَسْحَارِ هُمْ يَسْتَغْفِرُونَ ﴿١٨﴾﴾ الذاريات: ١٥ - ١٨

«(የዚያን ቀን) አላህን የሚፈሩ ሰዎች በአትክልቶችና በምንጮች ውስጥ ይሆናሉ፣ ያንን ጌታቸው የሰጣቸውን (ክብርና ዕጋ) ተቀባዮች ሆነው። እነርሱ ከዚህ በፊት (በምድረ ዓለም) መልካም ሠሪዎች ነበሩና። ከሌሊቱ የሚተኙት ጥቂትን ብቻ ነበር። ከሌሊቱ የመጨረሻ ወቅቶች ላይ (አላህን) ምሕረት ይማፀናሉ።» (አል ዛሪያት 15-18)

የአላህ መልእክተኛ (ሰዐወ) እንዲህ ብለዋል፦

«ፈጣሪ ከባሮቹ ይበልጥ ቅርብ የሚሆነው ከሌሊቱ መሐል ነው። በዚያች ሰአት አላህን ከሚያወሱት ለመሆን ከከጀልክ ሁን።» (ቲርሚዚ፣ ነሣኢና ሐኪም)

አላህ ከሳምንቱ ቀናት ውስጥ ጁሙዓን አላቀ። ለሙስሊሞች ሳምንታዊ በአላቸው ነው። በውስጡ የጁሙዓ ሶላትን ግዴታ ይዟል። ከሰዎች ጋር መገናኘትንም አመቻችቷል። አላህ ዱዓን የሚቀበልበትን ሰዓትም ከውስጡ አካቷል። ሙስሊም በዚህች ሰአት ዱዓ ካደረገ ተቀባይነት ያገኛል።

በሐዲስ የሚከተለው ተላልፏል፦

«ወደ ጁሙዓ ሶላት በመጀመሪያው ሰአት የገባ ግመል እንደመጸወተ ይቆጠርለታል። በሁለተኛው የሄደ ከብት፣ ቀጥሎ የሄደ ፍየል፣ በመቀጠል የደረሰ ዶሮ፣ ከዚያም እንቁላል እንደመጸወቱ ይቆጠርላቸዋል። ኻጢቡ ወደ ሚንበሩ ሲወጣ መላኢኮች መዝገቡን ይጠቀልላሉ።»

አላህ ከአመቱ ቀናት ውስጥ የዙልሂጃ አስር ቀናትን አልቋል። ይበልጥ የተላቀው የአረፋ ቀን ነው። እርሱም ከሁሉም የዓመቱ ቀናት የተላቀ ነው። ቡኻሪ ኢብን አባስን በመጥቀስ እንደዘገቡት ነቢዩ እንዲህ ብለዋል፦

«ከአላህ ዘንድ በነዚህ ቀናት ከሚሰራ ይበልጥ ተወዳጅ ስራ የለም።»

«በአላህ መንገድ የሚደረግ ጅሃድም ቢሆን?» ተብለው ሲጠየቁም፦ «አዎ፣ በአላህ መንገድ የሚደረግ ጅሃድም ቢሆን፣ ባይሆን ሰውየው ገንዘቡንና ራሱን ይዞ ለጅሃድ ከወጣ እና ሳይመለስ ከቀረ ብቻ ከዚህ ደረጃ ጋር እኩል ይሆናል።» አሉ።

ከወራት ውስጥም የረመዳንን ወር አላቀ። በዚህ ወር ውስጥ ለሰው ልጆች መመሪያ የሆነው ቁርአን ወርዷል። ጸም ግዴታ ተደርጎበታል። የሌሊት(ተራዊህ) ሶላት ተደንግጎበታል። በጎ ስራ ማብዛት ተወዳጅ ሆኗል። ረመዳን የሙእሚን መሀር ነው። የበጎ ሰዎች የንግድ ጊዜ ነው። የወንጀላቸውን ቆሻሻ ሊያጥቡ ይሻሉ። አላህ ተውበት አድራጊዎችን ይወዳል። ንጹሐንንም ይወዳል።

Scanned by CamScanner

ውባደት ቢን ሷሚት እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ ረመዳን በመጣ ጊዜ እንዲህ አሉ፡-

«የበረካ ወር የሆነው ረመዳን መጣላችሁ። አላህ (በችሮታው) ይከባችኋል። እዝነቱን ያወርዳል። ወንጀልን ይምራል። ዱዓን ይቀበላል። በርሱ ውስጥ የምታደርጉትን ለበጎ መሽቀዳደም (በደስታ) ይመለከታል። ከመላኢኮች ዘንድም ይኩራራባችኋል። ስለሆነም አላህን በጎ ነገራችሁን አሳዩት። እድለ ቢስ ማለት የአላህን እዝነት የተነፈገ ነው።»[1]

ረመዳን ሁሉም እጅግ ጠቃሚ ወር ነው። በላጩ ግን የመጨረሻው ሲሶ ወይም የመጨረሻዎቹ አስር ቀናት ናቸው። አስሩ ቀናት በላጭ የሆኑት ለሁለት ምክንያት ነው።

1) የወሩ መቋጫ በመሆናቸው። የስራ መለኪያው መቋጫው ነው። ለዚህም ነው የአላህ መልእክተኛ እንዲህ በማለት ዱዓ ያደርጉ የነበሩት፡-

«አላህ ሆይ፣ ከእድሜዬ መልካሙ የመጨረሻውን ከስራዬም መልካሙ ፍጻሜውን፣ ከቀናቶቼ መልካሞቹ የእለተ ቂያማን አድርግልኝ።»

2) «ለይለቱል ቀድር» በመባል የምትታወቀው የተቀደሰች ሌሊት በነዚህ አስር ቀናት ውስጥ ልትሆን የመቻል እድሏ የሰፋ በመሆኑ ነው። ይህች ሌሊት ከአንድ ሺህ ወር እንደምትበልጥ በቁርአን ተገልጿል። ክብሯም ተወስቷል፡-

﴿ إِنَّآ أَنزَلْنَٰهُ فِى لَيْلَةِ ٱلْقَدْرِ ۝١ وَمَآ أَدْرَىٰكَ مَا لَيْلَةُ ٱلْقَدْرِ ۝٢ لَيْلَةُ ٱلْقَدْرِ خَيْرٌ مِّنْ أَلْفِ شَهْرٍ ۝٣ تَنَزَّلُ ٱلْمَلَٰٓئِكَةُ وَٱلرُّوحُ فِيهَا بِإِذْنِ رَبِّهِم مِّن كُلِّ أَمْرٍ ۝٤ سَلَٰمٌ هِىَ حَتَّىٰ مَطْلَعِ ٱلْفَجْرِ ۝٥ ﴾ القدر: ١ - ٥

«እኛ እሱን ቁርአንን እጅግ በተላቀችው ሌሊት አወረድነው። ስለ ተላቀችው ሌሊት ምን የምታውቀው ነገር አለ? የተላቀችው ሌሊት ከአንድ ሺህ ወራት ትልታለች። በርሷ ውስጥ መላእክትና መንፈሱ በጌታቸው ፈቃድ (አላህ የወሰናቸውን) ነገሮች ሁሉ ይዘው (ወደ

[1] ኡዩጢ «ጀሚዑል ከቢር» ውስጥ ዘግበውታል። ጠበራኒ እና ሐኪም እንደዘገቡትም ተወስቷል።

ምድር) ይወርዳሉ። ይህች (ሌሊት) ጎህ እስኪቀድድ ድረስ ሰላም (የሠፈነባት ሌሊት) ናት።» (ሱረ ቀድር 1-5)

ይህች ሌሊት በረመዳን ውስጥ መሆኗ በቁርአን ተገልጿል። ረመዳን ቁርአን የወረደበት ወር ነውና። በመጨረሻዎቹ አስር የረመዳን ቀናት ውስጥ እንድንፈልጋትም በሐዲስ ታዘናል።

የአላህ መልእክተኛ በረመዳን የመጨረሻዎቹ አስር ቀናት ውስጥ በመልካም ስራ ይተጉ ነበር። ሌሎችንም ለአምልኮ ያበልፉ ነበር። ባጭር ይታጠቁ ነበር። ቤተሰቦቻቸውንም ለሌሊት ሶላት ያንቁ ነበር። ከመስጊድ ውስጥ «በኢእቲካፍ» ያሳልፏቸው ነበር።

አላህ ከረመዳን ቀጥሎ የተቀደሱ ወራትን (አሽሁሩል ሁሩም) አልቷል። እነርሱም ረጀብ፣ ዙልቂእዳ፣ ዙልሂጃና ሙሐረም ናቸው። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ إِنَّ عِدَّةَ ٱلشُّهُورِ عِندَ ٱللَّهِ ٱثْنَا عَشَرَ شَهْرًا فِى كِتَٰبِ ٱللَّهِ يَوْمَ خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضَ مِنْهَآ أَرْبَعَةٌ حُرُمٌ ۚ ذَٰلِكَ ٱلدِّينُ ٱلْقَيِّمُ ۚ فَلَا تَظْلِمُوا۟ فِيهِنَّ أَنفُسَكُمْ ۚ ﴾ التوبة: ٣٦

«የወራት ቁጥር -ከአላህ ዘንድ- አሥራ ሁለት ነው። (ይህ ቁጥር) አላህ ሰማያትን በፈጠረ ጊዜ ከአላህ መዝገብ ውስጥ ሰፍሯል። ከነኝህ (ወራት) መከከል አራቱ የተከበሩ ናቸው። ይህ ትክክለኛው ሃይማኖት ነው። በነኝህ (ወራት) ውስጥ ራሳችሁን አትበድሉ።» (ሱረ ተውባ 36)

በየትኛውም ወቅት ራስን መበደል ወንጀል ነው። በነዚህ ወራት መበደል ደግሞ የበለጠ ወንጀል ይሆናል።

♠ ♠ ♠

Scanned by CamScanner

የሙስሊም የየእለት ኘሮግራም

ሙስሊም እድሜው እንዲባረክለት ከፈለገ በኢስላማዊ የየእለት ኘሮግራም ራሱን መምራት ይኖርበታል። ኘሮግራሙ እንደሚከተለው ነው፦

በጊዜ ይተኛል። በጊዜም ይነሳል። ስራውንም በጠዋት፣ ቢያንስ ጸሐይ ከመወጣቷ በፊት ይጀምራል። እናም አየሩ በወንጀለኞች ትንፋሽ ከመበከሉ በፊት ንጹህ አየር ያገኛል። ወንጀለኞች ዘግይተው ነውና የሚነሱት።

እናም ሙስሊም በጠዋት ከስራ ይገኛል። ነቢዩ ዱዓ ያደረጉበትን በረከትም ያገኛል። እንዲህ ሲሉ ዱዓ አድርገዋል፦

«አላህ ሆይ፣ ለተከታዮቼ ጠዋታቸውን ባርክላቸው።» (አህመድ)

የዘመናችን ሙስሊሞች ትልቁ ችግር የየእለት ሕይወታቸውን በስርዓት አያደራጁም። ማታ እስከ እኩለ ሌሊት ያመሻሉ። ጠዋት የሱብሂ ሶላት እስኪያልፋቸው ድረስ ያረፍዳሉ። አንድ ሰለፍ እንዲህ ብለዋል፦

«ሱብሂን ጸሐይ ከወጣች በኋላ የሚሰግድ ሰው ሲሳይ (ሪዝቅ) ማግኘቱ ይገርመኛል።»

ቡኻሪ አቡ ሁረይራን በመጥቀስ እንደዘገቡት ነቢዩ (ሰዐወ) እንዲህ ብለዋል፦

«ከናንተ አንዳችሁ በሚተኛ ጊዜ ሰይጣን ከአናቱ ላይ ሦስት ቋጠሮዎችን በእያንዳንዱ ላይ፦ «ረዥም ሌሊት አለህና ተኛ» በማለት ይቋጥርበታል። ተነስቶ አላህን ሲያወሳ አንዱ ቋጠሮ ይፈታል። ውዱእ ሲያደርግ ሁለተኛው ይፈታል። ሲሰግድ ሦስተኛው ይፈታል። ብርቱና ጥሩ ስሜት ያለው ሆኖም ያነጋል። ካለበለዚያ ግን መጥፎ ስሜት ያለውና ስልቹ ሆኖ ይነሳል።»

የሰይጣን ቋጠሮዎች ሁሉ ተፈትተውለት ቀኑን በዚክር፣ በውዱእና በሶላት የተቀበለ፣ ወደ ሕይወት መድረክም ንቁ አካልና ስነ ልቦና ይዞ የሄደ ሙስሊምና የሰይጣን ቋጠሮዎች ከአናቱ ላይ ሰፍረው፣ ቀኑን በዛለ አካልና በተገለፈለፈ ስነ ልቦና በተቀበለ ሙስሊም መከካል እጅግ ከፍተኛ ልዩነት አለ።

ሙስሊም ቀኑን አላህን በመታዘዝ፣ ፈርድና ሱናዎችን ሰግዶ፣ ነቢዩ ካስተማሩት ዚክር የተወሰነውን አንብቦ ይቀበለዋል። ከሚያደርጋቸው ዚክሮች መካከል፦

«እኛም ሆንን ንግስና የአላህ ሆኖ አነጋን። ምስጋና ለአላህ ይድረሰው። አጋር የለውም። ከርሱ ሌላ አምላክ የለም። መመለሻም ወደርሱ ነው።»

«አላህ ሆይ፣ በኔም ሆነ በሌላ ፍጡር ላይ ያነጋው ጸጋ ካንተ ብቻ ነው። አንድ ነህ። አጋር የለህም። ምስጋና የሚገባው ላንተ ነው።»

«አላህ ሆይ፣ ካንተ በሆነ ጸጋ፣ ጤንነት እና ነውሬ ተሸፍኖልኝ አደርኩ። በዚህችም ሆነ በመጭው አለም ጸጋህን ሙላልኝ። የሰጠህኝን ጤንነትም አክልልኝ። ነውሬንም የበለጠ ሸፍንልኝ።»

ከዚያም ከተከበረው የአላህ መጽሐፍ ውስጥ ያሻውን ያህል በጹሙም ተመስጦና በማስተንተን ይቀራል። አላህ እንዲህ ብሏል፦

﴿كِتَٰبٌ أَنزَلۡنَٰهُ إِلَيۡكَ مُبَٰرَكٞ لِّيَدَّبَّرُوٓاْ ءَايَٰتِهِۦ وَلِيَتَذَكَّرَ أُوْلُواْ ٱلۡأَلۡبَٰبِ ٢٩﴾ ص: ٢٩

«ይህ ወዳንተ ያወረድነው የተባረከ መጽሐፍ ነው። አንቀጾቹን ያስተነትኗቸው፣ የአዕምሮዎች ባለቤቶችም ይገሰጹበት ዘንድ (አወረድነው)።» (ሷድ 29)

መጠነኛ ቁርስ ተመግቦም ወደ እለታዊ ስራው ይገባል። ሲሳይ ፍለጋ ይሰማራል።ራሱን ሐላል በሆነ የትኛውም ተግባር ያሰማራል። የቱን ያህል ባለ ሐብት ቢሆንም እንኳ መስራት አያቆምም። መቆጣጠርና መምራት ብቻም ስራ ነው። ምክንያቱም ቁጥጥር አልባ ገንዘብ ስርቆት ያስተምራል።

ኢስላም አራጣን እርም ይደረገው ለዚሁ ነው። ገንዘብ ብቻ ልፋት እና አደጋ ሳይኖሩ ገንዘብን ስለሚወልድ። የገንዘቡ ባለቤት እግሩን አጥፎ ይቀመጥና 10% የአራጣ ትርፍ -ያለ ልፋት- ይመጣለታል። ይህ እስልምና ለሰው ልጅ ካለው እይታ ጋር ይቃረናል። ምክንያቱም የሰው ልጅ የተፈጠረው ሲያመርት ነው። የተላከው ምድርን በስራ ሊያንጽና ሊያስውብ ነው።

﴿هُوَ أَنشَأَكُم مِّنَ ٱلۡأَرۡضِ وَٱسۡتَعۡمَرَكُمۡ فِيهَا﴾ هود: ٦١

Scanned by CamScanner

«ከምድር ያበቀላችሁ፣ ከበላዩም ያሰፈራችሁ እርሱ ነው።» (ሁድ 61)

ሰውየው ከሕይወት እንደሚቀበለው ሁሉ መስጠት አለበት። እንደሚያጠፋው ሁሉ ማምረት አለበት። መብላት እንጅ መስራት የማያውቅ ቦዘኔ ሆኖ መኖር የለበትም። በአምልኮ ስም እንኳ ቢሆን ይህ ሊፈጸም አይገባም። በእስልምና ብህትውና የለምና።

በይሐቅይ እንደዘገቡት አብደላህ ቢን ዙብይር እንዲህ ብለዋል፡-

«በዚህች አለም ላይ አደገኛው ነገር ስራ ፈትነት ነው።»

ዓላመተል መናዊ፡- «ፈይደልቀደር» በተባለ መጽሐፋቸው ይህን አባባል ሲያብራሩ፡-

«ሰውየው በስራ ሳይጠመድ ሲቀር ውስጡ ባዶ ይሆናል። ቀልቡ ግን ባዶውን አይቀመጥምና ስይጣን ጎጆውን ይቀልስበታል። በከፍተኛ ፍጥነትም ይራባበታል። በዓለማዊ ስራ የሰው ልጆችን ያልጠቀመ ሰው እነርሱ ያመረቱትን በመብላት ሕይወታቸውን ያጠብባቸዋል። እናም መኖሩ ለእነርሱ ፋይዳ የለውም። እንዲያውም ውሃ እያደፈረሰ እና የሸቀጥ ዋጋ እያናረ ይጎዳቸዋል።

ይህም በመሆኑ ዑመር ግርማ ሞገስ ያለው ሰው ሲመለከቱ፡- «ሙያ አለውን?» በማለት ይጠይቃሉ። «የለውም» ከተባሉ ይንቁታል።»

ሙስሊም የእለት ተግባሩን ከኢባዳ (አምልኮ) እና ከጅሃድ ይቆጥረዋል። ይህም የሚሆነው ሐሳቡ (ኒያው) ከተስተካከለ፣ አላህን ከማስታወስ ካላዘናጋው እና ተግባሩን በፍጹም ጥራት ካከናወነ ነው። ስራን በብቃት መስራት ኢስላማዊ ግዴታ ነውና። በሐዲስ የሚከተሰው ተወስቷል፡-

«አላህ በሁሉም ጉዳዮች ላይ ማሳመርን ጽፏል።» (ሙስሊም)

«ከናንተ አንዳችሁ ስራ በሚሰራ ጊዜ በብቃት (አሳምሮ) መስራቱን አላህ ይወዳል።» (በይሐቂ)

ሙስሊም ሊዘነጋው የማይገባው ሌላው የእለት ተግባር ሕብረተሰቡን የማገልገል እና ባለ ጉዳዮችን የመርዳት ሐላፊነት ነው። ይህን ሲሰራ ምጽዋት እንደሰጠ ይቆጠርለታል። ቡኻሪና ሙስሊም አቡዘርን በመጥቀስ እንደዘገቡት ነቢዩ (ሰዐወ) እንዲህ ብለዋል፡-

[1] ፈይደል ቀድር 290-29

«እያንዳንዱ ሙስሊም ምጽዋት (ሶደቃ) ሊሰጥ ይገባል።» በማለት ተናገሩ። «የአላህ መልእክተኛ ሆይ፣ ካላገኘስ» ተባሉ። «ብእጁ ሰርቶ ራሱን ይጥቀም። ይመጽውትም።»አሉ። «ካልቻለስ ወይም ካልሰራስ?» አሏቸው። «የተቸገረን ባለ ጉዳይ ይርዳ።» አሉ። «ይህን ካላደረገስ?» አሏቸው። «በመልካም ይዘዝ» አሉ። «ካላደረገውስ?» አሏቸው። «ከመጥፎ ይታቀብ» ምጽዋት ይሆንለታል።» አሉ።

ይህ ምጽዋት ወይም ማሕበራ ግብር የሙስሊም የየእለት ግዴታ ነው። ከዚህም አልፎ ጸሐይ በወጣች ቁጥር በእያንዳንዱ የሰውነት ክፍሉ ልክ ይህ ምጽዋት እንዳለበት ተገልጿል። ይህ ሲሆን ሙስሊም በዙሪያው ላሉ ሰዎች የመልካም ነገሮችና የሰላም ምንጭ፣ የሐብት መገኛ ማእከል ይሆናል።

አቡ ሁረይራ እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ማለታቸውን ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበዋል፡-

«የሰው ልጅ እያንዳንዱ የሰወነት ክፍል ምጽዋት (ሶደቃ) አለበት። ጸሐይ በምትወጣበት እያንዳንዱ ቀን የተጣሉትን ማስታረቅህ ሶደቃ ነው። አንድን ሰው ከመጓጓዣው ላይ እንዲወጣ ማገዝህ ወይም እቃውን ማቀበልህ ሶደቃ ነው። መልካም ንግግር ሶደቃ ነው። ወደ ሶላት የምትሄድበት እያንዳንዱ እርምጃ ሶደቃ ነው። ከመንገድ ላይ አንትፋትን ማስወገድም ሶደቃ ነው።»

እያንዳንዱ የሰውነት ክፍል ከአላህ የተሰጠ ጸጋ በመሆኑ አላህ ለዚህ ጸጋው ሊመሰገን ይገባል። የአካል ክፍሉችም እርሱን ለማገልገል ተግባር ሊውሉ ይገባል። ሕብረተሰቡን ማገልገል እና በጎ መስራት አላህን የማገልገል አካል ነው።

እኩለ ቀን ላይ ሙስሊም የዙህርን ሶላት ከቻለ በጀማዓ ለመስገድ ወደ መስጊድ ይጓዛል። በወቅቱ መጀመሪያ ላይ መስገድ የአላህን ወዴታ ያስገኛል። አላህ በበጎ ነገር መሽቀዳደምን አሏል። የአላህ መልእክተኛም ከጀማዓ ሶላት የቀሩ ግለሰቦችን ቤት ለማቃጠል እስከማሰብ ደርሰዋል። የጀማዓ ሶላት በግል ከሚሰገድ ሶላት በ27 ደረጃዎች እንደሚልቅም አስተምረዋል። በተለይም በመስጊድ ወስጥ የሚሰገድ ጀማዓ ደረጃው የላቀ ነው።

Scanned by CamScanner

ሙስሊም እኩለ ቀን ላይ ሐሳል የሆነ ምግብ ሚዛናዊ በሆነ የአመጋገብ ስልት፣ ማለትም ቁንጣን እስኪይዘው ሳያበዛ ወይም የረሃብ ጠኔ እስኪያንገላታው ሳያሳንስ ይመገባል። አላህ እንዲህ ብሏል፦

﴿ يَٰبَنِيٓ ءَادَمَ خُذُواْ زِينَتَكُمۡ عِندَ كُلِّ مَسۡجِدٖ وَكُلُواْ وَٱشۡرَبُواْ وَلَا تُسۡرِفُوٓاْۚ إِنَّهُۥ لَا يُحِبُّ ٱلۡمُسۡرِفِينَ ٣١ قُلۡ مَنۡ حَرَّمَ زِينَةَ ٱللَّهِ ٱلَّتِيٓ أَخۡرَجَ لِعِبَادِهِۦ وَٱلطَّيِّبَٰتِ مِنَ ٱلرِّزۡقِۚ ﴾

الأعراف: ٣١ - ٣٢

"የአደም ልጆች ሆይ! (ነውራችሁን የሚሸፍኑ) ጌጦቻችሁን በየትኛውም የየሱጁድ ቦታና ጊዜ ልበሱ። ብሉ፣ ጠጡም። ግና አታባክኑ። እርሱ አባካኞችን አይወድምና። (ሙሐመድ ሆይ!) በላቸው፦ "ያችን ለባሮቹ የፈጠራትን የአላህ ጌጥ፣ ከሲሳይም መልካሞቹን እርም ያደረገ ማን ነው?" (ሱል አዕራፍ 31-32)

በሞቃታማ አገር በተለይም በበጋ ወራት ሰዎች ሌሊት ለመነሳት፣ በጊዜም ለመንቃት ይችሉ ዘንድ ከሰአት በኋላ ጥቂት ረፍት ማድረግ (እንቅልፍ መተኛት) ሊያስፈልጋቸው ይችላል። «ቀይሉላ» (Nap) ይባላል።ቁርአን እንዲህ ሲል ይህን የእረፍት ሰአት ጠቁሟል፦

﴿ وَحِينَ تَضَعُونَ ثِيَابَكُم مِّنَ ٱلظَّهِيرَةِ ﴾ النور: ٥٨

«በቀትርም ልብሶቻችሁን በምታወልቁ ጊዜ።» (ሱል ኑር 58)

የዓስር ወቅት ደርሶ አዛ አድራጊው «ወደ ሶላት ኑ» በሚል ጊዜ ሙስሊም ረፍት ላይ ከሆነ ይነሳል። ስራ ላይ ከሆነም ስራውን አቁሞ ወደ «መሐከለኛዋ» ሶላት ይጣደፋል። ዓለማዊ ስራው ከዚህች ሶላት ሊያዘናጋው አይገባም። የሙእሚን ባሀሪ ምንጊዜም በሚከተለው የቁርአን ቃል የተገለጸው መሆን አለበት፦

﴿ رِجَالٞ لَّا تُلۡهِيهِمۡ تِجَٰرَةٞ وَلَا بَيۡعٌ عَن ذِكۡرِ ٱللَّهِ وَإِقَامِ ٱلصَّلَوٰةِ وَإِيتَآءِ ٱلزَّكَوٰةِ يَخَافُونَ يَوۡمٗا تَتَقَلَّبُ فِيهِ ٱلۡقُلُوبُ وَٱلۡأَبۡصَٰرُ ٣٧ ﴾ النور: ٣٧

«ንግድም ሆነ ሽያጭ አላህን ከማውሳት፣ ሶላትን በአግባቡ ከመስገድና ዘካም ከመስጠት የማታዘናጋቸው፣ ልቦችና ዓይኖች የሚገላበጡባቸውንም ቀን የሚፈሩ ወንዶች (ዘወትር ያመሰግኑታል)።»
(ሱል ኑር 37)

ሙስሊም የዓስርን ሶላት ጸሐይ ልትገባ እስክትቃረብ ድረስ ማዘግየት የለበትም። በዚህ ወቅት መስገድ የሙናፊቆች ባህሪ ነው። የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፦

«ይህች የሙናፊቅ ሶላት ናት። ይህች የሙናፊቅ ሶላት ናት። ይህች የሙናፊቅ ሶላት ናት። ጸሐይ ልትገባ እስክትቃረብ ይጠብቁና በለይጣን ቀንዶች መካከል ስትሆን ተነስቶ አራት ጊዜ በፍጥነት ጎንበስ ቀና ይላል። ከዚያ ውስጥ አላህን ጥቂትን እንጅ አያወሳም።» (ሙስሊም)

ጸሐይ ስትጠልቅ ሙስሊም ለመግሪብ ሶላት ይጣደፋል። በወቅቱ መጀመሪያ ላይም ይሰግዳታል፡ በተለይም ወቅቱ ጠባብ በመሆኑ ፈርዱንና ሱንና ሶላቱን ካጠናቀቀ በኋላ አላህ ያገራለትን ዚክር ያደርጋል። ለምሳሌ፦

«አላህ ይህ የቀንህ መሸሽ፣ የሌሊትህ መምጣትና የጠሪህ ድምጽ ነው። ስለሆነም ማረኝ።»

ጠዋት ላይ ያደረገውን አይነት ዚክርም፦ «አነጋን» በሚለው ምትክ «አመሸን» የሚል ቃል አስገብቶ ይዘክራል። ራት በመጠኑ ይመገባል። ከዚያም ኢሻን ይሰግዳል። ሱንናዎችን ያከላል። ሌሊት እንደሚነሳ ከተማመነ የዊትር ሶላትን ያዘገያል። ካልሆነ ግን ከመተኛቱ በፊት ይሰግዳል።

ራቱን ከኢሻ ሶላት በኋላ ሊያደርገውም ይችላል። ቀድሞ ከቀረበ ግን በሐዲስ እንደተነገረው ራቱን ያስቀድማል። ይህም የሆነው በምግብ አምሮት አእምሮው ተጠምዶ ለሶላት እንዳይቆም ለማድረግ ነው።

ከመተኛቱ በፊትም አንዳንድ ግዴታዎችን ሊወጣ ይችላል። ለምሳሌ ሰዎች መዘየር (መጠየቅ)። በየቀኑ የንባብ ኘሮግራም ሊኖረው ይገባል። ይህ ሲሆን የአወቀቱ ክምችት በየቀኑ ይጨምራል። አላህ ለነቢዩ እንዲህ ሲል አሏቸዋል፦

﴿ وَقُل رَّبِّ زِدۡنِي عِلۡمٗا ١١٤ ﴾ طه: ١١٤

---

[1] ነቢዩ ﷺ፦ «የኢሻ ሶላት ኢቃማ ተደርጎ ሊሶለ ራት ከተቀረበ እራቱን አስቀድሙ።» ብለዋል። (ቡኻሪና ሙስሊም)
በእርግጥ ሐዲሱ የተነገረው፦ በኢብን ዑመር እይታ መሠረት ከመግሪብ ሶላት ጋር የተያያዘ ቢሆንም ሁሉንም የሶላት ውቶቶች ያካትታል።

Scanned by CamScanner

"ጌታዬ ሆይ! እውቀትን ጨምርልኝ።" በልም። (ጧሃ 114)

ለዲኑም ሆነ ለዱንያው ጠቃሚ የሆኑ ጋዜጦችንና መጽሔቶችን መርጦ ቢያነብ ይበረታታል። አንድ ሊቅ፡- «የምታነበውን ንገረኝና ማንነትህን እነግርሐለሁ»በማለት ንባብ በሰውየው ስብእና ላይ ያለውን ተጽእኖ ገልጸዋል።

በቀን ወይም በማታ ሐላል በሆኑ ጨዋታዎች መዝናናትም ይፈቀዳል። ይሁንና መዝናናት ከኢባዳ ወይም ከእንቅልፍና ከእረፍት ሊያዘናጋው፣ የቤተሰቡን መብት እንዲያጓድል ሊያደርገው፣ በስራው ላይ ጫና ሊፈጥርበት ወይም ሌሎች ግዴታዎችን እንዳይወጣ እንቅፋት ሊሆንበት አይገባም።

ማታ ረዥም ጊዜ ተቀምጦ ማምሸት የተጠላውም ሳያስበው ሐላፊነቶቹን እንዳያጓድል ስለሚያሰጋ ነው። በአንድ ነገር ላይ ከመጠን ማለፍ ሌላወን ነገር መጉዳቱ የተለመደ ነው። ይህ ደግሞ በቁርአን የተላለፈውን ተከታዩን ትእዛዝ ይጻረራል፡-

﴿ أَلَّا تَطْغَوْا فِي الْمِيزَانِ ﴿٨﴾ وَأَقِيمُوا الْوَزْنَ بِالْقِسْطِ وَلَا تُخْسِرُوا الْمِيزَانَ ﴿٩﴾ ﴾ الرحمن: ٨ - ٩

«ሚዛን ላይ አትበድሉ። በትክክል መዝኑ። ሚዛንን አታጉድሉም።» (አል ረህማን 8-9)

አላህ ያዘዛ ውን አስር መብቶች በአግባቡ መወጣትን ሙስሊም ምንጊዜም ሊዘነጋ አይገባም። እነርሱም አላህ በቁርአኑ ወስጥ እንዲጠበቁ ያዘዛቸው መብቶች ናቸው፡-

﴿ وَاعْبُدُوا اللَّهَ وَلَا تُشْرِكُوا بِهِ شَيْئًا وَبِالْوَالِدَيْنِ إِحْسَانًا وَبِذِي الْقُرْبَىٰ وَالْيَتَامَىٰ وَالْمَسَاكِينِ وَالْجَارِ ذِي الْقُرْبَىٰ وَالْجَارِ الْجُنُبِ وَالصَّاحِبِ بِالْجَنبِ وَابْنِ السَّبِيلِ وَمَا مَلَكَتْ أَيْمَانُكُمْ ﴾ النساء: ٣٦

«አላህንም (በብቸኝነት) አምልኩ። ከርሱ ጋር አንድንም አካል አታጋሩ። ለወላጆቻችሁም መልካም ዋሉ። ለቅርብ ዘመዶቻችሁም፣ ለየቲሞችም፣ ለድሆችም፣ ዘመድ ለሆነ ጉረቤትም፣ ለጉን ጉረቤትም፣ ለቅን (ለቅርብ) ባልደረባም፣ (ስንቅ ላለቀበት) መንገደኛም፣ እጆቻችሁ በባለቤትነት ለያዟቸውም (ባሮቻችሁም) (እንዲሁ መልካም ዋሉ)።» (አል ኒሣእ 36)

የመጀመሪያው ሐቅ (መብት) የፍጡራን ፈጣሪ፣ የነገሮች ሁሉ ባለቤት፣ ሕይወትን ለጋሽ፣ ጸጋ ሰጭ የሆነው አላህ መብት ነው።

﴿ وَمَا بِكُم مِّن نِّعْمَةٍ فَمِنَ اللَّهِ ﴾ النحل: ٥٣

«የጌታችሁ ዐጋዎች ሁሉ ከአላህ (የተገኙ) ናቸው።» (አል ነህል 53)

የአላህን መብት ችላ ማለትና ከርሱ መዘናጋት ከሙስሊም የሚጠበቅ አይደለም። በዚህ ረገድ ጉልሁ ግዴታ አላህ የእወነተኛ አማኞች ዋነኛ መገለጫ ያደረጋትን ሶላትን በወቅቱና በአግባቡ መፈጸም ነው፡-

﴿ الَّذِينَ هُمْ فِي صَلَاتِهِمْ خَاشِعُونَ ﴿٢﴾ ﴾ المؤمنون: ٢

«እነዚያ ሶላታቸውን በፍዑም ተመስጦ የሚፈጽሙት፡» (አል ሙእሚኑን 2)

ሌላው የአማኞች ባህሪ ሶላትን መጠበቅ ነው፡-

﴿ وَالَّذِينَ هُمْ عَلَىٰ صَلَوَاتِهِمْ يُحَافِظُونَ ﴿٩﴾ ﴾ المؤمنون: ٩

«እነዚያ ሶላቶቻቸውን ወቅታቸውን ጠብቀው የሚሰግዱት፡» (አል ሙእሚኑን 9)

ወቅቱ እስኪያልፍ ድረስ የሚያዘገያትን ሰው አላህ ክፉኛ ኮንኖታል። «ወዮለት» ሲልም ዝቶበታል፡-

﴿ فَوَيْلٌ لِّلْمُصَلِّينَ ﴿٤﴾ الَّذِينَ هُمْ عَن صَلَاتِهِمْ سَاهُونَ ﴿٥﴾ ﴾ الماعون: ٤ - ٥

«ለሰጋጆች ወዮላቸው፣ ለእነዚያ ስግደታቸውን ዘነጊዎች ለሆኑ (ሰጋጆች)፡» (አል ማዑን 4-5)

ሁለተኛው መብት የወላጆች መብት ነው። የነርሱን መብት መጠበቅ አላህን በብቸኝነት ከማምለክ ጋር ተቆራኝቶ በቁርአን ተጠቅሷል። ቁርአንና ሐዲስ በተለይም ለእናት የተለየ ትኩረት ይሰጣሉ። የርሷ መብት ከአባት መብት ይበልጥ ከባድ ነው። ልጅ በመውለድና በማሳደግ ሂደት ከአባት የበለጠ መስራ ትሸከማለች።

Scanned by CamScanner

﴿ حَمَلَتْهُ أُمُّهُۥ كُرْهًا وَوَضَعَتْهُ كُرْهًا ۖ وَحَمْلُهُۥ وَفِصَٰلُهُۥ ثَلَٰثُونَ شَهْرًا ﴾ الأحقاف: ١٥

«እናቱ በሞንቅ (በችግር፣ በስቃይ...) አረገዘችው። በሞንቅም ወለደችው። ከተረገዘ እንስቶ ጡት እስኪጥል ድረስ ያሉት ጊዚያት (ለእናቱ ቀላል አይደሉም)። ሠላሳ (የድነገም) ወራት ናቸው።» (አል አህቃፍ 15)

ሰዎች በዓመት አንድ ጊዜ፡- «የእናት ቀን» የሚል በአል ለይተው በዚያ ቀን ለእናት ትኩረት ማድረግን ብቻ ኢስላም በቂ ነው ብሎ አይወስደውም። የዓመቱ ሁሉም ቀናት የእናት ቀናት እንዲሆኑ ይሻል።

ቀጥሎ የዘመድ መብት (ሐቅ) ይከተላል። የወንድም፣ የእህት፣ የአክስት፣ የአጎት፣ የልጆቻቸውና የሌሎችም ቤተሰቦች መብት መጠበቅ ይኖርበታል።

በሕብረተሰቡ ወስጥ የደካሞች መብትም አለ። እነርሱም የቲሞች፣ ድሆች፣ ጎዳና ተዳዳሪዎች ናቸው።

በማሕበራዊ ግንኙነት የምታገኛቸው ሰዎች ማለትም የጎረቤት፣ የስራ ባልደረባ፣ የንዞም ሆነ የአገር ቤት ባልንጀራ፣ የትዳር ጓደኛ ወዘተ መብቶች ይከተላሉ።

የነዚህ መብቶች መቋጫ በስር የሚገኙ አገልጋዮች መብት ነው። በጥንት ዘመን ለአገልጋዮች የሚውል ቢሆንም በአንድ ሰው ስር ያሉ ሁሉንም አይነት ሰዎች ያጠቃልላል። የቤት ሰራተኞች፣ እንስሳት፣ መገልገያ ቁሳቁሶች እዚህ ውስጥ ይካተታሉ። ለሁሉም በጎ መዋል፣ በአግባቡ መያዝና መጠበቅ፣ አለማባከንና አለማለቃየት ተገቢ ነው።

አንድ ሙስሊም ወደ እንቅልፍ መሄድ ሲፈልግ ውዱእ አድርጎ ሁለት ረከዓዎችን ከሰገደ በኋላ በቀኝ ጎኑ ጋደም ብሎ ከነቢዩ የተገኙ ዚክሮችንና ዱዓዎችን ማድረጉ ይወደዳል። ለምሳሌ እንዲህ ቢል፡-

«ጌታዬ ሆይ፣ በስምህ ጎኔን አሳረፍኩ። ባንተም አነሳዋለሁ። ነፍሴን በዚያው ካስቀረሃት ማራት። ከላክካት ደግሞ ደጋግ ባሮችህን በምትጠብቅበት ብልሐትህ ጠብቃት።»

ዑለሞቻችን የየእለት ተግባራትን በማስመልከት ከጻፏቸው መጽሐፍት ሊጠቀም እንደሚገባው አናስታውሳለን።

ለምሳሌ ኢማም ነሳኢ «የቀንና የሌሊት ተግባራት» የሚል መጽሐፍ ጽፈዋል። ኢማም አል ነወዊም «አል አዝካር» የተሰኘ መጽሐፍ ጽፈዋል። ሸይኽል ኢስላም ቢን ተይሚያህ «አልከላሙ ጦይብ»፣ ተማሪያቸው ኢብኑል ቀይም «አልዋሲ ሶይብ»፣ ኢብንል ጀዙሪ «አልሂስኑል ሒስን»፣ ኢማም ሸውካኒ «ቱህፈቱ ዛኪሪን»፣ በዚህ ዘመን የተነሱ ዓሊሞችም ለምሳሌ ኢማም ሸሂድ ሐሰን አልበንና «አልመእሱራት» የተሰኙ መጽሐፍት ጽፈዋል።

♣ ♣ ♣

@iqraabookspdf

Scanned by CamScanner

ትላንት፣ ዛሬና ነገ

የሰው ልጅ የሚኖርበት ጊዜ በሦስት ይከፈላል። ያለፈ፣ አሁን ያለ እና ወደፊት የሚመጣ ወይም ትላንት፣ ዛሬና ነገ ተብሎ።

ሰዎች ከነዚህ ወቅቶች ጋር ባላቸው ግንኙነት እየቅል የሆነ ባህሪ አላቸው። በአብዛኛው ከሁለት ተቃራኒ ጠርዞች ላይ መቆም ይስተዋልባቸዋል።

- የትላንት አምላኪዎች አሉ።
- የዛሬ አምላኪዎች አሉ።
- የነገ ሕልመኞች አሉ።
- ከነዚህ በተጓዳኝ ለሦስቱም ጊዜያት የሚገባቸውን ትኩረት የሚሰጡ ሚዛናዊያንና ልከኞች ይገኛሉ።

ትላንትን የሙጥኝ ያሉ

ትላንትን እንጅ የማያውቁ ሰዎች እናገኛለን። ያለፈውን ብቻ ይኖራሉ። ለሌላው ትኩረት አይሰጡም። ዛሬ አይታያቸውም። ነገንም አያልሙም። ባለፈው ተውጠዋል። ባላለፉት ግለሰባዊ ሕይወትና ጀብዱ ሊሆን ይችላል። ወይም ደግሞ በቤተሰባቸው፣ በወገኖቻቸውና በሕዝባቸው ታሪክና ቅርስ ሊሆን ይችላል። እንዲህ ዓይነት ትላንትን አምላኪ ሰዎች በርካታ መገለጫዎች አሏቸው፦

1) አንዳንዶቹ በጥንቱ ብቻ እየተኩራሩ፣ ትላንትን ከዛሬ የሚያገናኝ አዲስ ነገር ሳያክሉ እንዲሁ ብቻ ባለፈ ታሪክና ማንነት እየተኮፈሱ የሚኖሩ አሉ። «አባቶቻችንና አያቶቻችን እንዲህ ሰርተዋል።» በማለት ማውጋት ይወዳሉ። «እኛ ይህን ፈጽመናል።» የሚሉበት አንደበት ግን የላቸውም። እነርሱን በማስመልከት አንድ ገጣሚ እንዲህ ብሏል፦

ባባቶችህ ታላቅነት መኩራትህ ቢሆንም እውነት

ግን ልጃቸው አንተ ነህና ምን ይከፋ የወለዱት

ባለፈው ታሪክ፣ በአያት ቅድመ አያት ጀብዱና ድርጊት መኩራራት የጀመሩትን ለመጨረስ፣ አርአያነታቸውን ለመከተል ከሆነ የሚመሰገን ነው። መኩራራቱ ብቻ ግን ፋይዳ አይኖረውም።

2) «ቅርስ አምላኪዎች» በዚህ ረገድ ይጠቀሳሉ። ያለፈውን ሁሉ፣ ትክክ ሉንም ስህተቱንም፣ ቀልዱንም እንዳለ እንደ ቅዱስ ነገር አድርገው ይቆጥሩታል። በነርሱ እይታ ያለፈው ከአሁኑ ምንጊዜም የተሻለ ነው። የጥንቶቹ ለአሁኖቹ የተውት ነገር የለም፣ የተሻለ ነገር መፍጠር አይቻልም ብለው ያምናሉ።

ትክክለኛው አቋም ግን «ቅርስ» የሚባለውን ነገር በትክክል መግለጽና መገምገም ነው። ቁርአንንና ሱንናን የኛ የሙስሊሞች የቅርስ አካል አድርጎ የሚቆጥር አለ። እነርሱን አጥብቀን እንድንይዝ ታዘናል፦

﴿وَمَا كَانَ لِمُؤْمِنٍ وَلَا مُؤْمِنَةٍ إِذَا قَضَى اللَّهُ وَرَسُولُهُ أَمْرًا أَن يَكُونَ لَهُمُ الْخِيَرَةُ مِنْ أَمْرِهِمْ﴾ الأحزاب: ٣٦

«አማኝ ወንዶችም ሆኑ አማኝ ሴቶች አላህና መልዕክተኛው አንዳች ነገር ሲወስኑ ከዚያ (ከነርሱ ውሳኔ) የተለየ ምርጫ (አና ሐሳብ) ሊኖራቸው አይገባም።» (አል አህዛብ 36)

መለኮታዊው የቅርሳችን አካል ለድርድር የሚቀርብ አይደለም። ሰዋዊ የቅርሳችን ገጽታ ግን በትክክል መፈተሽና መመዘን አለበት። ስንዱውን ከአንክርዳዱ በመለየት ጠቃሚውን መውሰድ፣ ጎጅውን ማስወገድ ተገቢ ነው። አካባቢያዊ ባህሪ ያለው አለ። የፈለቀበትን አካባቢ ባህሪ የተላበሰ፣ ለሌላ አካባቢ የማይሆን፣ ለአንድ ዘመን እንጅ ለሌላ ዘመን የማይበጅ አለ። ስለ ታሪክና ቅርስ ስናወራ እነዚህ ሁሉ ነገሮች ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው።

ለዚህም ነው ስረ-መሠረትን ከማስታወስ (አሷላ) በተጓዳኝ ዘመኑን መምሰልን (ሙዓሰራህ) ጥሩ የሚሆነው።

3) ይለፈውን፣ አያት ቅድመ አያቶች ስላደረጉት ብቻ የሙጥኝ የሚልና በጭፍኑ የሚከተል፣ እውነቱን ከሐሰት፣ ጥሩውን ከመጥፎው፣ ስንዱውን ከእንክርዳዱ፣ ምርቱን ከገለባው ለመለየት ፍላጎቱ የሌለው አለ። አቋሙ መከተል እንጅ መፈተሽ አይደለም። ባለፈው መመራት እንጅ አንዳች ነገር መፍጠር አይደለም። ይህን በተመለከተ ቁርአን እንዲህ ብሏል፦

Scanned by CamScanner

﴿ وَإِذَا قِيلَ لَهُمُ ٱتَّبِعُوا۟ مَآ أَنزَلَ ٱللَّهُ قَالُوا۟ بَلْ نَتَّبِعُ مَآ أَلْفَيْنَا عَلَيْهِ ءَابَآءَنَآ ۚ أَوَلَوْ كَانَ ءَابَآؤُهُمْ لَا يَعْقِلُونَ شَيْـًٔا وَلَا يَهْتَدُونَ ﴿١٧٠﴾ ﴾ البقرة: ١٧٠

"(ካላችሁበት የክህደት ጽልመት ወጥታችሁ) አላህ (በነቢዩ ሙሐመድ ላይ) ያወረደውን (መልዕክት) ተከተሉ።" በተባሉ ጊዜ "በፍፁም! የምንከ ተለው የአባቶቻችንን ፈለግ ነው።" ይላሉ። (ይህ አቋማቸው እጅግ የሚደንቅ ነው!) አባቶቻቸው ምንም ነገር የማያውቁና ቅኑን ጐዳናም ያልጨበጡ ቢሆኑም (እንኳ ይከተሏቸዋልን?)" (አል በቀራህ 170)

በጥንት የአላህ መልእክተኞች ጥሪ ላይ እንቅፋት የሆነው ይህ አይነቱ አስተሳሰብ ነው። የሁድ ወገኖች እንዲህ ብለዋል፦

﴿ قَالُوٓا۟ أَجِئْتَنَا لِنَعْبُدَ ٱللَّهَ وَحْدَهُۥ وَنَذَرَ مَا كَانَ يَعْبُدُ ءَابَآؤُنَا ۖ ﴾ الأعراف: ٧٠

"ወደኛ የመጣኸው አላህን ብቻ እንድናመልከና አባቶቻችን ያመልኳቸው የነበሩ (አማልክትን) እንተው ዘንድ ነውን?።" (አል አዕራፍ 70)

የሷሊህ ወገኖችም እንዲህ ብለዋል፦

﴿ قَالُوا۟ يَٰصَٰلِحُ قَدْ كُنتَ فِينَا مَرْجُوًّا قَبْلَ هَٰذَآ ۖ أَتَنْهَىٰنَآ أَن نَّعْبُدَ مَا يَعْبُدُ ءَابَآؤُنَا ﴾ هود: ٦٢

"ሷሊሕ ሆይ! ከዚህ ቀደም ከኛ ዘንድ ተስፋ የተጣለብህ ሰው ነበርክ። አባቶቻችን ያመልኩት የነበረውን እንዳናመልክ ትከለክለናለህን?" (ሁድ 62)

የኢብራሂም ወገኖችም እንዲህ ብለዋል፦

﴿ مَا هَٰذِهِ ٱلتَّمَاثِيلُ ٱلَّتِىٓ أَنتُمْ لَهَا عَٰكِفُونَ ﴿٥٢﴾ قَالُوا۟ وَجَدْنَآ ءَابَآءَنَا لَهَا عَٰبِدِينَ ﴿٥٣﴾ ﴾

الأنبياء: ٥٢ - ٥٣

«ለአባቱና ለወገኖቹ፦ "የምታመልኳቸው ቅርጻ ቅርጾች ምንድን ናቸው?" ባለጊዜ (የሆነውን አስታውስ)። "አባቶቻችን ሲያመልኳቸው አገኘን (እኛም እነርሱን ተከትለን እናመልካቸዋለን)።" አሉ።» (አል አንቢያእ 52-53)

የሹዓይብ ሕዝቦችም እንዲህ ብለዋል፦

﴿ أَصَلَوٰتُكَ تَأْمُرُكَ أَن نَّتْرُكَ مَا يَعْبُدُ ءَابَآؤُنَآ ﴾ هود: ٨٧

"(እነርሱም)፦ "ሹዐይብ ሆይ! አባቶቻችን ያመልኩት የነበረውን እንተው ዘንድ ወይም በገንዘቦቻችን የፈለግነውን እንዳናደርግ ሶላትህ ታዝሃለችን?" (ሁድ 87)

ይህ አጉል ልምድ በየዘመናቱ ስለመደጋገሙ ቁርአን ሲገልጽ፦

﴿ وَكَذَٰلِكَ مَآ أَرْسَلْنَا مِن قَبْلِكَ فِى قَرْيَةٍ مِّن نَّذِيرٍ إِلَّا قَالَ مُتْرَفُوهَآ إِنَّا وَجَدْنَآ ءَابَآءَنَا عَلَىٰٓ أُمَّةٍ وَإِنَّا عَلَىٰٓ ءَاثَٰرِهِم مُّقْتَدُونَ ﴿٢٣﴾ ﴾ الزخرف: ٢٣

"ብተመሳሳይ ሁኔታ፥ ከአንተ በፊት ወደ የትኛውም ሕዝብ አስፈራሪዎችን (ነቢያት) አልላክንም -ከመካከሉ ባለፀጋዎቹ- "አባቶቻችንን አንድን እምነት ሲከተሉ አገኘናቸው፣ ፈለጋቸውን ተከታዮች ነን።" ያሉ ቢሆን እንጅ።" (ዙኽሩፍ 23)

ቁርአን የአያት ቅድመ አያትን እምነትና አመለካከትን በጭፍኑ መከተልን ክፉኛ ኮንኗል፦

﴿ أَوَلَوْ كَانَ ءَابَآؤُهُمْ لَا يَعْقِلُونَ شَيْـًٔا وَلَا يَهْتَدُونَ ﴿١٧٠﴾ ﴾ البقرة: ١٧٠

"(ይህ አቋማቸው እጅግ የሚደንቅ ነው!) አባቶቻቸው ምንም ነገር የማያውቁና ቅኑን ጐዳናም ያልጨበጡ ቢሆኑም (እንኳ ይከተሏቸዋልን?)» (አል በቀራህ 170)

﴿ أَوَلَوْ كَانَ ءَابَآؤُهُمْ لَا يَعْلَمُونَ شَيْـًٔا وَلَا يَهْتَدُونَ ﴿١٠٤﴾ ﴾ المائدة: ١٠٤

"አባቶቻቸው ምንም ነገር የማያውቁና ቅኑን መንገድ የሳቱ ቢሆንም እንኳ (ሊከተሏቸው ነውን)?» (አል ማኢዳህ 104)

﴿ قَٰلَ أَوَلَوْ جِئْتُكُم بِأَهْدَىٰ مِمَّا وَجَدتُّمْ عَلَيْهِ ءَابَآءَكُمْ ۖ ﴾ الزخرف: ٢٤

"(ነቢያት ለሕዝቦቻቸው)፦ "ከአባቶቻችሁ ካገኛችሁት የተሻለ መመሪያ ባመጣላችሁ (አትከተሉኝምን?)" አሉ። (ዙኽሩፍ 24)

4) ባለፈው አየተቆጨ፣ ባመስጠው አየተበሳጨ የሚኖርም አለ። ይህን አድርጌ በነበር፣ ያኛውን በፊጸምኩ፣ ይህንን በተውኩ፣ ያኔ ይህን አድርጌ

Scanned by CamScanner

ቢሆን ኖሮ ይህ ይሆን ነበር። ይህን ባስቀድምና ያኛውን ባዘገይ ጥሩ ነበር ወዘተ እያለ ራስን በቁጭት የሚያውክም አለ።

ይህም ዓይነቱ አስተሳሰብና ስሜት ለውየወን በጣም ይጎዳል። ለስነ ልቦናዊ መጎሳቆል ይዳርጋል። ምክንያትና ፋይዳ አልባ በመሆኑ በምሬት ውስጥ እዲኖር ያደርገዋል። አውዳሚ የሆነ አሉታዊ ጫና አለው። ለዚህም ነው፡- «ባለፈው ጊዜ መጠመድ ተጨማሪ ጊዜ ለማባከን ጥፋት ይዳርጋል።» የተባለው።

ይህ በመሆኑ ቁርአንና ሱንና ይህን ዓይነቱን ባህሪ ተችተዋል። ሙስሊሞች በኡሁድ ዘመቻ ላይ ሽንፈት ከደረሰባቸው በኋላ ባለፈው እንዳያስቡና እንዳይቆጩ ቁርአን ሲመክር፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ لَا تَكُونُوا۟ كَٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ وَقَالُوا۟ لِإِخْوَٰنِهِمْ إِذَا ضَرَبُوا۟ فِى ٱلْأَرْضِ أَوْ كَانُوا۟ غُزًّى لَّوْ كَانُوا۟ عِندَنَا مَا مَاتُوا۟ وَمَا قُتِلُوا۟ لِيَجْعَلَ ٱللَّهُ ذَٰلِكَ حَسْرَةً فِى قُلُوبِهِمْ ۗ وَٱللَّهُ يُحْىِۦ وَيُمِيتُ ۗ وَٱللَّهُ بِمَا تَعْمَلُونَ بَصِيرٌ ﴿١٥٦﴾ ﴾ آل عمران: ١٥٦

«እናንተ ያመናችሁ ሆይ! እንደነዚያ ለወንድሞቻቸው ምድር ላይ በተጓዙና ውጊያ ላይ በተሳተፉ ጊዜ "ከኛ ዘንድ ቢኖሩ ኖሮ ባልሞቱም ባልተገደሉም ነበር።" እንዳሉት ከሓዲያን አትሁኑ። አላህ ከልቦናዎቻቸው ውስጥ ፀፀትን ሊያደርግ (አመለካከታቸው ይህ እንዲሆን ፈቀደ)። ሕይወትን የሚለግሰው፣ ለሞት የሚያበቃውም አላህ ብቻ ነው። አላህ የምትሠሩትን ሁሉ ተመልካች ነው።» (አሊ ዒምራን 156)

የአላህ መልእክተኛም እንዲህ ብለዋል፡-

«ጠንካራ ሙእሚን ከደካማ ሙእሚን ይበልጣል። ሁለቱም በጎዎች ቢሆኑም። ለሚጠቅም ነገር ጓጓ። በአላህ ታገዝ። አትሳነፍ። ይህን አድርጌ ቢሆን ኖሮ ይህ ይከሰት ነበር፣ አትበል። ግና፡-«አላህ የሚሻውን ወሰነ» በል። ምክንያቱም «እንዲህ ሆኖ ቢሆን» የሚለው ቃል የሰይጣንን ተግባር ይከፍታልና።» (ሙስሊም)

በቀደር ማመን እዚህ ላይ አወንታዊ ሚና ይጫወታል። ሰወየውን ከቁጭት ስቃይ አድኖ፣ ባለፈው ከመቆዘም ሰቆቃ አውጥቶ ለወደፊቱ እንዲሰራ ያነሳሳዋል።

መጭውን ዘመን አምላኪዎች

ከላይ ከተወሱት በተቃራኒ አቅጣጫ መጭውን ዘመን የሚያመልኩ፣ ላለፈው ጀርባቸውን የሰጡ፣ ከታሪካቸው የተነጣጠሉ፣ ለሕዝባቸው እና ለሰው ልጅ ታሪክ ቅንጣት ግምትና ትኩረት የማይሰጡ፣ ለባህላዊ፣ ሐይማኖታዊ እና ስልጣኔያዊ ቅርሶች ዋጋ እና ግምት የሌላቸው፣ እውነቱን ከሐሰቱ፣ ምርቱን ከገለባው ሳይለዩ ሙሉ በሙሉ ውድቅ የሚያደርጉ ወገኖችን እናገኛለን።

«ስለሞቱ አያቶቻችን ሊታውሱብን። የነርሱን ጉዳይ ተውን። ስለነገ አገር ተረካቢ ወጣቶቻችን፣ ስለ ልጆቻችን ብሎም ስለ ጽንሶቻችን እናስብ» ይላሉ።

«ለይኖቻችን የተፈጠሩት ከፊት እንጅ ከኋላ አይደለም። ስለዚህም ወደፊት እንጅ ወደ ኋላ ማየት ኢ-ተፈጥሯዊ ነው። ወደኋላ መዞር ወደ ፊት ላለመሮጥ እንቅፋት ዮሚሆን ሆኖ እያለ ለምን ወደ ኋላ እንድዝር ታስገድዱናላችሁ?» ይላሉም።

በእርግጥ ያለፈውን የሙጥኝ ብለው በትላንት እስር ቤት ወስጥ መኖር የሚሹትን፣ የዛሬ መብታቸውንና የነገ ግዴታቸውን ችላ የሚሉትን በተመለከተ ይህ አባባል እውነት ሊሆን ይችላል።

በሌላ በኩል ግን ትላንትን እንርሳ፣ ትምህርት ሰጭና ለነገ መነሻ የሚሆን አቅጣጫ አመላካች ታሪካዊ ውርሳችንን ትቢያ እናልብስ ማለት ከሆነ ትልቅ ስህተት ነው። አላህ ካለፉ ክስተቶች መጠቀምን በማስመልከት እንዲህ ብሏል፡-

﴿ أَفَلَمْ يَسِيرُوا۟ فِى ٱلْأَرْضِ فَتَكُونَ لَهُمْ قُلُوبٌ يَعْقِلُونَ بِهَآ أَوْ ءَاذَانٌ يَسْمَعُونَ بِهَا ۖ فَإِنَّهَا لَا تَعْمَى ٱلْأَبْصَٰرُ وَلَٰكِن تَعْمَى ٱلْقُلُوبُ ٱلَّتِى فِى ٱلصُّدُورِ ﴿٤٦﴾ ﴾ الحج: ٤٦

«የሚያስተውሉበት ልቦና፣ የሚሰሙበትም ጆሮ ይኖራቸው ዘንድ በምድር ላይ አይጓዙምን? እነሆ ዓይኖች አይታውሩም። የሚታወሩት በደረቶች ውስጥ ያሉት ልቦች ናቸው።» (አል ሐጅ 46)

መጭውን ዘመን በጥቁር መነጽር መመልከት

ስለ ነገ ጥሩ ስሜት የሌላቸው ወገኖች አሉ። ከአይናቸው ላይ ጥቁር መነጽር አጥልቀው በርሱ ሕይወትን፣ ጊዜን፣ ቦታንና ፍጡራንን ሁሉ

Scanned by CamScanner

ይመለከቱበታል። እይታቸው ጸለምተኛ ነው። ተስፋ የቆረጡ ናቸው። በነገ አይተማመኑም። የስኬት ተስፋ አጥተዋል። ትላንት ከዛሬ ይሻላል፤ ነገ ይበልጥ ይከፋል የሚል እምነት አላቸው። ሕይወትን የማትነጋ ሌሊት፣ ጸሐይ የማይወጣባት ጽልመት አድርገው ያስቧታል።

ይህ በእርግጥም አውዳሚ አመለካከት ነው። በመጀመሪያ ሰውየውን ያወድማል። ቀጥሎ ሕይወትንና ማሕበረሰቡን ያወድማል።

የተስፋ ብርሃን ከሌለ የግለሰብ ሕይወት ይጨልማል። ከመርፌ ቀዳዳም ይጠባል።

የማሕበረሰቡ ሕይወትም ያለ ተስፋ ነፍስ የሌለው አካል፣ የማይንቀሳቀስ በድን ይሆናል። ሕንጻ ና ግንባታ አይኖርም። ምርት አይታሰብም። እድገትና ስልጣኔ፣ ወደፊት ግስጋሴ አይሞከርም።

ሐይማኖትም፣ ታሪክም ተጨባጭ እንደሚያስተምሩን ሕይወት ከተስፋ መቁረጥ ጋር ትርጉም የለውም። ተስፋ መቁረጥም ከሕይወት ጋር ትርጉም የለውም። ከመከራ ጋር ደስታ አለ። ሌሊት መንጋቱ አይቀርም። የማይቀየር ምንም ነገር የለም። አላህ እንዲህ ብሏል፦

﴿ إِنَّهُۥ لَا يَاْيَـْٔسُ مِن رَّوْحِ ٱللَّهِ إِلَّا ٱلْقَوْمُ ٱلْكَـٰفِرُونَ ﴿٨٧﴾ ﴾ يوسف: ٨٧

"ከአላህ እዝነት ተስፋ የሚቆርጡት ከሓዲዎች ብቻ ናቸው።" (ሶላቸውም)።. (ዩሱፍ 87)

﴿ وَمَن يَقْنَطُ مِن رَّحْمَةِ رَبِّهِۦٓ إِلَّا ٱلضَّآلُّونَ ﴿٥٦﴾ ﴾ الحجر: ٥٦

"ከጌታው እዝነት፥ ጠማሞች እንጅ ሌላ ማን ተስፋ ይቆርጣል?"። (ሂጅር 56)

በርካታ ሰዎች እንዲህ ያስባሉ፦ «እኛ የምንገኘው በመጨረሻው ዘመን (አኺሩ ዘማን) ላይ ነው። የቂያማ ምልክቶች መታየት ጀምረዋል። በጎ ነገር ዓለምን እየተሰናበተ፣ ክፋትም እየነገሰ ነው። ሐይማኖት (ዲን) ከቀን ቀን ብርሃኑ እየከሰመ፣ ክህደት (ኩፍር) ጉልበት እያገኘና ምድርን እየተቆጣጠረ መሄዱ፣ በመጨረሻም አንድም ሙስሊም የማይቀርበት ሁኔታ መፈጠሩ አይቀሬ ነው። ስለዚህም የተበላሸውን ለማስተካከል፣ የጠመመውን ለማቅናት የሚደረግ ጥረት ሁሉ ከንቱ ድካም ነው።»

ይህ አስተሳሰብ በእርግጥም የተስፋ መቁረጥ አንዱ መገለጫ ነው። ለዚህ ጸለምተኛና ተስፋ አልባ አስተሳሰባቸውም ስለ ቂያማ ምልክቶችና ፈተናዎች የተጠቀሱ የቁርአን እና የሐዲስ መልእክቶችን በአስረጅነት ይጠቀሳሉ።

በእርግጥ እውነታው እነዚህ ወገኖች በግልብ ግንዛቤያቸው እንደተረዱት አይደለም። ቂያማ መቃረቡንና ምልክቶቹ መታየታቸውን የሚገልጹ የቁርአንና የሐዲስ መልእክቶች፦ «ቂያማ አሁን ከበር ላይ ነው፤ ከቅጽበት በኋላ ይከሰታል።» ማለታቸው አይደለም።ምክንያቱም መቅረብና መራቅ አንጻራዊ ነገሮች ናቸው። በኛና በቂያማ መካከል አላህ እንጅ ቁጥራቸውን ማንም የማያውቃቸው ሺዎች አመታት ቀርተው ሊሆን ይችላል። የምናውቀው ነገር የለም። ምን አልባትም ከምናስበው በላይም ቅርብ ልትሆን ትችላለች።

ቁርአን ስለ ትንሳኤ ከሚከተለው መልእክት በላይ አላከለም፦

﴿ لَعَلَّ ٱلسَّاعَةَ تَكُونُ قَرِيبًا ﴿٦٣﴾ ﴾ الأحزاب: ٦٣

«ምናልባትም ሰዓቷ ቅርብ እንደሆነች ምን የምታውቀው ነገር አለ?» (አል አህዛብ 63)

﴿ لَعَلَّ ٱلسَّاعَةَ قَرِيبٌ ﴿١٧﴾ ﴾ الشورى: ١٧

«ምናልባትም ሰዓቷ (ትንሳኤ) ቅርብ እንደሆነች ምን የምታውቀው ነገር አለ?» (አል ሹራ 17)

﴿ لَا يُجَلِّيهَا لِوَقْتِهَآ إِلَّا هُوَ ﴾ الأعراف: ١٨٧

«የምትከሰትባቸው በድንገት ነው።»(አል አዕራፍ 187)

የነቢዩ ሙሐመድ (ሰዐወ) መላክ ራሱ የቂያማ ምልክት ነው። እርሳቸውም፦

«እኔና ትንሳኤ እንደነዚህ ጣቶቼ የተቀራረብን ሆነን ተላክሁ» በማለት ሌባ እና መካከለኛ ጣታቸውን አቀራርበው አሳይተዋል። (ቡኻሪና ሙስሊም)

በመጨረሻው ዘመን ላይ ነን በሚል ሰበብ ቂያማን እየተጠባበቁ የእስልምናን ሸሪዓ ሕያው ከማድረግ፣ ሕዝበ ሙስሊሙን ከመታደግ፣

Scanned by CamScanner

ኢስላማዊ መንግስት ከማነጽ መዘናጋት እስልምና ክፉኛ የሚነቅፈው ተግባር ነው። ሙስሊም እስከ መጨረሻው የሕይወት እስትንፋሱ ድረስ እንዲሰራና እንዲታገል ታዟል።

ሕዝበ ሙስሊሙም እንዲሁ ይህው ትእዛዝ ይመለከተዋል። በዚህች ዓለም የመጨረሻ ቀናት የተውባህ በር እስኪዘጋ፣ አላህ ለዚህች ዓለም ሕይወት የዘረጋቸው ስርዓቶች እስኪፋለሱና ጸሐይ በመግቢያዋ እስክ ትወጣ ድረስ መሥራት የግድ ነው። በእርግጥ እነዚህ ክስተቶች ከታዩ በኋላ ተውባ ላይኖር ይችላል:-

﴿ يَوْمَ يَأْتِي بَعْضُ ءَايَٰتِ رَبِّكَ لَا يَنفَعُ نَفْسًا إِيمَٰنُهَا لَمْ تَكُنْ ءَامَنَتْ مِن قَبْلُ أَوْ كَسَبَتْ فِيٓ إِيمَٰنِهَا خَيْرًا ﴾ الأنعام: ١٥٨

«ከጌታህ ተአምራት ከፊሉ በመጣ ጊዜ ከዚያ በፊት ያላመነች ወይም በእምነቷ በጉ ተግባር ያልፈፀመች ነፍስ እምነቷ ቅንጣት አይፈይዳትም።» (አል አንዓም 158)

የአላህ መልእክተኛ ዱንያዊ ስራን- ምንም እንኳ በዲን እይታ አናሳ ዋጋ የሚሰጠው ቢሆንም- እስከመጨረሻ የሕይወት እስትንፋስ ድረስ መስራትን አዘዋል። እንዲህ ብለዋል:-

«ከናንተ አንዳችሁ ችግኝ የያዘ ሆኖ ቂያማ ብትቆም እስኪተክላት ድረስ ጊዜ የሚያገኝ ከሆነ ይትከላት።» (አህመድ)

ቂያማ ልትቆም ቅጽበት በቀራት ሰአት በእጁ የያዛትን ችግኝ- ማንም ሊጠቀምባት እንደማይችል ቢያወቅ እንኳ- እንዲተክላት ከታዘዘ በኛና በቂያማ መካከል ከአላህ ውጭ ሌላ የማያውቀው ረዥም ዘመን መኖሩ እየታወቀ ከበጎ ስራ መዘናጋት ፍጹም ስህተት ይሆናል።

ስራ በራሱ ተፈላጊ ነው። ፍሬው ፈጥኖ ባይታይም። አንድ ሰው የስራውን ፍሬ ካገኘ ሁለት መልካም እድሎችን ተጎናጸፈ። ውጤት ባያይም ግን መስራቱ፣ ጥረት ማድረጉ፣ ግዴታውን መወጣቱ በራሱ በቂ ነው። በዚህ ረገድ ጥቂት ሐዲሶችን ቀጥሎ አወሳለሁ:-

1) አሲ ቢን አቢ ጧሊብን በመጥቀስ ቲርሚዚ እንደዘገቡት የአላህ መልእክተኛ (ሰዐወ):-

«ከኔ (ሕልፈት) በኋላ እንደ ጸለምተኛ ሌሊት ቁራጭ የሆኑ ፈተናዎች ይመጣሉ።።» በማለት ተናገሩ። «የአላህ መልእክተኛ ሆይ፣ መዳኛው ምንድን ነው?» አልኪቸው። «የአላህ መጽሐፍ ነው። ከናንተ በፊት የነበሩና ከናንተ በኋላም የሚመጡ ሕዝቦች ታሪክ፣ እንዲሁም አናንተ ያላችሁበት ዘመን መመሪያ ከርሱ (ከቁርአን) ውስጥ ይገኛል።» አሉ።

2) መልእክተኛው እንዲህ ብለዋል:- «ለበጎ ስራ ተሽቀዳደሙ። እንደ ጸለምተኛ ሌሊት ቁራጭ የሆኑ ፈተናዎች ይከሰታሉ። ሰውየው አማኝ ሆኖ አንግቶ ከሐዲ ሆኖ ያመሻል። አማኝ ሆኖ አምሽቶ ከሐዲ ሆኖ ያነጋል። ዲኑን በዱንያዊ ሽቀጥ ይለውጣል።» (ሙስሊም)

3) አቢ ሰአለበት አልኹሽኒን በመጥቀስ አቡ ዳውድ፣ ቲርሚዚና ቢን ማጃህ እንደዘገቡት የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል:-

«ከናንተ በኋላ የትእግስት ቀናት ይመጣሉ። በነዚህ ቀናት ውስጥ መታገስ ፍም የመጨበጥ ያህል ነው። በነርሱ ውስጥ በጎ የሚሰራ ሰው የመሰሎቹን ሐምሳ ሰዎች ምንዳ ያገኛል።»

«የአላህ መልእክተኛ ሆይ፣ ከነርሱ ውስጥ የአምሳ ሰዎችን ምንዳ ማለትዎ ነውን?» በማለት ጠየቅኳቸው «ከናንተ ወስጥ የሐምሳ ሰዎችን ምንዳ ማለቴ ነው።»ሲሉ መለሱልኝ።

4) ቡኻሪና ሙስሊም እንደዘገቡት ሁዘይፋ ቢን አልየማን እንዲህ በማለት አውግተዋል:-

ሰዎች የአላህን መልእክተኛ ስለ በጎ ነገሮች ሲጠይቁ፣ እኔ ግን ስለክፉ ነገሮች እጠይቃቸው ነበር። ይህን የማደርገው ክፉ እንዳያገኘኝ በመስጋት ነው። «የአላህ መልእክተኛ ሆይ፣ እኛ በመሐይምነት እና በክፋት ውስጥ ነበርን። አላህ ይህን በጎ ነገር ለገሰን። ከዚህ በኋላ ክፉ ነገር ይመጣብናልን?»ስል ጠየቅኳቸው። «አዎ» አሉ። «ከዚያ ክፋት በኋላ ደግ ነገር ይመጣልን?» አልኳቸው። «አዎ፣ ግና ጭጋግ አለበት።» አሉ። «ጭጋጉ ምንድን ነው?»አልኳቸው። «የኔን ፈለግ የማይከተሉ፣ መመሪያየን የማያከብሩ፣ የምትደግፈውንም የምትቃወመውንም ተግባር የሚፈጽሙ ሰዎች ናቸው።» አሉ። «ከዚህ በጎ በኋላ ሌላ ክፋት ይመጣልን?» አልኳቸው። «አዎ፣ ከጀሃነም በር ላይ ሆነው የሚጣሩ ሰዎች ይመጣሉ። ጥሪያቸውን የተቀበለ ወደ ጀሃነም ይወረውሩታል።»

Scanned by CamScanner

አሉ:: «ባህሪያቸውን ይንገሩኝ» አልኳቸው:: «የኛው ወገን የሆኑና ቋንቋችንን የሚናገሩ ሰዎች ናቸው::»አሉኝ::

ከላይ የተወሱ ሐዲሶች ክፋትን እንድንጠነቀቅ፣ በበጎ ነገር እንድንበረታ፣ በሐቅ ላይ እንድንጸና፣ የአላህን ኪታብ አጥብቀን እንድንይዝ፣ አላህን በመታዘዝና በአንድነት ገመድ እንድንተሳሰር፣ ከገሐነም ደጅ ላይ ቆመው ወደ ክፋት የሚጣሩትንና ጥሪያቸውን የሰማውን ወደርሷ የማወረውሩትን ወገኖች እንድንቃወም ከማስተማር የዘለለ መልእክት የላቸውም::

ሕልምና ምኞት

መጭውን ዘመን በተስፋ መቁረጥ አይን ከሚመለከተው ከዚህ ጸለምተኛ እይታ በተቃራኒ፣ በእውቀት፣ በተግባርና በእቅድ ሳይሆን እንዲሁ በባዶ ሕልም የሚጠብቁት ወገኖችን እናገኛለን::

ምኞት ክብርን አያገኝም:: ተስፋን እውን አያደርግም:: እንዲያውም ከእብ ቢን ዙሂር እንዳለው «ሕልሞችና ምኞቶች ያቄላሉ::»

አንድ ሰው ለኢብን ሲሪን:- «በሕልሜ ከየብስ ላይ ስዋኝና ያለ ክንፍ ስበር አየሁ:: ፍቹ ምንድን ነው?» በማለት ጠየቃቸው:: «ሕልምና ምኞት የምታበዛ ሰው ነህ» አሉት::

አሊ ቢን አቢ ጧሊብ ልጃቸውን እንዲህ ሲሉ መክረዋል:-

«የባዶ ምኞት ተገዥ አትሁን:: ባዶ ምኞት የቂሎች ሐብት ነውና::»

ለዚህም ነው የእምነትና የበጎ ተግባር ሰበቦችን ሳይዙ ጀነት እንደሚገቡ ይመኙና ያልሙ የነበሩ አይሁዶችንና ክርስትያኖችን ቁርአን ክፉኛ የነቀፈው:-

﴿ وَقَالُوا۟ لَن يَدْخُلَ ٱلْجَنَّةَ إِلَّا مَن كَانَ هُودًا أَوْ نَصَٰرَىٰ ۗ تِلْكَ أَمَانِيُّهُمْ ۗ قُلْ هَاتُوا۟ بُرْهَٰنَكُمْ إِن كُنتُمْ صَٰدِقِينَ ﴿١١١﴾ بَلَىٰ مَنْ أَسْلَمَ وَجْهَهُۥ لِلَّهِ وَهُوَ مُحْسِنٌ فَلَهُۥٓ أَجْرُهُۥ عِندَ رَبِّهِۦ وَلَا خَوْفٌ عَلَيْهِمْ وَلَا هُمْ يَحْزَنُونَ ﴿١١٢﴾ ﴾

"አይሁድ ወይም ክርስቲያን ካልሆነ በቀር ማንም ጀንነት አይገባም::" አሉም፣ ይህ የነርሱ (ከንቱ) ምኞት ነው:: (ሙሐመድ ሆይ!):- "(ለምትሉት ነገር) እውነተኞች ከሆናችሁ ማስረጃችሁን አምጡ" በላቸው:: አዎ! ለአላህ ሙሉ እሱነቱን ያስረከበ (በፍፁም ታዛዥነት የፀና

-የሰለመ) እና ፅድቅ ተግባራትን የሚሠራ ለርሱ ከጌታው ዘንድ (የበጐ ሥራው) ምንዳ አለው:: (እንዲህ ዓይነቶቹ ጻድቃን ሰዎች) ፍርሃትም፣ ሐዘንም የለባቸውም፣ (ዘልዓለማዊ ፀጋን ይቸራሉ፣ ገነትን ይጎናፀፋሉ)::" (አል በቀራህ 111-112)

ቁርአን የመጽሐፉ ባለቤቶችን ብቻ ሳይሆን ሙስሊም መሰኘት ወይም በሙስሊም ስም መጠራት ብቻውን ጀነት ያስገባናል የሚል ሕልም ያላቸውን ሙስሊሞችም ተችቷል:-

﴿ لَّيْسَ بِأَمَانِيِّكُمْ وَلَآ أَمَانِىِّ أَهْلِ ٱلْكِتَٰبِ ۗ مَن يَعْمَلْ سُوٓءًا يُجْزَ بِهِۦ وَلَا يَجِدْ لَهُۥ مِن دُونِ ٱللَّهِ وَلِيًّا وَلَا نَصِيرًا ﴿١٢٣﴾ وَمَن يَعْمَلْ مِنَ ٱلصَّٰلِحَٰتِ مِن ذَكَرٍ أَوْ أُنثَىٰ وَهُوَ مُؤْمِنٌ فَأُو۟لَٰٓئِكَ يَدْخُلُونَ ٱلْجَنَّةَ وَلَا يُظْلَمُونَ نَقِيرًا ﴿١٢٤﴾ ﴾

«(የአላህ የተስፋ ቃል) በእናንተም በመጽሐፉ ባለቤቶችም ምኞት (ብቻ) የሚገኝ አይደለም:: ክፉን የሠራ የሥራውን ዋጋ ያገኛል:: ከአላህ ውጭ (ከቅጣት) ጠባቂና ረዳት አያገኝም:: ከሴትም ከወንድም አማኝ ሆነው መልካም ሥራዎችን የሚሠሩ በእርግጥም ገነትን ይገባሉ:: ቅንጣት ያህልም በደል አይደርስባቸውም::» (አል ኒሣእ 123-124)

ቁርአን የተቸው ባዶ ምኞትን እንጅ ተስፋን አይደለም:: በነዚህ በሁለቱ መካከል ትልቅ ልዩነት አለ:: ተስፋ ማለት ተግባር የተቆራኘው ነው:: ተግባር ሳይኖርበት ሲቀር ከንቱ ምኞት ይሆናል::

የአላህን ይቅር ባይነት፣ ምህረትና የእዝነቱን ስፋት ተማምኖ የነፍስያን ፍላጎት ማስተናገድ፣ ስጋዊ ስሜትን ተከትሎ መንጎድ በሐዲስ የተወገዘውም ለዚሁ ነው:: አላህ እንዲህ ማለቱን መዘንጋት ተገቢ አይደለም:-

﴿ إِنَّ رَحْمَتَ ٱللَّهِ قَرِيبٌ مِّنَ ٱلْمُحْسِنِينَ ﴿٥٦﴾ ﴾ الأعراف: ٥٦

«የአላህ እዝነት (እና ችሮታ) ለመልካም ሠራዎች እጅግ ቅርብ ነውና::» (አል አዕራፍ 56)

﴿ وَرَحْمَتِى وَسِعَتْ كُلَّ شَىْءٍ ۚ فَسَأَكْتُبُهَا لِلَّذِينَ يَتَّقُونَ وَيُؤْتُونَ ٱلزَّكَوٰةَ وَٱلَّذِينَ هُم بِـَٔايَٰتِنَا يُؤْمِنُونَ ﴿١٥٦﴾ ﴾ الأعراف: ١٥٦

"ግና እዝነቴ ሁሉንም ነገር ያካትታል:: ለነዚያ ጌታቸውን ለሚፈሩትና ዘካንም ለሚሰጡት፣ ለነዚያም በአንቀጾቻችን ለሚያምኑት አውለዋለሁ::" አለ:: (አል አዕራፍ 156)

Scanned by CamScanner

የአላህ እገዛትና ችሮታ ቅርብ የሆነው፣ የተጻፈው ለበጎ ሰሪዎች፣ እርሱን ለሚፈሩና መልካም ስራዎችን ለሚሰሩ ሰዎች መሆኑ በጉልህ ተመልክቷል። በዚህ ረገድ የተነገረው ሐዲስ የሚከተለው ነው፡-

«ብልህ ማለት ነፍሱን የተቆጣጠረና ከሞት በኋላ ላለ ሕይወቱ የሚሰራ ሲሆን፣ ሰነፍ ማለት ስጋዊ ስሜቱን የሚከተል እና በአላህ ላይ ከንቱ ምኞት ያደረበት ነው።» (ቲርሚዚ፣ አህመድና ቢን ማጃህ)

በአንጻሩ ተስፋን ቁርአን አጽድቋል። ባለቤቶቹንም አሞግሷል፡-

﴿ إِنَّ ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ وَٱلَّذِينَ هَاجَرُوا۟ وَجَٰهَدُوا۟ فِى سَبِيلِ ٱللَّهِ أُو۟لَٰٓئِكَ يَرْجُونَ رَحْمَتَ ٱللَّهِ ۚ وَٱللَّهُ غَفُورٌ رَّحِيمٌ ﴿٢١٨﴾ ﴾ البقرة: ٢١٨

«እነዚያ ያመኑት፣ እነዚያም የተሰደዱትና በአላህ መንገድ የታገሉት የአላህን እዝነት የመጉናዐፍ ተስፋ ያላቸው እነርሱ ናቸው። አላህ እጅግ መሓሪና አዛኝ ነው።» (አል በቀራህ 218)

አንድ በጎ ሰው እንዲህ ብለዋል፡- «ጀነትን ያለ ስራ መከጀል ወንጀል ነው። ሱንናን ሳይከተሉ የነቢዩን አማላጅነት መመኘት ቂልነት ነው። ወንጀል እየሰሩ የአላህን እዝነት መሻት ሞኝነትና መሐይምነት ነው።»

አልሐሰን እንዲህ ብለዋል፡-

«አንዳንድ ሰዎች ምህረት የማግኘት ከንቱ ምኞት አቂላቸውና ያለ በጎ ስራ ይህችን ዓለም ይሰናበታሉ። «አምላኬን በበጎ እጠረጥረዋለሁ።» ሲሉም ይደመጣሉ። ውሸታቸውን ነው። በበጎ ቢጠረጥሩት ኖሮ በጎ ስራ በሰሩ ነበር።»

ይህን ካሉ በኋላ ተከታዩን የቁርአን መልእክት አነበቡ፡-

﴿ وَذَٰلِكُمْ ظَنُّكُمُ ٱلَّذِى ظَنَنتُم بِرَبِّكُمْ أَرْدَىٰكُمْ فَأَصْبَحْتُم مِّنَ ٱلْخَٰسِرِينَ ﴿٢٣﴾ ﴾ فصلت ٢٣

"ባጌታችሁ ላይ የነበራችሁ ይህ ግምታችሁ ለጥፋት ዳረጋችሁ። በመሆኑም ከኛሪዎች ሆናችሁ።" (ይሏቸዋልም)። (ፉሲለት 23)

«ሰዎች ሆይ፣ ከከንቱ ምኞት ታቀቡ። ምክንያቱም እርሷ የረዘመች ሸለቆ ስትሆን ባለቤቶቿ ከርሷ ዘንድ ያርፋሉ። በአላህ እምላለሁ፣ በከንቱ ምኞቱ በዚህችም ሆነ በመጭው ዓለም በጎ ነገር የሚያገኝ ሰው የለም።»

ዛሬን አፍቃሪዎች

ትላንትን የሚያዩ፣ ስለነገ ደንታ የሌላቸውና ዛሬን ብቻ መኖር የሚሹ ሰዎችም አሉ። ለነርሱ ትላንት አልፏል። ያለፈ ደግሞ የሞተ ነው። በሞተ ነገር መጠመድም ተገቢ አይደለም።

ነገ እውን ያልሆነ ነው። እውን ባልሆነ ነገር መጠመድም የአስተዋዮች ባህሪ አይደለም። ከአሸዋ ላይ መገንብት፣ ከአየር ላይ መጻፍ ይሰኖናል።

እነዚህ ወገኖች በዛሬ መጠመዳቸው ነገን ከግምትና ከትላንት ከመማር አዘናግቷቸዋል። የአሁን ብቻ ልጆች ናቸው። ሌላ ነገር አያሳስባቸውም። ስለ ነገ በማሰብ የዱቤ ሽያጭ አይፈጽሙም። ዛሬን በነገ ለመለወጥ አይፈቅዱም። ባለፈ ታሪክና ውርስ መጨነቅም አይሹም። ምክንያቱም አልፏል። የዛሬ ልጆች ናቸው ማለት ስለ አሁኗ ቅጽበት አንጅ አይጨነቁም ማለት ነው።ዛሬን ይደሰቱባታል። ይጠቀሙባታል። ራሳቸውን በትላንት ሐሳብና በነገ ምኞት ሳያውኩ በደስታ ባህር የቻሉትን ያህል ይሰጥማሉ። አንድ ገጣሚ፣ እንዳለው፡-

ያለፈው የሞተ ክስተት
ነገ የሚመጣ ምኞት
ሐብትህ የአሁኗ ሰአት

በእርግጥ ይህ አባባል ለአማኞችም ለአምላክ የሰሞችም ሊሰራ ይችላል። በአማኝ እሳቤ መሠረት ያለችው ጊዜ አሁን ናት። ስለዚህም አያባክናትም። አላህን ለማምለክ ተግባር ያውላታል። ሐቅን ይረዳባታል። በጎ ይሰራባታል። መልካምን ነገር ያስፋፋባታል። አንድ ሙን የአላህ ባሪያ ከላይ የተጠቀሰውን ግጥም ራሱን እንደተቀኙ ተገልጿል።

ዛሬ የምንለው ነገር በትላንትና በነገ መካከል የሚገኝ የሐሳብ መስመር ነው። ለዚህም ነው አንድ ገጣሚ እንዲህ ያሉው፡-

«ጊዜ ሁለት ነው። ያለፈውን ማስተንተንና ስለመጭው ማሰብ።»

ይህ ገጣሚ የአሁንን ለሊት ከለሊቱ ውጭ አድርጉታል።

◆ ◆ ◆

Scanned by CamScanner

ለጊዜ ትክክለኛው እይታ

ስለ ጊዜ ትክክለኛው እይታ ሦስቱንም ክፍሎቹን ማለትም ያለፈውን፣ ዛሬን እና መጭውን ባንድ አካቶ የያዘው ነው፡፡

ትላንትን ከስሌት ውስጥ ማስገባት

ትላንት የክስተቶች ማቋቻ ነው፡፡ በርሱ ውስጥ ከሆኑ ነገሮች፣ ሕዝቦች ከገጠማቸው ፍጻሜና በነርሱ ላይ ከተፈጸመው የአላህ ሕግ ትምህርት ይቀሰማል፡፡ አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ قَدْ خَلَتْ مِن قَبْلِكُمْ سُنَنٌ فَسِيرُوا فِي الْأَرْضِ فَانظُرُوا كَيْفَ كَانَ عَاقِبَةُ الْمُكَذِّبِينَ ﴿١٣٧﴾ ﴾ آل عمران: ١٣٧

«ከናንተ በፊት (ለትምህርት ሰጭነት የሚበቁ በርካታ) ክስተቶች አልፈዋል፡፡ በምድር ላይ ተጓዙ፣ የአስተባባዮች ፍጻሜ እንዴት እንደ ነበር ተመልከቱም፡፡» (አሊ ዒምራን 137)

﴿ إِن يَمْسَسْكُمْ قَرْحٌ فَقَدْ مَسَّ الْقَوْمَ قَرْحٌ مِّثْلُهُ ۚ وَتِلْكَ الْأَيَّامُ نُدَاوِلُهَا بَيْنَ النَّاسِ وَلِيَعْلَمَ اللَّهُ الَّذِينَ آمَنُوا وَيَتَّخِذَ مِنكُمْ شُهَدَاءَ ۗ وَاللَّهُ لَا يُحِبُّ الظَّالِمِينَ ﴿١٤٠﴾ ﴾

آل عمران: ١٤٠

«ጉዳት ቢደርስባችሁም (ሌሎች) ሕዝቦችም ተመሳሳይ ጉዳት ደርሶባቸዋል፡፡ እንዲህ ዓይነቶችን ቀናት በሰዎች ላይ እናፈራርቃለን፡፡ አላህ እነዚያን ያመኑትን ለማወቅና ከናንተ መካከልም ሰማእታትን ለመያዝ (እንዲህ ዓይነት ቀናት እንዲፈራረቁ ያደርጋል)፡፡ አላህ በደለኞችን አይወድም፡፡» (አሊ ዒምራን 140)

﴿ وَكَأَيِّن مِّن نَّبِيٍّ قَاتَلَ مَعَهُ رِبِّيُّونَ كَثِيرٌ فَمَا وَهَنُوا لِمَا أَصَابَهُمْ فِي سَبِيلِ اللَّهِ وَمَا ضَعُفُوا وَمَا اسْتَكَانُوا ۗ وَاللَّهُ يُحِبُّ الصَّابِرِينَ ﴿١٤٦﴾ ﴾ آل عمران: ١٤٦

«ብዙ ቅንና አዋቂ ሰዎች አብረዋቸው የተዋጉ ነቢያት አያሌ ናቸው፡፡ በአላህ መንገድ ላገኛቸው (ችግርና መከራ) እጅ አልሰጡም፣ አልደከሙም፣ (ለጠላቶቻቸውም) አልተገበረከኩም፡፡ አላህ ታጋሾችን ይወዳል፡፡» (አሊ ዒምራን 146)

﴿ أَفَلَمْ يَسِيرُوا فِي الْأَرْضِ فَتَكُونَ لَهُمْ قُلُوبٌ يَعْقِلُونَ بِهَا أَوْ آذَانٌ يَسْمَعُونَ بِهَا ۖ فَإِنَّهَا لَا تَعْمَى الْأَبْصَارُ وَلَٰكِن تَعْمَى الْقُلُوبُ الَّتِي فِي الصُّدُورِ ﴿٤٦﴾ ﴾ الحج: ٤٦

«የሚያስተውሉበት ልቦና፣ የሚሰሙበትም ጆር ይኖራቸው ዘንድ በምድር ላይ አይጓዙምን? እነሆ ዓይኖች አይታውሩም፣ የሚታውሩት በደረቶች ውስጥ ያሉት ልቦች ናቸው፡፡» (አል ሐጅ 46)

የጥንት ሰዎች ትተውልን ያለፉትን የሳይንስ፣ የስነ ጽሑፍና የኢኮኖሚ ውርስ ከፈተሽንና ለዘመናችን የሚበጁንን ከለየን በኋላ መጠቀም የግድ ነው፡፡ በሐዲስ የሚከተለው ተነግሯል፡-

«ጥበብ የሙእሚን የጠፋች ንብረቱ ናት፡፡ የትም ቢያገኛት ለርሱ ትገባዋለች፡፡» (ቲርሚዚና ቢን ማጃህ)

አንድን ነገር የጥንት ስለሆነ ብቻ ችላ ማለት አግባብ አይደለም፡ የጥንትነቱ ለርሱ ውበትና ልዩ ባህሪ የሚሆንለት፣ በባህሪው መቀደስ የማይመቸው ብዙ ነገር አለ፡፡ የቁርአን ውበቱና ታላቅነቱ ጽኒኤ ብዙት የማያረጅና የማይወይብ የጥንት የአላህ ቃል መሆኑ አይደለምን?

ካዕባ ልቅናው ሰዎች ከጥንት ዘመን ይዞ የሚጎበኙት የጥንት ቤት መሆኑ አይደለምን?

ቁርአን አይታደስም፡፡ ካእባ አይታደስም፡፡ እውነታዎች አይታደስም፡፡ የተሐድሶ አቀንቃኞች የጥንት ነገሮችን ሁሉ ችላ ብለው ለአዲስ ነገሮች ሁሉ በማጨብጨባቸው ስህተት ፈጽመዋል፡፡ ምክንያቱም ከጥንት ነገሮች ውስጥ በጣም የሚጠቅም፣ ከአዲሶች ውስጥም ከጣም የሚጎዳ ነገር አለና፡፡ የዓረባዊና የኢስላማዊ ስነ ጽሁፎች ሊቅ የሆነው መስጦፋ ሲዲቅ ሪፋኢ በነዚህ ወገኖች ላይ እንዲህ ሲል ተሳልቀል፡-

«ሐይማኖትን፣ ቋንቋን፣ ጼሐይንና ጨረቃን ባይቀር ሲያድሱ ይከጅላሉ፡፡»

የገጣሚዎች ንጉስ ሸውቂ «አዝሐር» በተሰኘ ግጥሙ እንዲህ ሲል ተችቷቸዋል፡-

የጥንቱን ሁሉ የሚነቅፉ ወገኖችን ፈለግ አትስቀል፣

ቢችሉ የሞቱ አባቶቻቸውን ቢኩፍ ይመኛሉ፣

የጥንቱን ለማፍረስ ይቻኮላሉ፣

Scanned by CamScanner

አዲስ ለመገንባት ግን አቅም የላቸውም።

በተጨማሪም አዲስነት እና የጥንትነት አንጻራዊ ነገሮች ናቸው። ለአንዱ የጥንት የሆነው ለሌላው አዲስ ሊሆንለት ይችላል። በአንድ አካባቢ የጥንት የተሰኘው ለሌላ አካባቢ አዲስ ሊሆን ይችላል። አዲስ ሁሌም አዲስ እንደሆነ አይኖርም።የዛሬ አሮጌ የትላንት አዲስ ነበር። የዛሬ አዲስ የነገ አሮጌ ነው።

እያንዳንዱ ቀን ካለፈ በኋላ አፈጻጸሙን መመርመር፣ በተለይም በአንቅልፍ ለአት ዛሬ ምን ሰራሁ? ምን ተውኩ? ለምን አልሰራሁትም? ወዘተ እያሉ መመርመር የእያንዳንዱ ሙስሊም የእለት ተግባር አካል ሊሆን ይገባል።

ሰውየው ራሱን የሚመረምርባት ቅጽበት ከፍተኛ ምጥቀት ያገኘባት አለት ተደርጋ ትቆጠራለች። ምክንያቱም አእምሮ ስጋዊ ፍላጎትን፣ ሕሊና ከንቱ ስሜትን (ሽሕዋን) የሚዳኙባት ቅጽበት ናትና። ሙእሚን በዚህች ቅጽበት እምነቱን ጠባቂ ፖሊስ እና መርማሪ እንደዚሁም ዳኛ ያደርጋል። በመሆኑም «በክፉ ከምታዝ ነፍስ» «ራሷን ወደ ምትተች ነፍስ» ይመጥቃል። ወቃሽ ነፍስ ሰውየውን መጥፎ ሲሰራና ግዴታውን ሳይወጣ ሲቀር ትተቸዋለች።

ከዚህ ቀደም ባወሳነው ሐዲስ ውስጥ እንዲህ የሚል ተዘክሯል፡-

«አእምሮ ያለው ሰው አራት ወቅቶች ሊኖሩት ይገባል። ከነርሱም ውስጥ ራሱን የሚመረምርበት ወቅት አንዱ ነው።»

አሚረል ሙእሚኒን ዑመር ቢን አልኸጣብ እንዲህ ብለዋል፡-

«ሳትመረመሩ በፊት ራሳችሁን መርምሩ። ስራችሁ ሳይመዘንባችሁ በፊት ራሳችሁ መዝኑት።»

ሌሊት እግሮቻቸውን ባለንጋ እየመቱም፡- «ዛሬ ይህን ለምን ሰራህ?» በማለት ራሳቸውን ይወቅሱ ነበር።

ታላቁ ታቢዒ መይሙን ቢን መህራን እንዲህ ብለዋል፡-

«አላህን የሚፈራ ሰው ራሱን ከመንግስትና ከስስታም ሸሪክ የበለጠ ይቆጣጠራል።»

አል ሐሰን እንዲህ ብለዋል፡-

«ሙእሚን ራሱን በጣም ይቆጣጠራል። በዚህች ዓለም ራሳቸውን የሚመረምሩ ሰዎች በመጭው ዓለም ምርመራ ይቀልላቸዋል። በዚህች አለም ራሳቸውን የማይመረምሩ ሰዎች ምርመራው ይከብድባቸዋል።»

የመመርመርን ትርጉም ሲያብራሩ እንዲህ ብለዋል፡-

«ሙእሚን አንዳች ደስ የሚያሰኝ ሐራም ነገር ሲያጋጥመው፡- «ወድጀሐለሁ። ፈልጌሃለሁ። ግና በኔና ባንተ መካከል ግርዶ አለ።» በማለት ይተወዋል። (ይህ ራስን ከተግባር በፊት መመርመር ነው።)

አንዳች መጥፎ ነገር ከሰራም፡- «ለምን ይህን ሰራሁ? ምንም ምክንያት የለኝም። ዳግም ወደዚህ ተግባር አልመለስም» ይላል። (ይህ ከተግባር በኋላ የሚያደርገው ምርመራ ነው።)»

በየቀኑ ራሱን መመርመር ያልቻለ በየሳምንቱ ወይም በየተወሰኑ ሳምንታት ራሱን በመፈተሽ ትርፍና ኪሣራውን ማወቅ አለበት። በየወሩ መጨረሻም ረዘም ያለ ምርመራ ያድርግ። ከአመቱ መቋጫ ላይ ደግሞ የበለጠ ጊዜ ወስዶ ጥልቅ ምርመራ በራሱ ላይ ያድርግ። ያመለጠውን ለማካካስም ቃል ይግባ። በበጀት መዝጊያ ላይ እንደሚከናወነው የሒሳብ ምርመራ አይነት ማለት ነው።

ምእራባውያኑ የፈጠሩትና አንዳንድ ሙስሊሞችም በአሳዛኝ ሁኔታ የሚከተሏቸው አንድ አጉል ባህል አለ። «ክሪስ ማስ» ይሉታል። ከአመቱ መጨረሻ ላይ ሰውየው ከአድሜው አንድ አመት በኃይለ ጊዜ ድግስ ይደግስና ይጨፍራል።

አላህ ላላወደደውና ላልፈቀደው ለዚህ ዓይነቱ አምልኮ ሰዎች ራሳቸውን ማስገዛታቸው ያሳዝናል። ለምሳሌ በአድሚያቸው ቁጥር ልክ ሻማ አብርተው ድራማዊ በሆነ መልኩ ያጠፉታል። በዚህ አጋጣሚም ስጦታዎችን ይለዋወጣሉ። እንኳን ደስ ያለህ (ያለሽ) ይባባሉ።

አስተዋይ ሰው- ከዚህ ትርጉም እና ጥቅም አልባ አጉል ባህል ይልቅ- ከአድሜው አንድ አመት የመጉደሉን አጋጣሚ ተጠቅሞ ማስተዋል፣ ማስተንተን፣ መፈተሽ ይኖርበታል። ብልህ ነጋዴ በየ አመቱ መጨረሻ ላይ የንግድ መዝገቡን ዘርግቶ ንብረቱን እና እዳውን እንደሚያሰላው ማለት ነው። ይህ ሲሆን የንብረቱን መጠን፣ ትርፍና ኪሣራውን ያውቃል። ዛሬ ከትላንት፣ ነገ ከዛሬ የተሻለ እንዲሆንለትም አላህን ይለምናል።

Scanned by CamScanner

አስተዋይ ሰው ከእድሜው ተነጥላ በሄደችው ዓመት የሰራውን ስራ ይፈትሻል። በርሷ አላህ እንደሚቀጣው ያውቃልና። ቀላል ጊዜ አይደለም። ድፍን አመት ነው። 12 ወራት። እያንዳንዱ ወር 30 ቀናት፣ እያንዳንዱ ቀን 24 ሰአታት፣ እያንዳንዱ ሰአት 60 ደቂቃዎች፣ እያንዳንዱ ደቂቃ 60 ሰኮንዶች አሉት። እያንዳንዱ ቅጽበት አላህ የሰገሰው ጸጋ ነው። ከርሰ ዘንድ ያስቀመጠው አደራ ነው።

ያለፈችው ዓመት ከእድሜው ግንብ ፈርሳ የወደቀች፣ የታጠፈች የሕይወቱ ገጽ በመሆኗ ልታሳስበውና ሊቆጭ ይገባው ነበር። እያንዳንዱ ቀን ከእድሜ ዛፍ የምትረግፍ ቅጠል መሆኗን መዘንጋት አልነበረበትም። ከረገፈች በቃ አከተመ። ተመልሳ አትገኝም።

ሐሰነልበስሪ- አላህ ይዘንላቸውና- እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል፡-

«የአደም ልጅ ሆይ፣ አንተ የቀናት ስብስብ ነህ። አንድ ቀን በሄደ ቁጥር ያንተ ከፊል አካል አብሮ ሄዷል።»

አቡ አሊ አልዲቃቅ እንዲህ ሲል ገጥሟል፡-

«ከፊል እኔነቴን ይዞ የሚሄደው እያንዳንዱ ቀን ቀልቤን በቁጭት ሞልቶት ይሄዳል።»

ሌላ ገጣሚም እንዲህ ብሏል፡-

ሌትና ቀን ሲፈራረቁ የሰው ልጅ ይደሰታል።

በነርሱ መፈራረቅ የርሱ ከፊል አካል መሄዱን ዘንግቶ

ሌላውም እንዲህ ብሏል፡-

በምናሳልፋቸው ቀናት አንደሰትም።

እያንዳንዱ ቀን የእድሜን ክፋይ ይዞ ይሄዳልና

አእምሮ ያለው ሰው ማድረግ ያለበት ይህን ነበር። ግና በዚህች ዓለም ውስጥ አስተዋዮች ጥቂቶች ናቸው።

ነገን አሻግሮ ማየት

ነገን አሻግሮ ማየት፣ ስለመጭው ጊዜ ማሰብና መሰናዳት ተገቢ ነው።

የሰው ልጅ በተፈጥሮው ከመጭው ዘመን ጋር የተሳሰረ ነው። ከርሱ ሊነጠል ወይም ችላ ሊሰው አይቻለውም። የማስታወስ ክሕሎቱ ከትላንት ጋር እንደሚያስተሳስረው ሁሉ ስለ ወደፊቱ የማሰም ችሎታውም ከመጭው ዘመን ጋር ያስተሳስረዋል።

የመጭው ዘመን ልዩ ባህሪ ሚስጥር መሆኑ ነው። በውስጡ ምን እንደቋጠረ፣ ምን በጎ ነገር እና ክፋት እንዳዘለ አይታወቅም።

﴿ وَمَا تَدْرِي نَفْسٌ مَّاذَا تَكْسِبُ غَدًا ﴾ لقمان: ٣٤

«የትኛዋም ነፍስ ነገ የምትሠራውን አታውቅም።» (ሉቅማን 34)

ሌላው ባህሪው ሰዎች ሩቅ አድርገው ቢመለከቱትም መምጣቱ አይቀሬና ቅርብ መሆኑ ነው። ለዚህም ነው፡- «ዛሬ ካለ ነገም አለ።»፣ «ነገ ቅርብ ነው» የተባለው። አላህ በቁርአኑ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ وَمَا أَمْرُ السَّاعَةِ إِلَّا كَلَمْحِ الْبَصَرِ أَوْ هُوَ أَقْرَبُ ﴾ النحل: ٧٧

«የሰዓቲ (ትንሳኤ) ነገር እንደ ዓይን ብልጭታ፡ ወይም ከዚያም የፈጠነ ነው።»(አል ነህል 77)

ብልህ ማለት መጭውን ዘመን ከስሌቱ ውስጥ የሚያስገባና ለርሱም ተገቢውን ዝግጅት የሚያደርግ ነው። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا اتَّقُوا اللَّهَ وَلْتَنظُرْ نَفْسٌ مَّا قَدَّمَتْ لِغَدٍ ۖ وَاتَّقُوا اللَّهَ ۚ إِنَّ اللَّهَ خَبِيرٌ بِمَا تَعْمَلُونَ ﴾ الحشر: ١٨

«እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ፍሩ። እያንዳንዷ ነፍስ (ከመልካም ተግባር) ለነገዋ ያስቀደመችውን ታስተውል። አላህን ፍሩ። አላህ የምትሠሩትን ሁሉ ዐዋቂ ነው።» (አል ሐሽር 18)

ሐይማኖት ሰዎችን ከትላንት ጋር ብቻ ያስተሳስራል ብለው የሚያስቡ ወገኖች የሐይማኖትን አስኳልና ምንነት በመረዳቱ ረገድ ስህተት ፈጽመዋል። የሐይማኖት ትልቁ ዓላማ የሰውን ልጅ ከዚህች ዓለም የተሻለና ቋሚ ለሆነው ዘለዓለማዊ ሕይወት፣ ለመጭው ዘመን ማዘጋጀት ነው።

ነገን ማየት የሐይማኖት መሠረት ነው። በሐዲስ የሚከተለው ተገልጿል፡-

Scanned by CamScanner

«ሰውየው በሁለት ፍርሃቶች ማለትም አላህ እንዴት እንደሚያየው በማያውቀው ያለፈ ጊዜና አላህ ምን እንደሚወስንበት በማያውቀው መጭው ጊዜ መሐል ነው። ስለሆነም ከራሱ ለራሱ፣ ከዱንያ ለአኼራው ይያዝ። ከማርጀቱ በፊት በወጣትነቱ ይሰናዳ። ነፍሴ በእጁ በሆነችው ጌታ እምላለሁ፣ ከሞት በኋላ ዳግም የመመለስ አድል የለም። ከዚህች ዓለም በኋላ ከጀነት እና ከእሳት ውጭ ሌላ ነገር የለም።»

ይህ ማለት ግን ሐይማኖተኛ ስለ መጭው ዓለም እንጅ አያስብ፣ ይህችን ዓለም ይዘንጋ ማለት አይደለም። ለነገ መዘጋጀትን፣ ለስኬት የሚያበቃውን ሁሉ ማድረግን እስልምና ያስተምረናል። ለዱንያም ለአኼራም።

ለሙእሚኖች መልካም አርአያ የሆኑት የአላህ መልእክተኛ ለዳእዋቸው የተሳካ መጭ ዘመን ተግተው ሲሰሩ እናያለን። ለዚህም ሲሉ ከአውስና ከኸዝረጅ ጋር ቃል ኪዳን ተጋቡ። በስደት ጉዳይ አሰቡ። ለኢስላማዊው ሸሪዓና ሕብረተሰብ ጠንካራ መሠረት ጣሉ።

ለመጀመሪያውና ለሁለተኛው የዓቀባ ስምምነቶች፣ ከዚያም ወደ የስሪብ ለሚደረገው ስደት ያደረጉት ከፍተኛ መሰናዶ ለእስልምና የወደፊት ሕልውና በአግባቡ ማቀድና እቅድንም በሚገባ መተግበር አይደለምን? በዱንያዊ ጉዳዮች የአላህ መልእክተኛ ለቤተሰቦቻቸው የዓመት ቀለብ ሲያኖሩ እናያቸዋለን። ይህ ግን በአላህ ከመመካት ጋር ተቃራኒ ሆኖ አላገኙትም። ምክንያቱም በአላህ መመካት ማለት ሰበቦችን አለማድረስ ማለት አይደለምና።

ለዛሬ ተገቢውን ትኩረት መስጠት

ሙእሚን ከትላንት የሚማርና ለነገ የሚዘጋጅ ከመሆኑ ጋር ለዛሬ የተለየ ትኩረት ይሰጣል። በእጁ ያሉት ለአታት ከማምለጣቸው በፊት ሊጠቀምባቸው ይተጋል። ኢማም አቡ ሐሚድ አልገዛሊ «ኢህያእ» በተሰኘው መጽሐፋቸው ውስጥ እንዲህ ብለዋል:-

«ጊዜያት ሦስት አይነት ናቸው። አንደኛው ያለፈ ጊዜ ነው። በደስታም ይለፍ በመከራ አልፏልና ሰውየው ምንም ሊያደርገው አይችልም። ሁለተኛው መጭው ጊዜ ሲሆን ሰውየው በሕይወት ይኑር አይኑር የሚያውቀው ነገር የለም። አላህ በርሱ ወስጥ ምን እንደወሰነም አያውቅም። ሦስተኛው የአሁን ጊዜ ሲሆን፣ በርሱ ውስጥ ራስን

መታገልና መምራት፣ አምላክን መጠንቀቅና መትጋት ይጠበቃል። ይህ ሲሆን ነገን ካልኖረ የአሁኑን ለአት በማባከኑ አይቆጭም። ነገን ከኖረም ትላንትን በተገቢው ሁኔታ እንደተጠቀመበት ሁሉ ዛሬንም ይጠቀምበታል። ምኞቱ 50 ዓመታት ተሰጥጦ ራስን ከመቆጣጠር ከመፈተሽና አይዘናጋም። ወኔውም አይዝልም። ይልቁንም የዛሬ ልጅ ይሆናል። በመጨረሻ እስትንፋስ ላይ እንዳለ አድርጎ ራሱን ያያል። ምን አልባትም የአሁኑ ትንፋሽ የመጨረሻው እንደሆነች የሚያውቀው ነገር የለም። ይህ የመጨረሻ እስትንፋሱ ከሆነም ሞትን ጥሩ ባልሆነ ሁኔታ መገናኘት ስለማይፈልግ ሕይወቱ አቡዘር እንደተናገሩት ይሆናል። እንዲህ ብለዋል:-

«ሙእሚን በሦስት ሁኔታዎች ውስጥ ብቻ፣ ማለትም ለመጭው አለም እየተሰነቀ፣ ለዚህች ዓለም ኑሮው እየሰራ ወይም ሐራም ባልሆነ ነገር እየተጠቀመ እንጅ አይገኝም።»

እንዲህ ማለታቸውም ተወስቷል:-

«ብልህ አራት ወቅቶች አሉት። አምላኩን የሚገናኝበት ወቅት፣ ራሱን የሚመረምርበት ወቅት፣ የአላህን ድንቅ ተግባር የሚያስተነትንበት ወቅትና ለምግብና ለውሃ የሚያውለው ወቅት።»

እህል ውሃ ለመቅመስ የሚያውለው ጊዜ ለሌሎች ተግባራቱ እገዛ የሚያደርግለትን ጥንካሬ የሚያገኝበት በመሆኑ የባከነ ጊዜ አይደለም። በተጨማሪም የሚመገበው ምግብና የሚጠጣው ውሃ በውስጣቸው የያዙትን ተአምር ቢያስተነትን ከብዙ የአካል አምልኳዊ እንቅስቃሴዎች የተሻለ ፋይዳ ያገኝበታል።»

አሁንን ተጠቅሞ ለሕይወት መስራት ተገቢ መሆኑን ከሚያሳስቡ ድንቅ ሐዲሶች መካከል ከአሁን ቀደም የጠቀስነው ተከታዩ ሐዲስ ይገኝበታል:-

«ከናንተ አንዳችሁ በእጁ ችግኝ የያዘ ሆኖ እያለ ቂያማ ብትቆም እርሷን ለመትከል ጊዜ እስካገኘ ድረስ ይትከላት።»

የሐዲሱን ይዘት ማስተንተን እና መተንተን አስፈላጊ ሳይሆን አይቀርም። የአላህ መልእክተኛ ይህን ሰው ችግኙን ለመትከል ጊዜ ካገኘ እንዲተክል ለምን አዘዙት? ችግኙ አድጎ ለፍሬ እስኪበቃ ሰውየው በሕይወት እንደማይቆይ እርግጥ ነው። ለነገ ፍሬ ለማግኘት አይደለም ዛሬ የሚተክለው። ቀጣዩ ትውልድ እንዲጠቀምበትም አይደለም። ምክ

Scanned by CamScanner

ንያቱም ቂያማ ተቃርቧል። አንድ አዛውንት የዘይቱን ዛፍ ሲተክሉ ሰዎች አይተዋቸው፡- «ከሞት አፋፍ ላይ ሆነህ ለምን ትተክላለህ?» በማለት ጠየቋቸው። «ከኛ በፊት የነበሩት ሰዎች የተከሉትን እኛ ተመገብን። እኛም መጭው ትውልድ ይመገበው ዘንድ እንተክላለን።» በማለት መለሱ።

በሐዲሱ ላይ የተጠቀሰው ግን ከዚህ ይለያል። ችግኙን የሚተክለው ልክ እንደዚህ አዛውንት ለመጭው ትውልድ አስቦ ነው እንዳይባል ከጥቂት ጊዜ በኋላ ቂያማ ይቆማል። ዓለም ትፈርሳለች። ምድራዊ ሕይወት ያከትማል። ስለዚህም በሕይወት የመቆየት ተስፋ ያለው ሰው የለም።

ታዲያ በዚህ ቅጽበት ችግኙን መትከል ለምን አስፈለገ? ነገሩ ግልጽ ነው። የስራን ክብር ለማጉላት የታለመ ነው። ስራ በራሱ ክብር ነው። ታላቅ ደረጃ አለው። በውጤቱ ሰዎች ተጠቀሙበትም አልተጠቀሙበት። እንደዚሁም የሰው ልጅ ሕይወቱ እስካለ ድረስ ከስራ፣ ከምርት፣ ምድርን ከማነጽ ለአፍታ እንኳ መዘናጋት እንደሌለበት ለማስተማር ነው። ሱራፌል በቀንድ ሊነፋና ሕይወት ልታከትም የተቃረበችበት ሰአት ቢመጣ እንኳ ለቅጽበት ምድራዊ ስራ መቆም እንደሌለበት ለማስገንዘብ ነው።

በዚህ ዓይነቱ ቅጽበት ችግኝ መትከል፣ ላለፈውም ሆነ ለመጭው ዘመን ትኩረት ሳይሰጡ የአሁኑን ጊዜ ግዴታና ሐላፊነት መወጣት ነው።

♠ ♠ ♠

እድሜ እንዴት ይረዝማል?

የሰው ልጅ በተፈጥሮው ሕይወትን ይወዳል። እድሜው እንዲረዝምለት ይሻል። ከዚህም አልፎ ቢችል ዘልዓለም ቢኖር ምኞቱ ነው። ሰይጣን የሰው ልጆችን አባት አደምን ያጠቃውና አላህ የከለከላትን ዛፍ እንዲመገብ የገፋፋቸው በዚህ ዘልዓለም የመኖር የስሜት ቀዳዳ ጩል በመግባት ነው፡-

﴿ فَوَسْوَسَ إِلَيْهِ ٱلشَّيْطَٰنُ قَالَ يَٰٓـَٔادَمُ هَلْ أَدُلُّكَ عَلَىٰ شَجَرَةِ ٱلْخُلْدِ وَمُلْكٍ لَّا يَبْلَىٰ ﴾ ﴿طه ١٢٠﴾

"ግና ሰይጣን ጮተጮተው። "አደም ሆይ! ዝንተዓለም መኖርና የማይወገድ ሥልጣን ማግኘት የምታስችልህን ዛፍ ላመላክትህን?" አለው። (ጣሃ 120)

እስልምና የእድሜን መርዘም ለበጎ ስራ እስከዋለ ድረስ ከትልቅ ጸጋ ቆጥሮታል። ነቢዩ (ሰዐወ) «ከሰዎች ሁሉ በላጩ የትኛው ነው?» ተብለው ሲጠየቁ፡- «እድሜው ረዝሞ ስራው ያማረው ነው።» ሲሉ መለሱ። (ቲርሚዚ)

ግና ሞት ይህን የሰዎች ምኞት እንደሚያጨናግፍ ጥርጥር የለውም። ወጣት በወጣትነቱ ይቀጠፋል። ሙሽራ ባገባ በመጀመሪያው ቀን በሞት ይወሰዳል። ሰውየው ከቤተሰቡ መሐል በሞት ይነጠቃል። ሐብታም ከድሎቱ ይነጠላል። አገረ ገዥ ሞት ጠንካራ ጠባቂዎችን አልፎ ይጎበኘዋል። ለዚህም ነው ሞት፡- «ጥፍጥናን ቆራጭ፣ ሕብረትን በታኝ» የተባለው።

ሞት የጉዞ መጠናቀቂያ፣ የሕይወት ፍጻሜ ከሆነ እድሜ የቱን ያህል ቢረዝምም አጭር ነው። የተወሰኑ ቀናት፣ የተመጠኑ እስትንፋሶች ብቻ። ሞት ያለፈቃድ ይቆርጣቸዋል። ባለቤቱንም «በነበር» ወሬ ውስጥ ይተወዋል።

በሐዲስ የሚከተለው ተነግሯል፡-

«የፈለግከውን ያህል ኑር ትሞታለህ። የፈለግከውን ውደድ፣ ትለየዋለህ። የፈለግከውን ስራ፣ የሰራህን ዋጋ ታገኛለህ። ትጠየቅቢታለህም።» (ጦበራኒ)

Scanned by CamScanner

ልብን በቀዶ ጥገና መተካት የቻለው የሕክምና ሳይንስ፣ የሰውን ልጅ ወደ ጨረቃ ያወጣው ሳይንስ እርጅናን ማስቀረት፣ አዛውንቱን ወጣት ማድረግ አልቻለም። የአላህ መልእክተኛ (ሰዐወ) እንዲህ ብለዋል፡-

«አላህ ያለ መድሐኒት የፈጠረው በሽታ የለም። እርጅና ሲቀር።» (ቡኻሪ)

የሰው ልጅ እድሜ እንዲህ ከሆነ እንዴት ያስረዝረው? በምን መልኩስ ይህን ማድረግ ይችላል?

እድሜ ማለት ከልደት እስከሞት ድረስ ያሉት ቀናት ቁጥር ማለት አይደለም። እውነተኛ እድሜ ከአላህ ዘንድ በጎ ስራ ያስመዘገቡበት፣ የመልካም አድራጎት ድልብ ያስቀመጡበት ጊዜ ነው።

ከመቶ አመታት በላይ በሕይወት ኖሮ አላህን የመፍራትና የበጎ ስራ ክምችቱ ዜሮ ወይም ከዚያ በታች፣ በሂሳብ ቋንቋ «ባለ እዳ» የሆነ ሰው እናገኛለን።

በሌላ በኩል በወጣትነቱ የሞተ፣ ግና ለአላለ መጠን ከደረሰ በኋላ ባሉት ጥቂት አመታት ውስጥ በአድናቆት የሚያስደምሙ ታላላቅ በጎ ተግባራትን ያከናወነ ሰው እናገኛለን።

አንድ ጠቢብ እንዲህ ብሏል፡-

«አንዳንዱ እድሜ ረዝሞ ምርቱ ያንሳል። ሌላው ደግሞ አጥሮ ምርቱ ይበዛል። አላህ እድሜውን የባረከለት ሰው በጥቂት ጊዜያት ውስጥ በታላላት ሊገለጽ የማይችል ስኬት ያስመዘግባል።»

ስለዚህም ሰውየው አላህን በማምለክ፣ ለሰዎች ደግ በመስራትና በጥሩ ምግባር እድሜውን ማርዘም ይችላል። ኢኽላስና ብቃት የታከለበት በጎ ስራ ሁሉ ምንዳና ችሮታ ይሆናሉ።

በጎ ምግባሩ በሌሎች ላይ በሚያሳድረው ተጽእኖ መጠንም የሰውየው ደረጃ ከፍ ይላል። ለምሳሌ ወደ በጎ ከጠራቸው፣ ከእኩይ ካቀባቸው፣ ችግራቸውን ካስወገደላቸው፣ ከበደል ከታደጋቸው፣ ጠላት ከተከላከለላቸው ወይም ግለሰቦችን በተሰይም ማሕበረሰቡን ሊጠቅሙ የሚችሉ ሌሎች በጎ ተግባራትን ከፈጸመ ደረጃው ከፍ ይላል።

ለዚህም ነው በአላህ መንገድ እንደሚደረግ ጅሃድ ዓይነት ተግባራት የበጎ ስራዎች ቁንጮ የተሰኙት። የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

«ወደ መቀናት የጠራ እርሱን የተከተሉ ሁሉ የሚያገኙትን ምንዳ ከነርሱ ምንም ሳይጓደል- እርሱም አነርሱ ያገኙትን ያህል ያገኛል።» (ሙስሊም)

«ጀነት ውስጥ አላህ በርሱ መንገድ ለሚታገሉ ሰዎች ያዘጋጃቸው ሙቶ ደረጃዎች አሉ። በሁለቱ ደረጃዎች መካከል ያለው ርቀት በሰማይና በምድር መካከል ያለውን ርቀት ያህላል።» (ቡኻሪ)

በመሪነትና በሐላፊነት ቦታዎች ላይ ያሉ ሰዎች የሚያሰፍኑት ፍትህም በርካታ ሰዎችን ብሎም ማሕበረሰቡን የሚጠቅም በመሆኑና ራስን ለመታገል፣ ስሜትን መጫን፣ የበደል ግፊትን መቋቋም ስለሚሻ ደረጃው ከፍ ብሏል። በሐዲስ የሚከተለው ተነግሯል፡-

«የፍትሃዊ መሪ አንድ ቀን ከስልሳ አመታት ኢባዳ ይበልጣል።» (ጦበራኒ)

አንድ ሶሐባ ጣፋጭ ምንጮች ባሉበት አንድ ሸለቆ አጠገብ ሲያልፍ በጣም ማረከውና፡- «ከሰዎች ተነጥዬ ለአምልኮ (ለኢባዳ) ከዚህ ሸለቆ ውስጥ ብቀመጥ መልካም ሳይሆን አይቀርም» ሲል አሰበ። ነቢዩንም ፈቃድ ጠየቃቸው። «ይህን አታድርግ። ከናንተ አንዳችሁ በአላህ መንገድ የሚያደርገው ተሳትፎ ከቤቱ ወስጥ ሰባ አመታት ከሚሰግደው ሶላት ይበልጣል። አላህ እንዲምራችሁ እና ጀነት እንድትገቡ አትሹምን? በአላህ መንገድ ዝመቱ። በአላህ መንገድ ለጥቂት ጊዜ የተዋጋ ጀነት ጸደቀችለት» አሉት። (ቲርሚዚና ሐኪም)

በጎ ስራዎች በዚህ አኳኋን ከሚያሳድሩት በጎ ተጽእኖ አኳያ ይበላለጣሉ። ስኬታማ ማለት የበለጠ ደረጃ ያለውን በጎ ስራ ለመስራት የሚተጋ ነው። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ فَبَشِّرْ عِبَادِ ﴿١٧﴾ الَّذِينَ يَسْتَمِعُونَ الْقَوْلَ فَيَتَّبِعُونَ أَحْسَنَهُ ﴾ الزمر: ١٧ - ١٨

«ስለዚህ ለባሮቼ ብሥራት ንገር፣ ለነዚያ ምክርን ለሚሰሙትና መልካሙን ብቻ ለሚከተሉት።» (አል ዙመር 17-18)

Scanned by CamScanner

በጥቂት ጊዜ ግዙፍ ተግባር ያከናወኑ በርካታ ሰዎች አልፈዋል:: ያከናወኑት ተግባር ተአምር ሊሰኝ የሚችል ሆኖ ይገኛል:: ግና የተለየ ተአምር ስለሆነ አይደለም:: አላህ በረከትና ተውፊቅ ስለሰጣቸው እንጅ::

በዚህ ረገድ የአላህ መልእክተኛ (ሰዐወ) በዋነኛነት ይጠቀሳሉ:: በ23 ዓመታት ጊዜ ውስጥ ብቻ የሰውን ልጅ ከጨለማ ወደ ብርሃን አሸጋግረዋል:: የታሪክንም ገጽታ እስከዛሬ ድረስ ቀይረዋል:: ተጽእኗቸው ወደፊትም አላህ እስከፈቀደው ዘመን ድረስ ይቀጥላል:: አዲስ እምነት አነጹ:: ልዩ ትውልድ ኮተኮቱ:: ፍጹም ተምሳሌታዋ የሆነ ማሕበረሰብ ገነቡ:: አለማቀፋዊ መንግስት መሠረቱ:: ገና ከመነሻቸው ጀምሮ በርካታ እንቅፋቶች ቢኖሩባቸውም በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ ይህን ሁሉ ተግባር አከናወኑ::

«መልእክተኛው የተአምር እገዛ ይደረግላቸዋል:: ስለሆነም ከርሳቸው ጋር እኛን ማወዳደር ተገቢ አይደለም» የሚል ሐሳብ ሊነሳ ይችላል:: እውነታው እንዲህ ነው:: የአላህ መልእክተኛ የ«ዳእዋ» እና የትግል ሕይወት የአላህን የተለመዱ ሕጎችና የሕይወት ቀመሮች ተከትሎ የተከናወነ ነው:: ሰዎችን የፈተኑበት ተአምራቸው ከተለመደው ወጣ ያሉ ነገሮች ሳይሆኑ የተከበረው ቁርአን ነው::

ከተለመደው ወጣ ያሉ ነገሮች (ተአምራት) የሚከሰቱት አልፎ አልፎና ማድረግ ያለባቸው ጥረቶች ሁሉ ተሟጠው አልቀው የአላህ እገዛ እንጅ ሌላ ምንም ነገር በሚጠፋባቸው አጋጣሚዎች ብቻ ነው:: በስደት ላይ ይህ ተከስቷል:: አላህ የልቦናን መስከን አወርዶላቸዋል:: በበድር ዘመቻ እለትም ይህው ተስተውሏል:: ማድረግ ያለባቸውን ጥረት ሁሉ አሟጠው ከጨረሱ በኋላ አላህ በ1000 መላኢኮች ረዳቸው::

﴿ وَمَا جَعَلَهُ ٱللَّهُ إِلَّا بُشْرَىٰ وَلِتَطْمَئِنَّ بِهِۦ قُلُوبُكُمْ ﴾ الأنفال: ١٠

«አላህ ይህን ያደረገው ለብስራትና ልቦቻችሁ እንዲረጋጉ ብቻ ነበር::» (አል አንፋል 10)

ኹለፋኡራሺዲን! ሌሎች የነቢዩ ባልደረቦችንና እነርሱን በበጎ የተከተሏቸውን ወገኖች ታሪክም ማስተዋል እንችላለን:: በአስሮች በሚቆጠሩ አመታት ጊዜ ውስጥ ዓለምን አንቅተዋል:: እስልምናን አስፋፍተዋል:: ሕዝቦችን አስተምረዋል:: ከመሐይምነት ሐይማኖትና ባህል ማውጣት! እንደዚሁም ቋንቋቸውን መቀየር ችለዋል:: ኢስላም

መቶ አመታት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ በአለም ሐይማኖታዊ! ስነ ልቦናዊ! አስተሳሰባዊ! ማሕበራዊና ፖለቲካዊ ሕይወት ውስጥ ያሳደረው ተጽእኖ ተመራማሪዎችን አስደንቋል:: ይህ ሁሉ ስኬት የሶሐቦችና ቀደምት ሙስሊሞች ጥረት ውጤት ነው::

ዑመር ቢን አብድል አዚዝ የኸሊፋውን ስርዓት ለማስተካከል! በደልን ለማጥፋትና ፍትህ ለማስፈን ቆርጠው ተነሱ:: በሁለት ተኩል አመታትተ ጊዜ ውስጥ ምድርን በፍትህ ሞሏት::

እንቅፋቶች በበዙና አጋር ባነሰ ቁጥር የበጎ ስራ ሚዛን ይከብዳል:: ምንዳውም ይነባበራል::

ለዚህም ነው ሶሐቦች ከነርሱ በኋላ ከመጡ ትውልዶች የበለጠ ደረጃ ያላቸው:: ምክንያቱም ሌሎች በካዱበት ዘመን እነርሱ አምነዋል:: ሌሎች ሲያስተባብሉ እነርሱ እውነት ብለው ተቀብለዋል:: ቀደምት ሙሐጅሮችና አንሷሮች! ከመካ በድል መከፈትና እስልምና ይፋ ከሆነ በኋላ ከሰለሙት ሶሐቦች የበለጠ ደረጃ ያላቸውም ለዚሁ ነው:: አላህ ይህን በማስመልከት ሲናገር:-

﴿ لَا يَسْتَوِى مِنكُم مَّنْ أَنفَقَ مِن قَبْلِ ٱلْفَتْحِ وَقَٰتَلَ ۚ أُو۟لَٰٓئِكَ أَعْظَمُ دَرَجَةً مِّنَ ٱلَّذِينَ أَنفَقُوا۟ مِنۢ بَعْدُ وَقَٰتَلُوا۟ ۚ وَكُلًّا وَعَدَ ٱللَّهُ ٱلْحُسْنَىٰ ۚ وَٱللَّهُ بِمَا تَعْمَلُونَ خَبِيرٌ ﴿١٠﴾ ﴾ الحديد: ١٠

«ከድል በፊት (ገንዘቡን በአላህ መንገድ) የለገሡና የተዋጋ ዘዚህ ረገድ ከዘገዩት ጋር) እኩል አይደለም:: እነዚያ (ገንዘባቸውን ከድል በፊት የለገሡትና የተዋጉት) ከነዚያ (ከድል) በኋላ ከለገሡትና ከተዋጉት የላቀ ደረጃ አላቸው:: ግና አላህ ለሁሉም መልካምን (ምንዳ) ሲሰጥባቸው ቃል ገብቷል:: አላህ የምትሠሩትን ሁሉ ዐዋቂ ነውና::» (አል ሐዲድ 10)

በተለይም ሕብረተሰብ ሲበከል! ነገሮች ሲበላሹ! ገዥዎች በዳይ! ሐብታሞች ቅንጡ! ጠንካሮች አምባገነን! ዓሊሞች አድር ባይ ሲሆኑ! ብክለት ሲስፋፋ! ንቅዘት ሲንሰራፋ! ደግ ነገር ሲጠፋ! የጥንት ዑለሞች «የፊትና መከሰት እና የዘመን መበላሸት» ባሉት ወይም እኛ:- «ዘመናዊ ጃሂልያ» በምንለው ዘመን የሚሰራ በጎ ስራ ምንዳው ይበዛል:: ደረጃውም ይልቃል:: በእንዲህ ዓይነቱ ውቅት ለአላህ ዲን የሚሰሩ እና ለርሱ በሚታገሉ ሁሉ የዚህ ዘመን ሲሐቦች ናቸው:: ምክንያቱም ዲን

Scanned by CamScanner

እየሸሸ፣ መሐይምነት እየነገሰ ባለበት ዘመን የተገኙ ጀግኖች ናቸውና። ነቢዩ (ሰዐወ) እንዲህ ብለዋል፦

«ፈተና በበዛበት ወቅት ዒባዳ ማድረግ በስደት ወደኔ እንደመምጣት ነው።» (ሙስሊም)

አቡ ኡመያህ ሹአባኒ እንዲህ ሲል አውግቷል፦

ከአቡ ሰአለብ ዘንድ መጣሁና፦ «ይህን አንቀጽ እንዴት ትረዳዋለህ?» አልኩት። «የቱን?» አለኝ። ተከታዩን አንቀጽ አነበብኩለት፦

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ عَلَيۡكُمۡ أَنفُسَكُمۡۖ لَا يَضُرُّكُم مَّن ضَلَّ إِذَا ٱهۡتَدَيۡتُمۡۚ ﴾ المائدة: ١٠٥

«እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ራሳችሁን (ከአሳት) አድኑ። ቅኑን መስመር ከተከተላችሁ የሌሎች መንገድ መሳት ቅንጣት አይጎዳችሁም።» (አል ማኢዳህ 105)

«ባለሙያ ጠቢብ ጠይቂያለሁ። እርሳቸውም የአላህ መልእክተኛ ናቸው።» አለኝና ተከታዩን መናገራቸውን ገለጸልኝ፦

«ከፊላችሁ ከፊሉን በመልካም ይዘዝ። ከመጥፎም ይከልክል። የሚታዘዙት ስስት፣ የሚከተሉት ከንቱ ስሜት፣ አድሎና ሁሉም በራሱ አስተያየት ሊኮራስ ስታይ፣ ነገሩ ከአቅምህ በላይ ሲሆን፣ ራስህን በማዳን ላይ አተኩር። ከኋላችሁ የትእግስት ቀናት ይመጣሉ። በነርሱ ወስጥ መታገስ ፍም የመጨበጥ ያህል ነው። ከነርሱ ወስጥ በጎ የሚሰራ የርሱን ዓይነት ስራ የሰሩ 50 ሰዎችን ምንዳ ያገኛል።» (ኢብን ማጃህ)

አቡ ዳውድ ባሰፈሩት ዘገባም፦ «ከኛ ውስጥ የሐምሳ ሰዎችን ምንዳ ወይስ ከነርሱ ውስጥ?» በማለት ጠየቋቸው። «ከናንተ ውስጥ የሐምሳ ሰዎችን ምንዳ ያገኛሉ።» ሲሉ መለሱ።

በአንድ ዘገባ የዚህ ምንዳ መነባበር ምክንያት ተጠቅሶ እናገኛለን። ይህውም፦ «እናንተ ለበጎ ነገር አጋዥ ታገኛላችሁ። እነርሱ ግን አያገኙም።» ማለታቸው ነው።

ይህም ማለት ነቢዩ በዚህ ሐዲስ ያናገሯቸው ሰዎች እስልምና ከተስፋፋ፣ ሰዎች በገፍ ከገቡበት በኋላ የተቀላቀሉትን ነው። እነዚህ ቀድመው የሰለሙ መሐጆሮች እና አንሷሮች ለእስልምና የሚያግዛቸው

አላገኙም። ይባስ ብሎ ጦርነት ነው የተከፈተባቸው። ሁሉም ዓረቦች በጽኑ ተዋግተዋቸዋል። በመሆኑም እነርሱን የሚስተካከል የለም።

ለሚ ጀሮ፣ የሚቋጥር ልቦና እስካለ ድረስ፣ በየትኛውም መልኩ ተቀባይነት የማግኘት እድል እስካልጠፋ ድረስ በመልካም ማዘዝና ከክፉ መከልከል ተገቢ መሆኑን ይህ ሐዲስ ያስተምራል። ግና በሮች ሲዘጉ፣ ብልሐት ሲጠፋ፣ ነገሩ የሰው ልጅ ሊሸከመው ከሚችለው በላይ ሲሆን ከትእግስት ውጭ ሌላ አማራጭ የለም። አላህ አንዳች ነገር እስኪወስን ድረስ መታገስ ተገቢ ነው።

ትእግስት አሉታዊ ባህሪ አይደለም። እጅ መስጠትና መሸነፍም አይደለም። ሁኔታዎች እስኪመቻቹ ድረስ ከአላት የባሰ ቃጠሎ በወሰጥ እያስተናገዱ መጠባበቅ እንጅ። ለዚህም ነው በሐዲስ፦ «ፍም የመጨበጥ ያህል» የተባለው።

እዚህ ላይ ትእግስት የተባለው ችግሩን ከስሩ የሚቀርፍ፣ ከመሠረቱ የሚያስተካክል፣ ረዥም ትንፋሽ እና የአማኞችን ትብብር የሚጠይቅ ጥልቅ ስራ ማሰብና ማቀድ ሲሆን ይችላል። ግለሰብ የማይችለውን ቡድን ይችለዋል። «ድር ቢያብር አንበሳ ያስር» እንዲል ብሂል። የአላህ በረከት ከስብስብ ላይ ነው። የ50 መሰሎቹን ከዚህም አልፎ የ50 ሶሐቦችን ምንዳ እንደሚያስገኝ የተገለጸው ስራ ይህ ሊሆን ይችላል። በተጨማሪም የ50 ሶሐባችን ምንዳ የሚያስገኘው ተግባር ከነሱም ተግባር ጋር የሚመሳሰል መሆን አለበት። እርሱም ሐቅን አጥብቆ መያዝ፣ እስልምናን ለመርዳትና ጀሂልያን ለመዋጋት መተባበር፣ ነፍስንም ሌሎች ውድ ነገሮችንም በአላህ መንገድ መሰዋት፣ አላህ ብርሃኑን እስኪሞላ ድረስ በዚሁ ጎዳና ላይ መጽናት ናቸው።

♠ ♠ ♠

Scanned by CamScanner

ዳግም መኖር

አላህ አድሱን የሰጠው ሰው ጊዜውን ከላይ በተጠቀሰው መልኩ ለበጎ ስራ በማዋል፣ እድሜውን ያረዝማል። ከሞተ በኋላም አላህ እስከፈቀደው ወቅት ድረስ ይኖራል። ሞቶ ሕያው ይሆናል። ተቀብሮ የሕያውያንን ተግባር ያከናውናል።

ይህ የሚሆነው ከበስተጀርባው ሰዎች የሚጠቀመብትን እውቀት፣ በጎ ተግባር፣ ጥሩ ቅርስ፣ መልካም አርአያ፣ አገልግሎቱ ከርሱ ሕልፈት በኋላም የማይቋረጥ የበጎ አድራጎት ተቋም ወይም ለበጎ ስብእናው ቀጣይ የሆኑ ጥሩ ልጆችን ትቶ ካለፈ ነው።

ሙስሊም አቡ ሁረይራን በመጥቀስ እንደዘገቡት ነቢዩ (ሰዐወ) እንዲህ ብለዋል፡-

«የሰው ልጅ ሲሞት ተግባሩ ይቋረጣል። ሦስት ነገሮች ሲቀሩ። እነርሱም ቀጣይነት ያለው ምጽዋት (ሶደቃ)፣ ሰዎች የሚጠቀመብት እወቀት ወይም ዱዓ የሚያደርግለት ልጅ ናቸው።»

በሌላ ሐዲስ እነዚህ ሦስቱ ነገሮች በዝርዝር ተብራርተዋል፡-

«ሙእሚንን ከሞተ በኋላ ከበጎ ስራዎቹ መካከል (ምንዳቸው) የማይቋረጥበት ያሳለፈውና ያስተማረው እውቀት፣ ትቶት የሄደው በጎ ልጅ፣ ያወረሰው ቁርአን፣ የገነባው መስጊድ፣ ለስንቅ አልባዎች ያነጸው ቤት፣ እንዲፈስ ያደረገው ወንዝ፣ ወይም ከገንዘቡ በሕይወት እያለ የመጸወታት ምጽዋት፣ እነዚህ ተግባራት ከሞት በኋላ ይከተሉታል።»

ሙስሊም ባሰፈሩት ዘገባም ነቢዩ እንዲህ ብለዋል፡-

«መልካም ፈር የቀደደ የርሱንና እስከ እለተ ቂያማ ፈለጉን የተከተሉትን ሁሉ ምንዳ ያገኛል።»

አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ إِنَّا نَحْنُ نُحْيِ ٱلْمَوْتَىٰ وَنَكْتُبُ مَا قَدَّمُوا۟ وَءَاثَٰرَهُمْ ۚ ﴾ يس: ١٢

«እኛ በርግጥም ሙታንን ሕያው እናደርጋለን። (ከመልካሙና ከክፉው) ያስቀደሙትንና (ፈለጉቻቸውንም ትተው) ያሳለፉትን ቋሚ ሥራ እንጽፋለን።» (ያሲን 12)

﴿ يُنَبَّؤُا۟ ٱلْإِنسَٰنُ يَوْمَئِذٍۭ بِمَا قَدَّمَ وَأَخَّرَ ﴿١٣﴾ ﴾ القيامة: ١٣

«የሰው ልጅ በዚያን ቀን ያስቀደመውና ያዘገየው ነገር ሁሉ) ይነገረዋል።» (ቂያማህ 13)

ሰውየው ስለራሱ ትቶት የሚያልፈው የበጎ ተግባር አሻራና ታሪክ ውስን ከሆነችው እድሜው በኋላ የሚኖረው በአመታት ያልተገደበ እድሜ መሆኑን ሰዎች ይስማማሉ። የነብያት አባት ኢብራሂም እንዲህ ሲሉ ዱዓ ቢያደርጉ የሚያስገርም አይሆንም፡-

﴿ وَٱجْعَل لِّى لِسَانَ صِدْقٍ فِى ٱلْءَاخِرِينَ ﴿٨٤﴾ ﴾ الشعراء: ٨٤

«በቀጣዮቹ ትውልዶች ዘንድም በመልካም መዘከር ጻፍልኝ።» (አል ሹዓራእ 84)

ሲሞት ልቦች የሚያገዙለት፣ ዓይኖች የሚያለቅሱለት፣ አንደበቶች በጎን የሚያወሱትና አላህ ይምረው ዘንድ ዱዓ የሚያደርጉለት ሰውና ሲሞት ዓይኖች የማያለቅሱለት፣ ቀልቦች የማያገዙለት፣ አንደበቶች በዱዓ የማያወሱት ሰው እኩል አይደሉም። በሕይወት ውስጥ አሉታዊ እና አፍራሽ፣ በዳይና አምባገነን ሆነው የኖሩ ሰዎች ሲሞቱ በደግ አይወሱም። የሚያለቅስና የሚያዝን፣ በዱዓ የሚያወላቸውም የለም። አላህ እንዲህ ዓይነቶቹን ሰዎች በተመለከተ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ كَمْ تَرَكُوا۟ مِن جَنَّٰتٍ وَعُيُونٍ ﴿٢٥﴾ وَزُرُوعٍ وَمَقَامٍ كَرِيمٍ ﴿٢٦﴾ وَنَعْمَةٍ كَانُوا۟ فِيهَا فَٰكِهِينَ ﴿٢٧﴾ كَذَٰلِكَ ۖ وَأَوْرَثْنَٰهَا قَوْمًا ءَاخَرِينَ ﴿٢٨﴾ فَمَا بَكَتْ عَلَيْهِمُ ٱلسَّمَآءُ وَٱلْأَرْضُ وَمَا كَانُوا۟ مُنظَرِينَ ﴿٢٩﴾ ﴾ الدخان: ٢٥ - ٢٩

«(ፈርዐውንና አጋሮቹ) በርካታ የአትክልት ቦታዎችንና ምንጮችን ትተው አለፉ። አዝመራዎችንም፣ እጅግ የተዋቡ ሕንጻዎችንም። (ሌሎችንም) ይቀናጡባቸው የነበሩ አስደሳች ነገሮችን (ሁሉ ጥሰው ሄዱ)። (ፍጻሜያቸው) እንዲህ ነበር። (ሃብቶቻቸውንም) ሌሎች ሕዝቦች እንዲወርሷቸው አደረግን። ሰማይም ምድርም አላለቀሰላቸውም። (ጥቂት) የመቆየት ዕድልም አልተሰጣቸውም።» (አል ዱኻን 25-29)

እነዚህ ወገኖች ሞተውም ወንጀላቸው አይሞትም። በደላቸው፣ ክህደታቸውና ጥመታቸው አይሞትም። ተከታዮቻቸው ከነርሱ ወርሰዋቸዋልና። ፈለጋቸውን ተከትለውም ይፈጽሟቸዋል።

Scanned by CamScanner

መልካም ፈር የቀደደ የተከታዮቹንም ሁሉ ምንዳ እስከ እለተ ቂያማ የሚያገኝ እንደሆነው ሁሉ መጥፎ ፈር የቀደደውም እስከ እለተ ቂያማ የተከተሉትን ሁሉ እኩያን ሐጢአት ይሸከማል።

ጠቃሚ እውቀት ትቶ ያለፈ ሰው በጎ ስራው እንደማይቋረጠው ሁሉ መጥፎ አሻራና አውዳሚ አስተሳሰብ ትቶ ያለፈውም እኩይ ስራዉ አይቋረጥም። አፈር ከለበሱ በኋላም በመጽሐፍ፣ በጋዜጦች፣ በፊልም፣ በቲአትር ወይም በክሴት ትተዋቸው ያለፉ እኩይ ስራዎቻቸው፣ ከንቱ ንግግሮቻቸው፣ አውዳሚ አስተሳሰቦቻቸው መጥፎ ውጤት ከሞት በኋላም በሚከተሏቸው ወገኖች እጣ ፈንታ ያሳዝናል። ለዚህም ነው አንድ በጎ ሰው እንዲህ ሲሉ የተናገሩት፦

«ሲሞት ሐጢአቱ አብሮት የሞተ ሰው አማረለት። ከሞተ በኋላም ወንጀሉ ሕያው ሆኖ የሚቆይ ሰው ደግሞ ወዮለት።»

♠ ♠ ♠

@iqraabookspdf

ጊዜን የሚገድሉ በሽታዎችን መጠንቀቅ

ጊዜን የሚያጠፋ፣ እድሜን የሚበሉ በሽታዎች አሉ። ካልነቃንና ካልተጠነቀቅን ይጎዱናል። የሚከተሉት በዋነኛነት ይጠቀሳሉ፦

ዝንጉነት

የሰውየውን አእምሮና ልቦና የሚያጠቃ በሽታ ነው። ማለትም በዙሪያው ለሚከናወኑ ክስተቶች ስሜትና ደንታ ያጣል። መምሸትና መንጋት ሰርሱ የተለየ ትርጉም አይሰጡትም። የነርሱን ትርጉምና መልእክት፣ አቅጣጫና ፍጻሜ ለመረዳት ንቃት የለውም። ላዩን እንጅ ውስጡን፣ መጀመሪያውን እንጅ ፍጻሜውን አያይም። ቁርአን ዝ ጉነትን አጥብቆ ያስጠነቅቃል። ባለቤቶቹንም የገሃነም መቀጣጠያዎች እስከማድረግ ድረስ ይዝታል። ከእንስሳት ይበልጥ የጠመሙ እንደሆኑም ይገልጻል፦

﴿وَلَقَدْ ذَرَأْنَا لِجَهَنَّمَ كَثِيرًا مِّنَ الْجِنِّ وَالْإِنسِ ۖ لَهُمْ قُلُوبٌ لَّا يَفْقَهُونَ بِهَا وَلَهُمْ أَعْيُنٌ لَّا يُبْصِرُونَ بِهَا وَلَهُمْ آذَانٌ لَّا يَسْمَعُونَ بِهَا ۚ أُولَٰئِكَ كَالْأَنْعَامِ بَلْ هُمْ أَضَلُّ ۚ أُولَٰئِكَ هُمُ الْغَافِلُونَ ﴿١٧٩﴾﴾ الأعراف: ١٧٩

«የማይገነዘቡባቸው ልቦች፥ የማያዩባቸው ዓይኖች፥ የማይሰሙባቸው ጆሮዎች ያሏቸውን በርካታ ሰዎችና አጋንንት ለገሃነም ፈጠርን። እነርሱ ልባቸው እንደ እንስሳ፥ ከዚያም የባሱ ናቸው። እነርሱ በእርግጥም (ማስጠንቀቂያውን) የዘነጉ ናቸው።» (ሰል አዕራፍ 179)

ላዩን እንጅ ወስጡን፣ ቅርፊቱን እንጅ አስኳሉን የማያዩትንም ኮንኗል፦

﴿وَلَٰكِنَّ أَكْثَرَ النَّاسِ لَا يَعْلَمُونَ ﴿٦﴾ يَعْلَمُونَ ظَاهِرًا مِّنَ الْحَيَاةِ الدُّنْيَا وَهُمْ عَنِ الْآخِرَةِ هُمْ غَافِلُونَ ﴿٧﴾﴾ الروم: ٦ - ٧

«አላህ ቃልኪዳኑን አያፈርስም። ግና ብዙዎቹ ሰዎች (ይህን) አያውቁም። ከዚህች ዓለም ሕይወት ውስጥ የሚያውቁት ግልፁን (ላይ ላዩን) ብቻ ነው። ግና መጭውን ዓለም ዊራሽኑ ይዘነጋሉ።» (ሰል ሩም 6-7)

መልእክተኛውን እንዲህ ሲል አናግሯል፦

Scanned by CamScanner

﴿ وَٱذۡكُر رَّبَّكَ فِي نَفۡسِكَ تَضَرُّعًا وَخِيفَةً وَدُونَ ٱلۡجَهۡرِ مِنَ ٱلۡقَوۡلِ بِٱلۡغُدُوِّ وَٱلۡأٓصَالِ وَلَا تَكُن مِّنَ ٱلۡغَٰفِلِينَ ﴿٢٠٥﴾ ﴾ الأعراف: ٢٠٥

«ጌታህን በመተናነስና በፍርሃት ሰሚት ተውጠህና ከሚፈለገው በላይ ባልጮሳ ቃል (ድምጽ) እና በምስጢር ሟትም ማታም አውሳው። ከዘንጊዎችም አትሁን።» (ሰል ሰዕራፍ 205)

በሌላ አንቀጽም እንዲህ ብሏል፡-

﴿ وَلَا تُطِعۡ مَنۡ أَغۡفَلۡنَا قَلۡبَهُۥ عَن ذِكۡرِنَا وَٱتَّبَعَ هَوَىٰهُ وَكَانَ أَمۡرُهُۥ فُرُطًا ﴿٢٨﴾ ﴾ الكهف: ٢٨

«ልቦናውን እኛን ከማስታወስ ያዘነጋነውን፣ ስሜቱንም የተከተለውን፣ ነገረ ሥራውም ወሰንን ሁሉ ያለፈውን (አማጺ) አትታዘዝ።» (ሰል ከህፍ 28)

ተራራን የሚያንቀጠቅጡ ክስተቶች በዓይናችን ስር እየተፈጸሙ በኛ ላይ ምንም አይነት ተጽእኖ አለማሳደራቸው፣ እንደ ድራማ ወይም ሲኒማ ትእይንት በቸልታ መታለፋቸው በእርግጥም ታላቅ መከራ ነው።

አቡበክር እንዲህ ሲሉ ዱዓ ማድረጋቸውም ለዚሁ ነው፡-

«አላህ ሆይ፣ በኪሣራ ውስጥ አትተወን፣ በድንገት አትያዘን። ከዝ ጉዎችም አታድርገን።»

ሰህል ቢን አብደላህ እንዲህ ብለዋል፡-

«ሦስት አይነት ሰዎችን ከመጎዳኘት ተጠንቀቅ። አድር ባይ ዓሊምን፣ ሱፊ ነኝ ባይ መሐይምንና ገ ጉ አምባገነን።»

በይደር ማቆየት

ጊዜህን በመግደል ላቅ ያለ ድርሻ ያለው አደገኛ በሽታ ስራን ማዘግየት፣ ዛሬ ማከናወን የሚችሉትን ለነገ ማሳደር ነው። ይህ ባህሪ ወደ ቋሚ ልምድነት ከተቀየረ አውዳሚ ነው። አንድ ጠቢብ፡- «ይምከሩን» ተባሉ። «ስራን በይደር ማቆየትን ተጠንቀቁ»አሉ።

ሌላ ጠቢብ እንዲህ ብለዋል፡-

«ስራን በይደር ማቆየት የሰይጣን ወታደር ነው።»

ዛሬን በጠቃሚ እውቀትና በበጎ ተግባር ማሸጥ የዛሬ ግዴታህ ነው። ስራን ለነገ ስታዘገይ ዛሬን ታጣለህ። በእጅህ ያለው ጊዜ ታሪክ ይሆናል። ነገ እንድታጭድ ዛሬ መዝራት አለብህ። ካልሆነ ቁጭት በማይፈይድበት ጊዜ ትቆጫለህ።

ወንድሜ ሆይ፣ በይደር የማቆየት ባህሪ እንዳይቆጣጠርህ አደራ። የስንፍና ቋት፣ አጥፊ ባህሪ ነውና። ተስፋን ይቆርጣል። እድሜን ያሳጥራል። በአቅምህ እንዳትጠቀም ያግድሐል።

ወንድሜ ሆይ፣ ሊይዝህ የሚፈጥን (ሞት) አለና አጉተም ፍጠን። ነገሩ የምር ነወና ብርቱ ሁን። ከእንቅልፍህ ተነስ። ከዝ ጋታህ ንቃ። ያሳለፍከውን ስራ መርምር። ስትመረምር የተውከውን፣ ያበላሸህውን አስታወስ። ጥሩ በሰራኸው ትደሰታለህ። ባጠፋኸው ትቆጫለህ። ለማስተካከልም ትተጋለህ።»

በይደር ማቆየት የሚያስከትለው ጥፋት

ስራን በይደር ማቆየት በርካታ ክፋቶች አሉት።

1) እስከ ነገ እንደምትቆይ አታውቅም። አንድ አገረ ገዥ አንድን ዓሊም ምግብ ጋበዛቸው። ጾመኛ መሆናቸውን ገለጹለት። «ዛሬን ያፍጥሩና ነገ ይጹሙ» አላቸው። «ነገ በሕይወት እንደምናር ዋስትና ትሰጠኛለህን?»አሉት።

ነገን በሕይወት ስለመኖሩ እርግጠኛ የሚሆን አንድም ሰው የለም። ሞት በድንገት ሊወስደው ይችላል። መምጫ ምክንያቶቹም በርካታ ናቸው። አንድ ገጣሚ እንዳለው፡-
የተቅዋ ስንቅ ያዝ አደራ
ምሽቱን አልፈህ
ንጋት ላይ ስለመድረስህ
እርግጠኛ አይደለህምና።

ሳይታመም ድንገት ብዙ ሰው ይሞታል። ቤሕመም የሚሰቃይም ለዘመናት ይኖራል። መገነባው እየተሰፋ ሊያለ በሰላም አምሽቶ የሚያነጋ ብዙ ሰው አለ። ድንገተኛ ሞት ከየትኛውም ዘመን ይልቅ በዘመናችን ይበዛል። የሕክምና ጥበብና ሳይንስ ከስፍተኛ የእድገት ደረጃ ላይ ቢደርሱም እውነታው ይህ ነው። ሕክምና በልብ ድካም፣ በደም

Scanned by CamScanner

ግፊት ወዘተ በድንገት መሞትን ሊያስቀር አልቻለም። ሳይንስ በልዩ ልዩ ዘመን አመጣሽ አደጋዎች፣ ለምሳሌ በመኪና፣ በአውሮፕላን፣ በኤሌክ ትሮኒክስና መካኒካል መሳሪያዎች በድንገት መሞትን አላስቀረም። እንዲያውም በነዚህ ምክንያቶች መሞትን ያመጣው ሳይንስ ነው። ከኢንዱስትሪው ዘመን በፊት የሰው ልጅ ከነዚህ አደጋዎች የተጠበቀ ነበርና።

2) ነገን የመኖር ዋስትና ብታገኝ እንኳ በበሽታ ላለመጠቃትህ፣ በስራ ወይም በአንዳች መከራ ላለመጠመድህ ዋስትና የለህም። በመሆኑም በጎ ስራን አሁን መስራት፣ ሐላፊነትን መወጣት ጥንካሬ ነው። በይደር ማቆየት ግን ስንፍና ነው። ነገ የደካሞች ቀን ነውና። ነገ የራሱ ጉዳዮችና ሐላፊነቶች አሉበትና። ነቢዩ (ሰዐወ) አንድን ሰው እንዲህ ሲሉ መክረውታል፦

«አምስት ነገሮችን ከአምስት ነገሮች በፊት ተጠቀም። ከመሞትህ በፊት ሕይወትህን፣ ከመታመምህ በፊት ጤንነትህን፣ በስራ ከመጠመድህ በፊት ነጻ ጊዜህን፣ ከማርጀትህ በፊት ወጣትነትህን፣ ከመደህየትህ በፊት ሐብትህን ተጠቀምባቸው።» (አህመድ)

አንድ ዓሊም ለአንድ ወጣት እንዲህ ሲሉ መክረውታል፦

«መስራት የማትችልበት ጊዜ ከመምጣቱ በፊት ስራ። እኔ እነሆ ዛሬ መስራት እየፈለግኩ ግን አልችልም።»

ሐፍሷ ቢንት ሲሪን እንዲህ ብላለች፦

«ወጣቶች ሆይ፣ ስራን መስራት በወጣትነት ነው።»

3) አያንዳንዱ ቀን የራሱን ስራዎች እና ግዴታዎች ይዞ ይመጣል። ከስራ ነጻ የሆነ ጊዜ የለም። ዑመር ቢን አብድል ዓዚዝ ከስራ ብዛት በድካም በሚዝሉ ጊዜ፦ «ይህን ለነገ ያቆዩት» ሲባሉ እንዲህ ይሉ ነበር፦

«የአንድ ቀን ስራ እንኳ እንዲህ አዝለፍልፎኝ እያለ የሌላ ቀን ሲታከልበትማ እንዴት እችለዋለሁ?»

ኢብን አጧእ እንዲህ ብለዋል፦

«በጊዜ ውስጥ ያሉ መብቶችን ማድረስ አይከብድም። የጊዜን መብት ግን ማድረስ ይከብዳል። ከአያንዳንዱ ወቅት ውስጥ ለአላህ ማድረስ ያለብህ

አዲስ ግዴታ ምንጊዜም ይኖራል። በርሱ ውስጥ ያለውን የአላህ ሐቅ ላትወጣ የሌሎችን ሐቅ እንዴት ልትወጣ ትችላለህ?»

4) በጎ ነገርን በይደር ማቆየት ነፍስ ይህን መጥፎ ባህሪ እንድትላመድ ያደርጋታል። አንድ ባህሪ ስር ሲሰድ ሁለተኛ ተፈጥሮ ይሆንና ለማስወገድ ያስቸግራል። ሰውየው ለበጎ ስራ መጣደፍ እንዳለበት ቢያምን እንኳ ይህን ለማድረግ አጋዥ ወኔና ፍላጎት ያጣል። ስንፍና ይጫጫነዋል። ይከብደዋል። መሸሸት ይቀለዋል። አንድ ቀን ሲሰራ ቢነሳ እንኳ ከጀርባው ላይ ትልቅ ሸክም የተሸከመ ያህል ይሆናል።

ከወንጀል መቶበትን በይደር ማቆየትም ተመሳሳይ ችግር ያስከትላል። ምክንያቱም ነፍስ ሐጢአት መስራትን፣ በስጋዊ ስሜቶች ወስጥ መሆንን ትላመድና ይህን ማስተው አስቸጋሪ ይሆናል። በየቀኑ ለወንጀል ያላት ፍቅር ይጨምራል። ከሐጢአት መለየት ያቅታታል። የወንጀሏ መጠን ይበዛል። ቀልብ በወንጀል ትሸፈናለች። በጽልመት ትዋጣለች። የመቀናት ብርሃን በስቶ ሊገባት አይቻለውም። በሐዲስ የሚከተለው ተነግሯል፦

«አንድ ሙእሚን ወንጀል በሚሰራ ጊዜ ከቀልቡ ላይ ጥቁር ነጥብ ያርፋል። ሲቶብት፣ ምህረት ሲለምንና ከወንጀል ሲታቀብ ይወገድለታል። ወንጀል ከሰራም ጥቁረቱ ይጨምራል። በመጨረሻም ቀልቡን በሙሉ ይሸፍነዋል። አላህ በተከታዩ ቃል ያወሳው «መመርገም» (ራን) ይህ ነው።»

አሉና የሚከተለውን የቁርአን አንቀጽ አነበቡ፦

﴿ كَلَّا بَلْ رَانَ عَلَىٰ قُلُوبِهِم مَّا كَانُوا يَكْسِبُونَ ﴿١٤﴾ ﴾ المطففين: ١٤

«በፍፁም፣ (ነገሩ ከሐዲያን እንደሚያስቡት አይደለም)፣ ይፈፅሙት የነበረው (ኃጢአት) ልቦቻቸውን ሸፈናቸው፣ (ለናም ትክክለኛውን ጉዳና መመልከት ተሳናቸው፣ የክህደታቸው ለበብ ይህ ነው።» *(አል መጦፊፊን፣14)*

5) ስራ በሕይወት ላለ ሰው ተልእኮ ነው። የማይሰራ በሕይወት ሊኖር አይገባውም፣ አስትንፋስ ያለው ሰው ሁሉ ዱንያዊም ሆነ ዲናዊ ስራ መስራት ግዴታው ነው። ከሙስሊሞች ዘንድ በስፋት የሚታወቅ አንድ አባባል አለ፦

Scanned by CamScanner

«ለዚህች አለም ዘልዓለም እንደምትቆይ እያሰብክ ስራ። ለመጭው ዓለም ነገ እንደምትሞት እያሰብክ ስራ።»

ጊዜን መስደብ

ከመጥፎ ባህሪያት እና ልምዶች መካከል ዘመንን መስደብ እና መተቸት፣ በርሱ ማማረርና፡- «ጊዜ በደለኝ፣ ጨከነብኝ» ብሎ ማሰብ ይጠቀሳል። አንዳንድ ሰውማ ጊዜን የሚያንገላታው ባላጋራ ወይም ሊያጠቃው የሚጠባበቅ ጠላት ወይም ንጹሐንን የሚቀጣ፣ ክፋውዎችን የሚሸልም፣ አድሏዊ ወይም ምክንያትና አመክንዮ አልባ አምባገነን አድርጎ ያየዋል።

ይህ ትክክለኛ ያልሆነ «ጀበርይ»[1] አመለካከት ነው። ግለሰቦችና ቡድኖች በዚህ አመለካከት ተደብቀው ከሐላፊነት ይሸሻሉ። የስራቸውንና የስህተታቸውን ውጤት መሸከም አይፈልጉም። ጥፋታቸውን በሌላ ማላከክ ይሻሉ። ለጥፋታቸው ሌላውን፣ ጊዜን፣ የአምላክን ፈቃድ፣ እጣ ፈንታን፣ ተጨባጭ ሁኔታን ወይም ሌላን ነገር ተጠያቂ ማድረግ ይፈልጋሉ።

የወረደባቸውን መከራ፣ የተነጠቁትን ጸጋ መነሻ ምክንያቶች ከግልብ ግንዛቤ በጸዳ መልኩ በጥልቀት ማየትና መተንተን፣ ከአላህ የተፈጥሮ ሕግ አንጻር ምክንያትን ከውጤት ማገናኘት ይጠበቅባቸው ነበር። ጊዜ አላህ በዘረጋው ሕግና መርህ መሠረት ለሚያስኬዳቸው ክስተቶች ማቋቻ እንጅ ሌላ አይደለም። የተከታዩ ሐዲስ ትርጉም ይህ ነው፡-

«ዘመንን አትስደቡ። አላህ ዘመን ነውና።» (ሙስሊም)

በዘመን ውስጥ የሚገኙ የሕይወት መርሆዎችንና ሕግጋትን ያስቀመጠው አላህ ነው ለማለት ነው።

ሙስሊሞች የአሁድ ዘመቻ አለት ሽንፈት በገጠማቸው ጊዜ፣ ነቢዩ ከመሐከላቸው እያሉ 70 ያህል ሙስሊሞች በተገደሉ ጊዜ፣ ይህ ሰምን እንደተከሰተ ግራ በመጋባት ሲጠይቁ የቁርአን መልስ እንዲህ የሚል ነበር፡-

[1] የሰው ልጅ በራሱ ፈቃድና ነጻነት የለውም ብሎ ማሰብ

﴿ أَوَلَمَّآ أَصَٰبَتْكُم مُّصِيبَةٌ قَدْ أَصَبْتُم مِّثْلَيْهَا قُلْتُمْ أَنَّىٰ هَٰذَا ۖ قُلْ هُوَ مِنْ عِندِ أَنفُسِكُمْ ۗ إِنَّ ٱللَّهَ عَلَىٰ كُلِّ شَىْءٍ قَدِيرٌ ﴿١٦٥﴾ ﴾ ال عمران: ١٦٥

"(ምን!) እናንተ (ከሌሎች ላይ) ያደረሳችሁት ዓይነት መከራ በናንተ ላይ ሲደርስባችሁ፡- "ይህ (ጥቃት) ከየት መጣ?" ትላላችሁን? (መሐመድ ሆይ!) ፡-"እርሱ ከራሳችሁ የመጣ ነው። አላህ በሁሉም ነገር ላይ ቻይ ነውና።" በላቸው።" (አሊ ዒምራን 165)

ቁርአን ይህን አጠቃላይ መርህ በሚከተለው ቃሉ ያጸድቃል፡-

﴿ ذَٰلِكَ بِأَنَّ ٱللَّهَ لَمْ يَكُ مُغَيِّرًا نِّعْمَةً أَنْعَمَهَا عَلَىٰ قَوْمٍ حَتَّىٰ يُغَيِّرُوا۟ مَا بِأَنفُسِهِمْ ﴾ الأنفال: ٥٣

«ይህ የሆነው አላህ ለአንድ ሕዝብ የለገሰውን ፀጋ፣ እነርሱ በነፍሶቻቸው ውስጥ ያለውን (ውስጣቸውን) እስካልቀየሩ የማይቀይር በመሆኑ ነው።» (አል አንፋል 53)

ስለዚህም ሰዎች ጊዜን ከመውቀስና ከማማት ይልቅ ለጥፋታቸው ራሳቸውን ተጠያቂ በማድረግ የጠመመውን ማቅናት፣ የተበላሸውን ማስተካከል ይጠበቅባቸዋል። አንዳንድ ጸሐፍት እና ገጣሚዎች የሕብረተሰቡን መበከል እና ጥፋት ለዘመን በማሸከም እርሱን ሲተቹና ሲወቅሱ ይስተዋላሉ።

አንድ አምባገነን አገረ ገዥ እንዲህ ማሉቱ ተወግቷል፡-

«ጊዜ መንግስት ነው። ጊዜን የሰደበ ቅጣት ይገባዋል።»

ሙእሚን አንዳች የሚጠላው ነገር ሲያጋጥመው ራሱን መፈተሽ፣ ምክንያቱን መመርመር፣ ወደ ጌታውም መቃረብና ምህረት በመለመን መመለስ ይጠበቅበታል። ወላጆቹ አደምና ሐዋ ከጀነት ሲባረሩ ያሉትን ሊል ይገባዋል፡-

﴿ رَبَّنَا ظَلَمْنَآ أَنفُسَنَا وَإِن لَّمْ تَغْفِرْ لَنَا وَتَرْحَمْنَا لَنَكُونَنَّ مِنَ ٱلْخَٰسِرِينَ ﴿٢٣﴾ ﴾ الأعراف: ٢٣

"ጌታችን ሆይ! ራሳችንን በድለናል። ካልማርከንና ካላዘንክልን ከከሣሪዎች እንሆናለን።" በማለት (ጌታቸውን) ተማጸኑ።" (አል አዕራፍ 23)

Scanned by CamScanner

ሙሳ ከአላህ ጋር ተገናኝተው ሲመለሱ ወገኖቻቸው የወንድማቸውን የሐሩንን ምክር ችላ ብለው፣ እርሱን እንደ ደካማ ቆጥረው ጥመት ውስጥ ገብተው፣ ወይፈን እያመለኩ በጠበቋቸው ጊዜ፣ ወደ አምላካቸው በዱዓ እጃቸውን ዘርግተው እንዲህ ነበር ያሉት:-

﴿ رَبِّ ٱغۡفِرۡ لِي وَلِأَخِي وَأَدۡخِلۡنَا فِي رَحۡمَتِكَۖ وَأَنتَ أَرۡحَمُ ٱلرَّٰحِمِينَ ﴿١٥١﴾ ﴾
الأعراف: ١٥١

"(ሙሳም):- "ጌታዬ ሆይ! ለኔም ለወንድሜም ምሕረትን ለግሰን። እዘንልንም። አንተ ከማንም ይበልጥ አዛኝ ነህና።" አለ።"

(አል አዕራፍ 151)

የአላህ አገልጋዮች ከመካከላቸው የተወሰኑት መስዋእት በሆኑ ጊዜ ያሳዩት አቋም የማከተለውን ነበር:-

﴿ فَمَا وَهَنُواْ لِمَآ أَصَابَهُمۡ فِي سَبِيلِ ٱللَّهِ وَمَا ضَعُفُواْ وَمَا ٱسۡتَكَانُواْۗ وَٱللَّهُ يُحِبُّ ٱلصَّٰبِرِينَ ﴿١٤٦﴾ وَمَا كَانَ قَوۡلَهُمۡ إِلَّآ أَن قَالُواْ رَبَّنَا ٱغۡفِرۡ لَنَا ذُنُوبَنَا وَإِسۡرَافَنَا فِيٓ أَمۡرِنَا وَثَبِّتۡ أَقۡدَامَنَا وَٱنصُرۡنَا عَلَى ٱلۡقَوۡمِ ٱلۡكَٰفِرِينَ ﴿١٤٧﴾ فَـَٔاتَىٰهُمُ ٱللَّهُ ثَوَابَ ٱلدُّنۡيَا وَحُسۡنَ ثَوَابِ ٱلۡأٓخِرَةِۗ وَٱللَّهُ يُحِبُّ ٱلۡمُحۡسِنِينَ ﴾ آل عمران: ١٤٦ - ١٤٩

«(ይህ ሁሉ ሲሆን) ቃላቸው:- "ጌታችን ሆይ! ኃጢአታችንን፣ በጉዳዮቻችን ላይ ድንበር አላፊነታችንንም ማርልን። ጽናትም ለግሰን። በከሓዲያን ላይም እርዳን።" የሚል ብቻ ነበር። በመሆኑም አላህ የዚህችን ዓለም ሰኬት፣ የመጭውን ዓለምም መልካም ምንዳ ለገሳቸው። አላህ መልካም ሠሪዎችን ይወዳልና።» (አሊ ዒምራን 147-148)

ሙእሚን የነዚህን ብርቅ ስብእናዎች አርአያነት በመከተል አንዳች ጥፋት በደረሰ ጊዜ ራሱን መፈተሽና ወደ አምላኩ መመለስ ይገባዋል።

=ተፈጸመ=

Scanned by CamScanner